አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3588 | ቅዳሜ ነሐሴ 23 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




## የህዝብ ድምፅ፣ የለውጥ ተምሳሌት

➡ 6



ፎቶ- ከፋይል

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከአዲስ አበባ ምክር ቤት እውቅና ሲበረከትለት

## የመዝናኛ ስፍራዎችን በአዲስ እይታ

➡ 11



ፎቶ፦ ኤ አይ ቻት ጂፒቲ

ውሃ ተጨማሪ ውበት ከፈጠረላቸው የአዲስ አበባ የመዝናኛ አካባቢዎች በከፊል

## የቀጠለው የድል ቅብብሎሽ

➡ 20



ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ

በአትሌቲክስ ስፓርት ውጤታማ በመሆን የኢትዮጵያ መልካም ገፅታ ከገነቡ አትሌቶች ጥቂቶቹ

# የመዲናዋ የዘመናዊነት መልኮች

- በአዲስ አበባ የተገነቡ የተሽከርካሪ ማቆያዎች እና ተርሚናሎች የመዲናዋ የዘመናዊነት ጉዞ ማሳያዎች መሆናቸው ተጠቁሟል

➡ 3



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና ከፍተኛ አመራሮች በጎተራ፣ ቦሌ፣ የካ እና ቀበና የተገነቡ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች፣ ተርሚናሎችና ገበያ ማዕከላትን መርቀው አገልግሎት ባስጀመሩበት ወቅት

# ዲጂታል ክህሎት ለስማርት ከተማ

- የኢትዮ ኮደርስ ስልጠና የመንግስት ሰራተኞችን አፈጻጸም በማሻሻል የመንግስት ተቋማትን አገልግሎት እያዘመነና እያቀላጠፈ መሆኑ ተገልጿል

**በቶለሳ መብራቴ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ የቴክኖሎጂ ግኝት በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት እያደገ ይገኛል። ይህ ፈጣን ዕድገት የሰውን ልጅን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በብርቱ እያገዘ ነው፡፡ ይህም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴው እንዲሻሻል አስችሎታል። ከኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን ጀምሮ እስከ አሁኑ የዲጂታል ዘመን ድረስ ያለው የቴክኖሎጂ ፈጠራና መስፋፋት ሁኔታ ሲታይ፣ ቴክኖሎጂ የዓለም ኢኮኖሚ ዋና መሪና አንቀሳቃሽ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል




ፎቶ ከገፀ ድር

የኢትዮ ኮደርስ ስልጠና በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በማሻሻል ረገድ ግልህ ሚና እያበረከተ ነው

# የአዲስ አበባ የመንገድ መሰረተ ልማት እምርታ

- የመንገድ መሰረተ ልማቷ ከ8 ሺህ 227 ኪሎ ሜትር በላይ ደርሷል

**በስንታየሁ ምትኩ**

የአራት ኪሎ አካባቢ ነዋሪውና የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የሚሰሩት አቶ ተማም ከማል ከሁለትና ሶስት ዓመታት በፊት የነበሩ መንገዶች ጠባብ ከመሆናቸው የተነሳ ወደተለያዩ አካባቢዎች ሲንቀሳቀሱ የትራፊክ መጨናነቅ ያጋጥማቸው እንደነበር ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡ ለምሳሌ ከአራት ኪሎ ወደ መገናኛ ለመድረስ በመንገድ መዘጋጋት ምክንያት እየተንፏቀቁ የሄዱበትን፣ ይህም ከ2 ሰዓት በላይ እንደወሰደባቸው አልፎ ተርፎም፣ ነዳጅ ጨርሰው እንዲቆሙ ያደረጋቸውን አጋጣሚ አስታውሰዋል፡፡

በኮሪደር ልማቱ መንገዱ እንዲሰፋ ተደርጎ በመሰራቱ በዚሁ መስመር በ15 እና ከዚያ ባነሰ ደቂቃ እየደረሱ መሆኑንና ይህም በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት ያባክኑት የነበረውን ጊዜና ገንዘብ መቆጠብ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



# ርዕሰ አንቀፅ



## የተሽከርካሪ ማቆሚያ ልማቶች ምቹ ከተማ የመገንባቱ ሂደት ማሳያ ናቸው!

ድርሻ የምታከናውን ከተማ ናት። ይሁንና ይህን ግዙፍ ስምና ኃላፊነት የሚመጥን የከተማ መሠረተ ልማት ለመገንባት ሳትችል ቆይታለች። በተለይም የመንገድ፣ የሕዝብ ትራንስፖርትና የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማት እጥረት ለዓመታት የከተማዋ የእንቅስቃሴ ችግር አካል ነበር። በ2020 እ.ኤ.አ የዓለም ባንክ ጥናት በአዲስ አበባ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ እጥረት ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ እንዲቆሙ በማድረግ ለትራፊክ መጨናነቅና ለአደጋ መንስኤ እንደሆነ ጠቁሞ ነበር። ይህ ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ መገንባት የከተማዋን የእንቅስቃሴ ሥርዓት ማስተካከል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

የችግሩ ጥልቀት የሚታወቀው የተሽከርካሪዎችን ቁጥር ስንመለከት ነው። በኢትዮጵያ ካሉ ተሽከርካሪዎች ውስጥ፣ አብዛኞቹ በአዲስ አበባ የሚገኙ ሲሆን ይህን የሚመጥን መስተ ልማት መገንባት አንዱ የከተማዋ ኃላፊነት ነው። ከመሰረተ ልማቶቹ መካከል ደግሞ የተሽከርካሪ ማቆሚያና ተርሚናል ግንባታ አንዱና ዋነኛው ነው። ይህንንም በመገንዘብ በትጋት እየሰራች ትገኛለች፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዚህ ሳምንት በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች፣ ተርሚናሎችና ገበያ ማዕከላትን መርቀው ለአገልግሎት ክፍት ማድረጋቸውን ተከትሎ ባስተላለፉት መልዕክት፣ "ከለውጡ በፊት 3 ሺህ ብቻ የነበረውን የአንድ ጊዜ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አቅም እና ምንም ያልነበረንን ተርሚናል በአሁኑ ጊዜ በጥራትና በፍጥነት የተገነቡ፣ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎችን እና ተርሚናሎችን ከ170 ሺህ በላይ ማድረስ ችለናል" ብለዋል፡፡ ይህ ትልቅ እመርታ ነው፡፡ ከመንገድ ላይ የሚያቆሙ ተሽከርካሪዎችን ወደ ዘመናዊ ማቆሚያዎች በመምራትና የከተማዋን መንገዶች ለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች እንዲውሉ በማስቻል አጠቃላይ የትራፊክ ፍሰቱና ምቹነት ላይ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ ነው።

ይበልጥ አስፈላጊው ደግሞ የአዲሱ ልማት ትርጉም በመኪና ማቆሚያ ብቻ የማይገደብ መሆኑ ነው። ሰሞኑን በጎተራ፣ በሌ፣ የካና ቀበና በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና በከተማዋ ከፍተኛ አመራሮች የተመረቁ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎችና ተርሚናሎች የታክሲና የአውቶቡስ ተርሚናል፣ የኤሌክትሪክ መኪና ቻርጅ ማድረጊያ፣አዲስ አበባ የአፍሪካ ተቋማት መቀመጫ፣ የዲፕሎማሲ ማዕከልና ከሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ የመጠበቂያ ቦታ፣ የንግድ ቦታዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ አሳንሰሮችና የደህንነት ሥርዓቶችን አካትተዋል። ከዚህ ቀደም በፒያሳ የተመረቀው የዓድዋ የገበያ ማዕከልና የትራንስፖርት ተርሚናልም ከ101 በላይ የንግድ ሱቆች፣ ባለሁለት ደረጃ የመሬት ውስጥ የታክሲና አውቶቡስ ተርሚናልና የኤሌክትሪክ ቻርጅ ማድረጊያን ያካተተ ነው። ይህ አሁን ላይ የከተማ ልማት ከመንገድ ግንባታ ወደ ሙሉ አገልግሎት ስርአት እየተሸጋገረ መሆኑን ያሳያል።

ስለዚህ የተሽከርካሪ ማቆሚያና ተርሚናል ልማትን ስንገመግም የምንመዝነው የተገነባውን የቁጥር መጠን ብቻ ሳይሆን፣ ለነዋሪው የተፈጠረው ምቾት፣ ለእግረኛው የተፈጠረው ምቹ ቦታ፣ ለትራፊክ የተለቀቀውን የመንገድ አቅም፣ ለንግድ እንቅስቃሴው የተፈጠረውን እድልና ለከተማዋ የተጨመረውን ምቹነት መሆን አለበት። የከተማዋ የወደፊት ርዕይም የበለጠ የተደራጀ፣ የተዋሃደ፣ ለእግረኛና ለሕዝብ ትራንስፖርት ቅድሚያ የሚሰጥ፣ በቴክኖሎጂ የሚመራና የማቆሚያ ሥርዓቱም ዘመናዊነትን ተላብሶ መገንባትን ታላሚ ያደረገ ነው። ዛሬ በከተማዋ የምናያቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለንግድ ሥራ ስንዱ፣ ለእንቅስቃሴ ቀልጣፋና ለዘመናዊ ከተማነት የመጠነች መዲና ለመሆን የሚያስችሏትን ስራዎች እያከናወነች መሆኗን የሚያሳዩ የልማት ምልክቶች ናቸው።

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ትምህርት እና ትውልድ

**ሰናይ ምግባሩ**

ትምህርት ለትውልድ እና ሀገር ግንባታ የሚኖረው አበርክቶ ትልቅ ነው፡፡ የአደጉት ሀገራት የእድገት ምስጢር በዘርፉ ላይ ትኩረት አድርገው መስራታቸው ነው ቢባል ማጋነት አይሆንም፡፡ በእኛም ሀገር የትምህርት ዋጋ ትልቅ እንደሆነ አብዛኞቻችን ልብ የምንለው ጉዳይ ነው፡፡

"...ተማር ልጄ ተማር ልጄ

ወገን ዘመድ የለኝ ሃብት የለኝም ከጄ፤

ስማኝ ልጄ ሌት ፀሃይ ነው

ላልተማረ ሰው ግን ቀኑ ጨለማ ነው፤..." የሚለውን የድምጻዊ አለማየሁ እሸቴ ዘፈን ለዚህ በአስረጅነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ታሪክ ውስጥ፤ በተለይ ከሀገራዊ ለውጡ በፊት ባሉት ዓመታት በትምህርት ተደራሽነቱ ባለፈ ጥራቱ ላይ የተሠራው ሥራ ብዙ ስብራቶች እንደነበሩበት በግልጽ መመልከት ተችሏል፡፡ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ኩረጃን በሚያስቀር መንገድ የአፈታተን መንገዱን ሲቀይር የማለፊያ ውጤት የሚያመጡት በጣም ጥቂቶቹ ብቻ መሆናቸውን ለዚህ በአስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የዘንድሮውን ጨምሮ በየዓመቱ የሚያልፉ ተማሪዎች ቁጥር እያደገ ቢመጣም አሁንም ግን ሰፊ ስራዎች መሥራት የግድ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

በትምህርት መስኩ ዘላቂ ውጤት ማምጣት መሰረቱ ላይ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ጀምሮ ልጆች በምቹ የመማር ማስተማር ሂደት እና በተግባር በተደገፈ ትምህርት አሰጣጥ እያለፉ መምጣት አለባቸው፡፡

የትምህር ት ቤቶች የጥራት ደረጃ መሻሻል ይገባዋል፡፡ ለተግባር ተኮር የማስተማር ሂደት አጋዥ የሆኑ ግብዓቶች በሚገባ መሟላቱን መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ መምህራንም እውቀታቸው እንዲያድግ እና የማስተማር ክህሎታቸው ወቅቱን የዋጀ እንዲሆን ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት ያስፈልጋል ብዬ አስባለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፤ ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ መንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መሰረቱ እንዲስተካከል በማድረግ ረገድ የራሳቸውን አሻራ ማሳረፍ ይጠበቅባቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አዲስ አበባ "ትምህርት ለትውልድ" ንቅናቄን ጨምሮ ዘርፉ ላይ ትኩረት ሰጥታ መስራት በመቻሏ ከሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ መጠነ ማሳለፍ ማስመዝገብ እንደቻለች መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ውጤት የሚያኩራራ ሳይሆን፤ ለተጨማሪ ሥራ የሚያተጋ መሆን አለበት፡፡ እንደ ከተማ ብሎም ሀገር ትምህርት ላይ አሁንም ትኩረት ሰጥተን መስራት ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል እላለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በየትምህርት ቤቶች ያሉ መልካም ተሞክሮዎችን ወደ ሌሎች ማስፋት ይገባል፡፡ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ የሚያሳልፉበትን ሁኔታ እየተመለከትን ነው፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ያለው የመማር ማስተማር ሂደትና መሰል ክንውኖች ለይቶ ወደሌሎቹ እንዲሰፋ ማድረግ ላይ አበክሮ መስራት ይገባል እላለሁ፡፡ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቴ

ዜና ትንታኔ

# የመዲናዋ የዘመናዊነት መልኮች

- **በአዲስ አበባ የተገነቡ የተሽከርካሪ ማቆያዎች እና ተርሚናሎች የመዲናዋ የዘመናዊነት ጉዞ ማሳያዎች መሆናቸው ተጠቁሟል**

በሳህሉ ብርሃኑ



ፎቶ:- ከገጸ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ ከተገነቡ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች፣ ተርሚናሎችና ገበያ ማዕከላት መካከል አንዱ

ትራንስፖርት የከተሞች ‘የደም ዝውውር’ ብቻ ሳይሆን፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን የዕለት ተዕለት ውሎና የኑሮ ሂደት የሚያስተሳስር የልብ ምት ነው ማለት ይቻላል። የአንድን ከተማ ህልውና የሚወስኑት የመሠረተ ልማት አውታሮች ደግሞ በተናጠል ሳይሆን፣ ወጥነት ባለው መልኩ ተቀናጅተው ሲሰሩ የከተማዋን ዘመናዊነት እንደሚያጎሉ እሙን ነው፡፡

መንገዶች ሲዘረጉ አብረው የሚገነቡ ዘመናዊ ተርሚናሎችና የፓርኪንግ (የተሽከርካሪ ማቆያ) ቦታዎች የከተማ መጓጓዣን ከማቀላጠፍ ባለፈ፣ ከተማዋን ለንግድ፣ ለእንቅስቃሴ እና ለኑሮ ምቹ የሚያደርጉ ትላልቅ ማዕከላት ሆነው ያገለግላሉ።

እንደዚሁም ከተማዋን ከትራፊክ መጨናነቅና ከዕለት ተዕለት ውጥንቅጥ ነፃ በማውጣት፣ ለኢኮኖሚ እድገትና ለህብረተሰቡ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ምቹ መሠረት ይጥላል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እያከናወናቸው ያሉ የልማት ስራዎች የዚህ ዘመናዊና የተቀናጀ አስተሳሰብ ሕያው ማሳያ ናቸው። ከተማዋን ለኑሮ ምቹ፣ ዘመናዊ፣ ሳቢ፣ የቱሪዝም፣ የንግድና የኢንቨስትመንት ማዕከል ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ሰፋፊ መንገዶች ከዘመናዊ የእግረኛ መንገዶች፣ የብስክሌት መተላለፊያዎች እንዲሁም ከተቀናጁ የፓርኪንግና የተርሚናል አውታሮች ጋር ተሳስረው እየተገነቡ ይገኛሉ።

ከሰሞኑም የከተማ አስተዳደሩ የከተማዋን ገጽታ የሚያድሱ፣ የትራንስፖርት መጨናነቅን በዘላቂነት የሚቀርፉ እና ለወጣቶች ሰፊ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ የተገነቡ ትላልቅና ዘመናዊ የፓርኪንግ (የተሽከርካሪ ማቆያ) ፕላዛዎችን እንዲሁም የታክሲ እና የአውቶቡስ ተርሚናሎችን መርቆ ለሕዝብ አገልግሎት ክፍት አድርጓል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፣ አስተዳደሩ የሚተገብራቸው ፕሮጀክቶች ሕዝብን በቅንነት ለማገልገል እና የተገቡ ቃሎችን በተግባር ለማዋል የሚከናወኑ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። “ቃላችን አንዳንዶች እንደሚሉት ባዶ ፕሮፓጋንዳ እንዳልሆነ ሥራችን ምስክር ነው፡፡ ህዝባችንን ለማገልገል ቃላችንን በተግባር እየፈጸምን፣ የተናገርነውን በተጨባጭ እያቀረብን የምንሰራው ከልብ ነው” ሲሉም ተደምጠዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በመዲናዋ አራት ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ተርሚናልና የንግድ ማዕከል እንዲሁም ፕላዛ በተመረቁበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፣ በአዲስ አበባ ከተማ ከለውጡ ወዲህ በትራንስፖርት ዘርፍ ታሪካዊና መሰረታዊ ለውጦች መመዝገባቸውን ተናግረዋል፡፡ ከጎተራ እስከ ቦሌ፣ ከየካ እስከ ቀበና በአጭር ጊዜ ተገንብተው የተመረቁት ፕሮጀክቶች የከተማዋን ፈጣን የለውጥ ጉዞ በግልጽ የሚያሳዩ መሆናቸውን አክለዋል።

ከዚህ ቀደም መንገዶች ለእግረኛ፣ ለተሽከርካሪ፣ ለፓርኪንግ እና ለንግድ በአንድ ላይ ይጨናነቁ እንደነበርና አሁን ላይ የተገነቡት ዘመናዊ ተርሚናሎችና የተሽከርካሪ ማቆያዎች የነዋሪዎችን ማህበራዊ መስተጋብር ማጠናከራቸውን እና ለሰዎች ክብር የሚመጥን አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ገልፀዋል።

> **“አዲስ አበባ በአንድ ጊዜ ከ180 ሺህ በላይ ተሽከርካሪዎችን የማቆየት አቅም ያላቸው ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆያ እና ተርሚናሎች ባለቤት ሆናለች፤ የተሽከርካሪ ማቆያዎቹ እስካሁን ከ20 ሺህ በላይ ለሆኑ ወጣቶች የስራ ዕድል ፈጥረዋል”**

አዳዲሶቹ ተርሚናሎች ቀደም ሲል እናቶች እና አረጋውያንን ጨምሮ የከተማዋ ነዋሪዎች ፀሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው በከፍተኛ እንግልት እና መገፋፋት ትራንስፖርት ይጠብቁ የነበረበትን አሠራር በመቀየር፤ በክብር አረፍ ብለው ተራቸውን ጠብቀው የሚስተናገዱበትን ዕድል መፍጠራቸው ተነግሯል።

ፕሮጀክቶቹ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆያዎችን ብቻ ሳይሆን የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያዎችን ያካተቱ በመሆናቸው፣ የአረንጓዴ ትራንስፖርት ራዕይን ለማሳካት ትልቅ ሚና እንደሚጫወቱም ተመላክቷል።

በተጨማሪም የሕዝቡን ደህንነት ለመጠበቅ የደህንነት ካሜራዎች (CCTV) የተገጠሙላቸው ሲሆን፣ ህብረተሰቡ ተገናኝቶ የሚወያይባቸውና ማህበራዊ መስተጋብሩን የሚያጠናክርባቸው ሰፋፊ ፕላዛዎች፣ ሱቆች እና ካፌዎች በውስጣቸው መያዛቸውን ከንቲባ አዳነች በንግግራቸው አንስተዋል።

የአዲስ አበባ የትራንስፖርት ስርዓት ከተናጠል ወደ ተቀናጀና ዘመናዊ አሰራር ስለመሸጋገሩ የሚገልፁት የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ክበበው ሚደቅሳ በበኩላቸው፣ ከተማችን ለረጅም ዓመታት ስትታገልላቸው የነበሩ የትራፊክ መጨናነቅና የፓርኪንግ እጥረት ችግሮች በዘላቂነት የሚፈቱ ትላልቅ መሠረተ ልማቶች እየተገነቡ ነው ብለዋል። አያይዘውም አዳዲሶቹ ማዕከላት የከተማዋን ተሽከርካሪ ፍሰት ከማቀላጠፍ ባሻገር፣ ሾፌሮችና ተሳፋሪዎች ስርዓት ባለው እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ረገድ የላቀ ፋይዳ እንዳላቸው ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ የተገነቡት ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆያዎች የተገልጋዩን እንግልት የሚቀንሱ ስለመሆናቸው የሚገልፁት ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነየር አያልነሽ ሃብተማርያም ናቸው። ኢንጂነየሯ እያንዳንዳቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጁ፣ ሙሉ በሙሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ልዩ ምቾትን የሚያጎናጽፉ ናቸውም ብለዋል፡፡

በውስጣቸው የታክሲ እና አውቶብስ ተርሚናሎች፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ቻርጀሮች እንዲሁም የህዝብ መዝናኛ ስፍራዎች ተካትተዋል። በተጨማሪ የንግድ ሱቆች፣ ካፍቴሪያ እና ሬስቶራንቶች፣ የልጆች መጫወቻ እና ማረፊያ ስፍራዎች እንዲሁም ምቹ የተሳፋሪ መጠበቂያ ስፍራዎች ተሟልተዋል። ተርሚናሎቹ አሳንሰሮችን እና ንጹህ መጸዳጃ ቤቶችን እንዲሁም የደህንነት እና አደጋ ቅድመ መከላከያ ስርዓቶችን ያካተቱም ናቸው፡፡

ፕሮጀክቶቹ በሙሉ አቅማቸው ወደ አገልግሎት ሲገቡ በከተማዋ ጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የተሽከርካሪ ፍሰት እና የእግረኛ እንቅስቃሴ እንዲኖር ከማስቻላቸውም ባሻገር ለከተማዋ የ‘ስማርት ሲቲ’ ውጥን እውን መሆን ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

ከሰባት ዓመታት በፊት 3 ሺህ ብቻ የነበረውን የአንድ ጊዜ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አቅም እና ምንም ያልነበረን ተርሚናል በአሁኑ ጊዜ በጥራትና በፍጥነት የተገነቡ፣ ዘመናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎችን እና ተርሚናሎችን ከ180 ሺህ በላይ ማድረስ ተችሏል። በስራ እድል ፈጠራ በኩልም በፓርኪንግ ዘርፍ ብቻ እስካሁን ከ20 ሺህ በላይ ወጣቶች ወደ ሥራ መግባታቸውንና አዳዲሶቹ ፕላዛዎች፣ ሱቆችና ካፌዎችም ሰፊ የስራ ዕድል ይዘው መጥተዋል።

የዕድገት ጉዞዋን በቁጭትና በታታሪነት እየቀጠለች የምትገኘው አዲስ አበባ፣ ዛሬ ላይ በቅንጅታዊ አሰራር በገነባቻቸው ዘመናዊ መሰረተ ልማቶች የስማርት ሲቲነት ጉዞዋን እያፋጠነች ትገኛለች፡፡

ትራንስፖርትን ከሰዎች ክብር፣ ቴክኖሎጂን ከአረንጓዴ ልማት፣ እንዲሁም የንግድ ማዕከላትን ከማኅበራዊ መስተጋብር ጋር ያጣመረው ይህ አዲስ ምዕራፍ፤ ከተማዋ ለኑሮ፣ ለስራ እና ለዕውቀት ተስማሚ የሆነች እውነተኛ የዕድገት ምዕራፍ ላይ መድረሷን ያመላክታል። እነዚህ ዘመናዊ ተርሚናሎችና ፕላዛዎች የነዋሪዎችን እንግልት በቀላሉ የሚቀንሱ ብቻ ሳይሆኑ፣ መዲናዋን ከቀጣዩ ትውልድ ፍላጎት ጋር የሚያስተሳስሩ የዘላቂ ልማት መሰረቶች ናቸው።

አዲስ አበባ ከዚህ በላይ እንደሚገባት ያመለከቱት ከንቲባ አዳነች አቤቤም መሠረተ ልማቶቹ ከመሀል ከተማ ወደ ዳርቻዎች እየሰፉ እንደሚሄዱና የትራንስፖርትና ማህበራዊ መስተጋብር ቦታዎችም እያንዳንዱን ሰፈር እንደሚያዳርሱ አረጋግጠዋል።

# ከጎስቋላነት ወደ ስልጡን ከተማነት

- **አዲስ አበባ ቀደም ሲል የነበራትን ጎስቋላነት በኮሪደርና በወንዝ ዳርቻ ልማቶች ቀርፋ ምቹ፣ ዘመናዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፎካካሪ ወደ ሆነች ስልጡን መዲናነት መሸጋገሯ ተጠቁሟል**



ፎቶ፡- ገፀ ድር
የቀድሞው እሪበከንቱ አካባቢ ከፊል ገጽታ



ፎቶ- ከገፀ ድር
አዲስ አበባን ውብ ገፅታ ካላበሱ የልማት ስራዎች መካከል አንዱ የሆነው የአራዳ ፓርክ በከፊል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

"ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ፣

አገርም እንደሰው ይናፍቃል ወይ?" የሚሉትን ስንኞች ከዚህ ቀደም ሰዎች ለአዲስ አበባ ያላቸውን ጥልቅ ፍቅርና ናፍቆት የሚገልጹበት የትዝታ ቅኝት ነው። ብዙ የተዜመላትና ከተቆረቆረች ዓመታትን ያስቆጠረችው ይህች ታሪካዊ መዲና፣ ስሟ ያማረ፣ ውስጧ ግን በብዙ መዋቅራዊ ችግሮችና ጎስቋላነት የተከበበ የነበረች፤ ዛሬ ግን ያንን የታሪክ አቧራ አራግፋ ወደ አዲስ የስልጣኔና የዘመናዊነት ምዕራፍ እየተሸጋገረች ትገኛለች።

የመሰረተ ልማት፣ የፅዳት፣ የመልካም አስተዳደር፣ ውስብስብ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አሳስረዋት ምዕተ ዓመቱን የተሻገረች ስሟ ያማረ ውስጧ ግን ብዙ ጉድ የተሸከመ ከተማ ነበረች አዲስ አበባ፡፡ ከተማዋን መልከ ጥፉ ካደረጓት ጉዳዮች መካከል በቀደሙት ጊዜያት የጎርፍ አደጋ፣ የእሳት ቃጠሎ፣ የወረርሽኝ መንስኤ እና የደህንነት ስጋት ሆነው ይታዩ የነበሩ ደሳሳ መንደሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ለዚህም ቋሚ ምስክር ከሆኑ አካባቢዎች መካከል እድሜ ጠገብ የሆኑት እንደ እሪ በከንቱ፣ ዶሮ ማነቂያ፣ ቀበና ዙሪያ እና የቁርጡሚ ወንዝን ታክከው የነበሩ ደሳሳ መንደሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

አሁን ላይ የአዲስ አበባን ለውጥ ለማስተዋል ዓመታት መጠበቅ አያስፈልግም። በሳምንታት ውስጥ ተገንብተው ያለቁ የሚመስሉ የልማት ስራዎች የከተማዋን ገጽታ በፍጥነት እየቀየሩት ይገኛሉ። "አሁን ላይ የመዲናዋን አቧራ አራግፈን የደበዘዘውን ታሪክና ቅርሶቻችንን በተጨባጭ አልምተናል" ሲሉ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የሚገልፁትም ለዚሁ ነው። አሁን በእነዚህ የቀድሞ ደሳሳ አካባቢዎች ለነዋሪዎች ምቹ የሆኑ ጂምናዚየሞች፣ የካፍቴሪያ እና ውብ የእግረኛ መንገዶች ተገንብተውባቸዋል፤ የፈራረሱና መንገድ አልባ የነበሩ መገዶች ተስተካክለዋል፤ የወንጀለኞች መደበቂያ የነበሩ ስርቻዎች ጠርተው አካባቢው ብርሃንና ውበት እንዲላበስ ተደርጓልም ይላሉ ከንቲባዋ፡፡

የጂኦግራፊና ሶሺዮሎጂ ምሁር ዴቪድ ሃርቪ፣ ለከተማ የመብት ጥያቄ (Right to the City) የተሰኘ ታዋቂ ንድፈ-ሐሳባዊ ትንተና አቀንቃኝ ናቸው፡፡ በዚሁ ንድፈ-ሐሳባ መሰረት አንድን ከተማ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን አነስተኛ መንደሮች ማልማት የከተማዋን ቦታ ማሻሻል ብቻ ሳይሆን የቦታ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትልቅ ፋይዳ አለው ይላሉ።

ቀደም ሲል ችላ ተብለው የነበሩ የሕዝብ መጠቀሚያ ቦታዎችን፣ የእግረኛ መንገዶችን እና የጋራ መሰረተ ልማቶችን እንደገና በመገንባት፣ የኅብረተሰቡ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ክፍሎች ንጹሕ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ምቹ የከተማ አካባቢ የመጠቀም መብታቸውን ያጎናጽፋል። ይህ ዓይነቱ የተቀናጀ ልማት ዝቅተኛ መንደሮችን ከዋናው የከተማዋ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንስቃሴ ጋር በቀጥታ በማቀናጀት ነዋሪዎቿ የከተማዋ እድገት ተካፋይና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል ባይ ናቸው ዴቪድ ሃርቪ።

አዲስ አበባም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያከናወነቻቸው የኮሪደር፣ የወንዝ ዳርቻ እና ሌሎች የልማት ስራዎችም ከምሁሩ ዴቪድ ሃርቪ ንድፈ ሐሳባዊ ትንተና ጋር የተዋደደ ሆኖ እናገኘዋለን፤ የአፍሪካ መዲናና የበርካታ የዲፕሎማቲክ ተቋማት መናኸሪያ የሆነችው አዲስ አበባ፣ ስሟን የሚመጥንና ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነ አካባቢን ለመፍጠር በትኩረት እየሰራች ትገኛለች፡፡ የዘመናዊነት አኗኗርን በመላው ሀገሪቱ በማስፋፋት መሰረተ ልማትን በሁሉም አካባቢዎች በፍጥነት ማዳረስ ወሳኝ ጉዳይ ሆኗል። በወንዝ ዳርቻዎችም ሆነ በኮሪደር ልማት እየታዩ ያሉ ለውጦች ከተማዋን ከማዘመን ባለፈ፣ የነገውን ትውልድ ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን የውጭ ሀገራት ዜጎችም ጭምር ሲናገሩ ተደምጧል።

በአዲስ አበባ ከተማ የተከናወነው አስደናቂ የኮሪደር ልማት ሥራ፣ ከተሞችን እንዴት ለዜጎች ምቹ፣ ውብና ተስማሚ አድርጎ መገንባት እንደሚቻል ለመላው ዓለም ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ ዳንኤል ካርል ገልጸዋል። መቀመጫቸውን በእንግሊዝ ሀገር ያደረጉ ስምንት ዓለም አቀፍ ምሁራንና ጋዜጠኞች በአዲስ አበባ ፈጣን የለውጥ ጉዞ ላይ ጥናት ማካሄዳቸውን ጋዜጠኛው የገለጸ ሲሆን፣ ይህ ጥናታዊ ግኝታቸውም በቅርቡ መጽሐፍ ሆኖ ታትሟል።

በጥናቱ ላይ በንቃት የተሳተፈው ጋዜጠኛ ዳንኤል ካርል፤ ከዓመታት በፊት የምናውቃት አዲስ አበባ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ባከናወነችው ዘመናዊ የከተማ ልማት ግንባታ በአሁኑ ወቅት ዓለም ሁሉ ሊያያቸውና ሊጎበኛቸው ከሚጓጓላቸው ከተሞች ተርታ መሰለፏን ይገልጻል። ከተማዋ በአሁኑ ወቅት በአረንጓዴ ሽፋኗ፣ በበለጸገ ውበቷ እንዲሁም በእግርና በሳይክል ለመጓዝ ባላት ምቹነት እንደ ባርሴሎና፣ ሞናኮና ዱባይ ካሉ የዓለም ታዋቂ ከተሞች ጋር እንደምትመሳሰል ጋዜጠኛው ጠቁሟል።

ቀደም ሲል የሚሸቱ፣ መርዛማና ሕገ-ወጥ ድርጊቶች ይፈጸሙባቸው የነበሩት ወንዞች ዛሬ ማራኪ የተፈጥሮ መዝናኛዎች ሆነዋል። ይህም የነዋሪዎችን የዕይታ ለውጥ በማምጣት መስታወት ሳይዘጉ ማለፍ በማይቻልበት ቦታ፣ አሁን ቤተሰብን ይዞ መዝናናት፣ ንጹሕ አየር መተንፈስና ልጆችን ማጫወት ተችሏል። እንዲሁም በትራንስፖርት መጨናነቅ ፈንታ፣ ነዋሪዎች በማራኪ የእግር መንገዶች አዕምሯቸውን እያደሱ ለመጓዝ ችለዋል።

በእርግጥ የከተማ ወንዞችን ማልማት የውበት ሥራ ብቻ አይደለም፤ የከተማን ነፍስ የመታደግ፣ የሕዝብን ጤና የመጠበቅና ዘላቂ የኢኮኖሚ መሠረትን የመጣል ስልታዊ ኢንቨስትመንት እንጂ። ወንዞችን ከብክለት በማዳን አረንጓዴ ሥነ- ምህዳርን ሲመልሱ፣ ይህ ለቀጣዩ ትውልድ የሚተርፍ የነቃ እና ውብ ታላቅ የከተማ ልማት የታሪክ አሻራ ነው። የኮሪደር ልማት ስራው የመዲናዋን ሽፍንፍን ገልጦ ልዩ ውበት አላብሷታል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደሚገልጹትም የአዲስ አበባ ከተማ የኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማት ዘላቂነት ባለው አግባብ ለነዋሪዎቿ ኑሮ የተመቸችና የላቀች፣ ውብ መኖሪያ ከተማ የማድረግ ዘመን ተሻጋሪ ፋይዳ አለው።

መቀመጫውን በሕንድ ያደረገው ኦብሰርቨር ሪሰርች ፋውንዴሽን የተሰኘው ዓለም አቀፍ የጥናት ተቋም መረጃ እንደሚያሳየው፣ የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ የኮሪደር ልማት ሥራዎች የዜጎችን የኑሮ ጥራት ማዕከል ያደረገ የከተማ ትራንስፎርሜሽን ምርጥ ተሞክሮ መሆኑን ነው። ከልማቱ ጋር ተያይዞ ከቀደመ ቀያቸው የተነሱ ዜጎች አብሮነታቸው ሳይናጋ፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የመጫወቻ እና የመዝናኛ ስፍራዎችን እንዲሁም የንግድ ቦታዎችን ያካተቱ ዘመናዊ መሠረተ ልማቶች በተሟሉላቸው መንደሮች እንዲኖሩ መደረጉ የዜጎችን የኑሮ ጥራት ማዕከል ያደረገ የልማት ማሳያ መሆኑ ተረጋግጧል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተከናወኑ መጠነ ሰፊ የመሰረተ ልማት እና የአገልግሎት ማሻሻያ ስራዎች ለከተማዋ የላቀ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እያተረፈላት ይገኛል። ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባቀረቡት የ2018 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርት እንደገለጹት፣ አዲስ አበባን ወደ ስማርት (ስሉጥ) ከተማነት ለመቀየር እየተደረገ ባለው ተከታታይ ጥረት በርካታ ታዋቂ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችንና እውቅናዎችን ለመቀዳጀት ችላለች።

እ.ኤ.አ 2024 በደቡብ ኮሪያ የተበረከተውና ለከተማዋ ከፍተኛ አመራር እውቅና የሰጠው የ'ሴኡል ስማርት ከተማ ሽልማት' አንዱ ነው፡፡ እንደዚሁም በናይሮቢ ኬንያ በተካሄደው የአፍሪካ ስማርት ከተሞች ኢንቨስትመንት ሰሚት ላይ አዲስ አበባ 'የአፍሪካ ምርጥ ስማርት ከተማ ሽልማት (እ.ኤ.አ 2024)' ባለቤት ለመሆን መብቃቷ ይታወሳል። ይህም ከተማዋ በአህጉሪቱ ካሉ ግንባር ቀደም መዲናዎች ጋር በቀዳሚነት ያስጠቅሳታል።

አዲስ አበባ ከነበራት ምዕተ ዓመታትን የተሻገረ የጎስቋላነትና የብዙ ጉድ አዙሪት ወጥታ ወደ ስልጡን፣ ዘመናዊና ምቹ ከተማነት ያደረገችው ሽግግር ታሪክን በተግባር የመለወጥ ትልቅ የታሪክ አሻራ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ፕላን ባለሙያው መስፍን አለሙ እንደሚገልፁትም የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች የከተማዋን ውበትና የነዋሪዎችን የኑሮ ጥራት ከማሻሻላቸው ባሻገር፣ ለአፍሪካና ለአዳጊ ሀገራት ከተሞች ትልቅ ተግባራዊ ሞዴል መሆን ችለዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ የተመዘገቡት ዓለም አቀፍ ሽልማቶችና የምሁራኑ አዎንታዊ ግምገማዎች እንደሚያስረዱት፣ ከተማዋ የያዘችው የለውጥ ጉዞ ስሟን ከፍ የሚያደርግና የአፍሪካ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን በላቀ ደረጃ የሚያጎላ ነው።

ከዚህ ቀደም ጠባብና ለአደጋ ተጋላጭ የነበሩና መሰረታዊ የሆኑ የመሰረተ ልማት አውታሮች (እንደ ንጹህ ውኃ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ እና የመብራት ኔትዎርክ ያሉ) ያልተሟሉላቸው በርካታ መኖሪያ መንደሮች ዛሬ ላይ ገጽታቸው ተቀይሯል።

አሁን ላይ የከተማዋን ነዋሪዎች ሰብዓዊ ክብር የሚመጥን፣ ንጹህ አየር የሚተነፍሱበትና ለኑሮ ምቹ የሆነ ውብ የከተማ ከባቢን ተላብሰዋል። እንደ እሪ በከንቱ፣ ዶሮ ማነቂያ፣ ቀበና ዙሪያ እና ወንዞችን ታክከው የነበሩ ደሳሳ መንደሮች የተሰራው የኮሪደር ልማት ስራ የድሮውን ኋላቀርነት በመቀየር ለአዲስ አበባ የዘመናዊ ከተማነት ትልቅ ማሳያ ሆኗል።

# ዲጂታል...

ሞተር ለመሆን የበቃ ይመስላል።

በአሁኑ ወቅት የዓለም ሀገራት የኃይልና የሃብት ውድድር መለኪያ ከባህላዊው የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት ወደ ቴክኖሎጂና የሳይበር የበላይነት ተቀይሯል። ይህ የቴክኖሎጂ እሽቅድምድም የዘመናችንን ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚና ጂኦፖለቲካዊ ሚዛን በቀጥታ የሚወስን ዋነኛ መስክ ሆኗል ሊባል ይችላል።

ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ገዥ ብቻ ከመሆን አልፋ የራሷን አዳዲስ ፈጠራዎች በማመንጨት በጥቅም ላይ ከሚያውሉ ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች። የሀገርን የዲጂታል አቅም በዘላቂነት ለማሳደግ ቴክኖሎጂ መግዛት ብቻ በቂ ባለመሆኑ፣ በዋናነት ቴክኖሎጂውን በአግባቡ የሚጠቀም፣ የሚገነባ፣ የሚያሻሽልና አዳዲስ ፈጠራዎችን ማመንጨት የሚችል የበቃ የሰው ኃይል ማፍራት ላይ ትኩረት ማድረግ ላይ ጠንካራ አቋም ይዛ እየሰራች ትገኛለች፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ወደ አጠቃላይ ዲጂታል ኢኮኖሚ እና ዘመናዊ የአሰራር ሥርአት ለመሸጋገር ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች። የኢትዮ ኮደርስ መርሃ ግብር ለዚህ የሽግግር ሂደት መሳካት እንደ አንድ ግብዓት የሚጠቀስ ነው፡፡

ከ3 ዓመት በፊት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት ይፋ የተደረገው የ'5 ሚሊዮን ኢትዮ-ኮደርስ' ኢኒሺዬቲቭ የሰው ኃይልን በዲጂታል ክህሎት ለማብቃት ያለመ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ነው። ይህ መርሃ ግብር በዋናነት በወጣቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በፕሮግራሚንግ፣ በዳታ ሳይንስ፣ በአንድሮይድ ልማት እና በሰው ሰራሽ አስተውሎት ዘርፎች ላይ ነጻ እና ዘመናዊ የኦንላይን ስልጠናዎችን በማቅረብ ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ሰርቲፊኬት የሚያስገኝ አሰራርን ዘርግቷል።

የዚህ ስልጠና ተጠቃሚዎች በሀገር ደረጃ ትርጉም ያለው ልዩነት እያመጡ ስለመሆኑ የሚያመላክቱ ውጤቶች አሉ፡፡ ለአብነትም በዲጂታሉ ዓለም ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ወጣቶች ቁጥር መበራከት እና በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች መዘመንና መቀላጠፍ ሊጠቀሱ የሚችሉ ውጤቶች ናቸው፡፡

በኢትዮ ኮደርስ መርሃ ግብር አማካኝነት በመንግስት ሰራተኞች ዘንድ መልካም የሚባል የስራ ባህል እየዳበረ ነው፤ በተለይ በዲጂታል ክህሎት ላይ ግልጽ ልዩነት ተፈጥሯል። በአሁኑ ጊዜ የፋይዳ ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት፣ የኤሌክትሮኒክስ ግብር አከፋፈል ስርዓት እና የተለያዩ አገልግሎቶች በኦንላይን እንዲሰጡ መደረጉ የቢሮክራሲ ሂደቶችን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣ ይገኛል።

በዚህ መሻሻል ውስጥ የኢትዮ ኮደርስ መርሃ ግብር አበርክቶ እንደዋዛ የሚታይ አለመሆኑን ከአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያረጋግጣል፡፡በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ግልጽ አሰራርን ለመገንባት ያለመውን የ'ስማርት ሲቲ' ራዕይ ለማሳካት ይህ መርሃ ግብር ትልቅ እገዛ እያደረገ ስለመሆኑም መረጃው ያመለክታል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮ ኮደርስ ስልጠና በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በማሻሻል ረገድ ግልህ ሚና እያበረከተ ነው

ቴክኖሎጂን በአግባቡ የሚጠቀም የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ያለው የ'5 ሚሊዮን ኢትዮ ኮደርስ ኢኒሺዬቲቭ' ስልጠናውን በተከታተሉ የመንግሥት ሰራተኞች አፈፃፀም ላይ ተጨባጭ መሻሻል አስገኝቷል፡፡

ይህ የዲጂታል ክህሎት የከተማዋን የ'ስማርት ሲቲ' ግንባታ እውን የማድረግ አቅምን አጠናክሯል፡፡ አንድ ከተማ 'ስማርት' ወይም ስሉጥ ሆነ የሚባለው አንድም አሰራርን ከወረቀት ንክኪ ነፃ ማድረግ ሲሆን፣ የአገልግሎት ጥራት ሲሻሻልና ውሳኔዎች በዳታ ላይ ተመስርተው ሲሰጡ የበለጠ ይረጋገጣል። ይህ ፅሑፍ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ 985 ሺህ 150 ግለሰቦች ለኢትዮ ኮደርስ ስልጠና የተመዘገቡ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ 870 ሺህ 582 ሰልጣኞች ስልጠናቸውን በአግባቡ አጠናቅቀው ሰርቲፊኬት ተቀብለዋል።

ስልጠናው የመንግስት ሰራተኞችን፣ ወጣቶችን እና የከተማዋን ነዋሪዎች ያካተተ እንደሆነም በአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ እና ስልጠና ቡድን መሪ አቶ ባይሳ ኢፋ ተናግረዋል፡፡ የኢትዮ ኮደርስ ኢኒሺዬቲቩ ዋና ዓላማ በሀገር ደረጃ የዲጂታል አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማዘመን መሆኑን የጠቀሱት ቡድን መሪው፤ ስልጠናው በተለይም አዲስ አበባ የጀመረችውን 'ስማርት ሲቲ' የመገንባት ውጥንን በእጅጉ እንደሚያግዝ አስረድተዋል።

> **"የኢትዮ ኮደርስ ኢኒሺዬቲቭ የመንግሥት ሰራተኞችን በዲጂታል ክህሎት በማነጽ፣ አዲስ አበባን በአፍሪካ ተወዳዳሪ ከሆኑ ስማርት ከተሞች ተርታ እንድትሰለፍ የማስቻል አቅም ያለው በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ይገኛል"**

የስልጠናው ሌላኛው ዓላማ፤ በኮዲንግ እና በሶፍትዌር ልማት የበቁ ወጣቶችን ለማፍራት፣ የኤሌክትሮኒክስ (የኢንተርኔት ላይ አገልግሎት) አሰጣጥን ለማፋጠን፣ እንዲሁም በከተማዋ የትራንስፖርት፣ የቆሻሻ አያያዝ፣ የመንገድና የውሃ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት አብራርተዋል።

በተጨማሪም የዲጂታል ክህሎት በማሳደግ ለወጣቶች የስራ እድል እና የፈጠራ አቅም የሚፈጥር በመሆኑ፣ በአሁኑ ወቅት በአዲስ መሶብ እና በሌሎች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ፈጣን፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት ለመስጠት ብቁ የሰው ኃይል ማቅረብ ተችሏል።

ይህ ሥልጠና ሰራተኞች ቴክኖሎጂዎችን በቅጡ ተገንዝበው ከዲጂታል ስርዓት በስተጀርባ ያሉ አሰራሮችን (Algorithms) በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ በማድረግ ረገድ ትልቅ ለውጥ አምጥቷል። የሥልጠናው ዋና ዓላማ በማንኛውም ዕድሜና የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍል ለዲጂታሉ ዓለም ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ፣ ፈጠራና ኢኖቬሽንን ማበረታታት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተቶችን ማጥበብ እንደሆነ አቶ ባይሳ አብራርቷል።

የሥልጠናው ተጠቃሚ ሰራተኞች በስራ ቦታቸው ኮምፒውተርና ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በብቃት በመጠቀም ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ መደላደል ፈጥሯል። በተጨማሪም ሰራተኞችን ወደ ዲጂታል ዓለም ለማምጣት የሚደረገውን ጉዞ ያፋጠነና ከተማዋን ወደ ሙሉ 'ስማርት ሲቲ'ነት ለማሸጋገር ለሚደረገው ጥረት ጠንካራ መሰረት የጣለ መሆኑ ተመላክቷል።

አቶ ባይሳ ከኢትዮ ኮደርስ ኮርሶች መካከል የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ፕሮግራሚንግ እና አንድሮይድ ሶፍትዌር ልማት ስልጠናዎችን በመውሰድ በዕለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴያቸው ላይ ከፍተኛ ቅልጥፍና ማምጣታቸውን ጠቁመዋል።

በከተማ አስተዳደሩ ሥር በሚገኙ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ በርካታ ሰራተኞችና አመራሮች በዚሁ ሥልጠና ውስጥ ያለፉ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ባይሳ፣ በተለይም በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ሰራተኞችና አመራሮች በዚሁ ሥልጠና ተሳትፈው እውቀታቸውን እያዳበሩ መሆኑን ገልጿል።

ስልጠናውን ከወሰዱ የከተማ አስተዳደሩ ሰራተኞች መካከል ከዚህ ቀደም ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኤክስኪዩቲቭ ፀሐፊ የምስራች አሰፋ፣ የስልጠናው ውጤት በመሥሪያ ቤታቸው በተግባር መታየት መጀመሩን ገልፀዋል።

ቀደም ሲል በካቢኔት ውስጥ ሰነድ ለመፈለግ ይባክን የነበረው ጊዜ ቀርቶ፣ መረጃዎችን በቀላሉ ማደራጀትና ሲፈለግም ከመረጃ ቋት ማግኘት ተችሏል፤ ይህም የህዝብን እንግልት በእጅጉ ቀንሷል። በተጨማሪም ሰራተኞች የሶፍትዌርና የዳታ አያያዝ ችግሮችን በራሳቸው አቅም መፍታት የጀመሩ ሲሆን፣ ይህም አዳዲስ የቴክኖሎጂ አሰራሮችን የመቀበልና የፈጠራ አስተሳሰብን የማዳበር ትልቅ አቅም ፈጥሮልናል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ስማርት ሲቲ ግንባታ ስኬታማ የሚሆነው ቴክኖሎጂውን የሚመራና የሚጠቀም የሰለጠነ የሰው ኃይል ሲኖር ነው። የኢትዮ ኮደርስ ኢኒሺዬቲቭ የመንግሥት ሰራተኞችን በዲጂታል ክህሎት በማነጽ፣ ለከተማዋ የዘመናዊነት እና ስሉጥነት አስተማማኝ መሰረት እየጣለ ይገኛል።

ሰራተኞች ያገኙትን እውቀት ወደ ተግባር በመቀየር የሚያሳዩት ውጤትም አዲስ አበባን በአፍሪካ ተወዳዳሪ ከሆኑ ስማርት ከተሞች ተራ እንድትሰለፍ የማስቻል አቅም ያለው በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል።

# የሕዝብ ድምጽ፣ የለውጥ ተምሳሌት

**በጊዜው አማረ**

የመዲናችን አዲስ አበባ ፈጣን ዕድገት፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ጉዞ ሲነሳ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አስተዋጽኦ አብሮ ይጠቀሳል፡፡ ተቋሙ "የትውልድ ድምፅ" በመሆን የመዲናዋን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለሀገር ውስጥ እና ለዓለም አቀፍ ተመልካቾች ተደራሽ ከማድረግ ባለፈ፣ ህብረተሰቡን እያዝናና በማስተማር እና ለለውጥ በማነሳሳት ታላቅ ሀገራዊ ሀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በአሁኑ ወቅት እንደ ኮሪደር ልማት፣ የወንዝ ዳርቻ ልማት እና አረንጓዴ አሻራ ያሉ ትላልቅ የከተማዋን ፕሮጀክቶች ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ ረገድ የጎላ ሚና አለው። የመዲናዋ ነዋሪዎች የልማት ስራዎቹን አላማና ጥቅም ተረድተው የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የማስገንዘብ ስራም በሰፊው በመስራት ላይ ይገኛል።

ተቋሙ መረጃ በመስጠት ብቻ ሳይወሰን፣ በይዘቶቹ ውስጥ እያዝናኑ የማስተማር ስልትን በስፋት ይጠቀማል። በአዲስ ቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ (FM 96.3)፣ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ እና በዲጂታል አማራጮች የሚቀርቡት ትምህርታዊ፣ የኪነ-ጥበብ ዝግጅቶች፣ የመዝናኛ ፕሮግራሞች እና ጹሁፎች ህብረተሰቡ በመዝናናት ውስጥ ሆኖ ስለ ከተማዋ ደንብና ስርዓት፣ ስለ ጤና፣ ስለየከተሜነት አኗኗር ዘይቤና ማህበራዊ አብሮነት አስፈላጊ ትምህርቶችን እንዲያገኝ እያደረጉ ነው፡፡

ከዲጂታል ዘመን ጋር አብሮ የሚጓዘው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ፣ ወጣቱን ትውልድ በዲጂታል ማህበራዊ ሚዲያዎች በቅርበት በማግኘት ገንቢና አስተማሪ ዘገባዎችን ያሰራጫል፡፡ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በከተማዋ የሚከናወኑ ማህበራዊ ሁነቶችን፣ የምገባ ማዕከላትን፣ ሴቶችና ህፃናትን ታሳቢ ያደረጉ ስራዎችን በመስራት ነዋሪዎች በልማት፣ በበጎ አድራጎትና በወል ትርክት ግንባታ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያነቃቃል፤ ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሚዲያው የመዲናዋ ነዋሪዎች ሀሳብና አስተያየት የሚንጸባረቅበት፣ የተጠቃሚነትና የአገልግሎት ጥያቄዎች የሚነሱበት የህዝብ ድምፅ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በህዝቡ መካከል የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ ነው። ለአብነትም አገልጋዩ እና ዋርካ የተሰኙ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሚዲያው ባስመዘገበው ተጨባጭ ውጤት እና ለከተማዋ ዕድገት እያበረከተ ባለው የጎላ አስተዋጽኦ የተነሳ በዘንድሮው ዓመት ብቻ በርካታ እውቅናዎችንና



**ፎቶ ከገፀ ድር**

**የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሰለሞን ዲባባ ለተቋሙ የተሰጠውን እውቅና ከአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ቡዜና አልከድር ሲቀበሉ**

ሽልማቶችን ማግኘት ችሏል። ከተለያዩ ተቋማት ጋር አብሮ ለመስራት የሁለትዮሽ ስምምነት ተፈራርሟል፡፡ ተቋሙ በሚዲያ ዘርፍ ያሳየው የፈጠራ ብቃት፣ ወቅታዊና ታማኝ መረጃዎችን ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ ጥረት እንዲሁም የከተማዋን በጎ ገፅታ በመገንባት ረገድ የተጫወተው ሚና በተለያዩ አካላት ከፍተኛ ምስጋናና አድናቆት እንዲቸረውም አድርጎታል።

ለአብነት፡- ባሳለፍነው ሐምሌ ወር በ2018 በጀት ዓመት አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የላቀ አፈጻጸም በማስመዝግቡ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እውቅና እንደተበረከተለት የሚታወስ ነው። እውቅናው የበጀት ዓመቱን እቅድ አፈጻጸም መሠረት በማድረግ በተካሄደው ከተማ አቀፍ ምዘና ሚዲያው ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገቡ የተበረከተ ነበር፡፡ በወቅቱ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሰለሞን ዲባባ የእውቅና ምስክር ወረቀቱን ከአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ መቀበላቸው ይታወሳል፡፡

ባሳለፍነው ሀሙስ እለት ደግሞ ሚዲያው በከተማዋ የተሰሩ ሁሉን አቀፍ ስራዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ላበረከተው አስተዋጽኦ ከአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት እውቅና ተሰጥቶታል። ኤ ኤም ኤን ባለፉት አምስት አመታት በከተማዋ የተመዘገቡ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስራዎች በህዝቡ ተደግፈው ስኬታማ እንዲሆኑ በሚዲያ አማራጮቹ በሰራቸው የይዘት ስራዎች ነው ምክር ቤቱ እውቅና የሰጠው። በወቅቱም የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ቡዜና አልከድር፤ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የህብረተሰቡ አቤቱታ ምላሽ እንዲያገኝ በማድረግ በኩል ትልቅ ሚና ተወጥቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰለሞን ዲባባ በበኩላቸው የተቋሙን እውቅና በተቀበሉበት ወቅት ሚዲያው በየጊዜው በይዘት፣ በፈጠራና በመረጃ ተደራሽነት እያሳየ ያለው ለውጥ የህዝቡን የለውጥና የመልማት ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ነው። የአሁኑ እውቅናም ለተሻለ ትጋት የሚያነሳሳውና ለቀጣይ የህዝቡን አዳጊ የልማት ፍላጎትና የመረጃ እርካታን ይበልጥ ለማላቅ ስንቅ የሚሆነው ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም ከሰሞኑ የአዲስ አበባ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በ2018 ተቋሙ በርካታ ስኬቶችን እንዲያስመዘግብ ላገዙት አካላት እውቅና ሰጥቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል የትውልድ ድምጽ የሆነው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በዜና፣ በምርመራ ዘገባዎቹ እንዲሁም በዋርካ፣ በጠረጴዛ እና በአገልጋይ ፕሮግራሞቹ አገልግሎቶችን ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ እና ብልሹ አሰራሮችን በማጋለጥ ላበረከተው አስተዋጽኦ እውቅና ተበርክቶለታል።

እነዚህን በማሳያነት ጠቀስን እንጂ ሚዲያው በበጀት ዓመቱ ሌሎች እውቅናዎችንና ሽልማቶችንም አግኝቷል። ለዚህ ውጤት የተቋሙ አመራሮችንና ባለሙያዎችን ጨምሮ የባለድርሻ አካላት የማያቋርጥ ጥረት አይተኬ ሚና አለው።

ሽልማቶቹ ደግሞ የመዲናዋን እድገትና ለውጥ በውጤታማነት ለማጉላት ትልቅ የሞራል ብርታትና መነቃቃትንም የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

በእርግጥም በዩኒቨርሲት ኦፍ ሚኒሶታ ገጸ-ድር ላይ የታተመውና "How to reward, recognize and encourage strong performance" የሚል ርእስ የተሰጠው ጥናታዊ ጹሁፍ እንደነዚህ አይነት እውቅናዎች ከገንዘብ ሽልማት በላይ የአንድን ተቋም አመራሮችንና ሰራተኞችን ለበለጠ ስራ ያነሳሳል በማለት ያብራራል፡፡ ለአንድ ተቋም ወይም ግለሰብ የምትሰራው ስራ ውጤት እያመጣ፣ ትልቅ ግብ እያሳካህ ነው ማለት ከሁሉም በላይ ለተሻለው ወጤትና ስራ መነሳሳትን ይፈጥራል በማለት ጥናቱ ያክላል፡፡

የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሰለሞን ዲባባም፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የህዝብ ልሳንነቱን በላቀ ጥራትና ይዘት አጠናክሮ እንደሚቀጥል የ2018 ዓ.ም በጀት ዓመት አፈፃፀምና የ2019 እቅድ ውይይት በተካሄደበትና የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ አመራሮችና ሰራተኞች የእውቅና መርሃ ግብር በተካሄደበት ወቅት ተናግረዋል፡፡

ተቋሙ ጥራት፣ ፈጠራና ፍጥነትን ባማከለ መልኩ በተለያዩ የይዘት አማራጮችና ቋንቋዎች በተለያዩ ቻናሎች የትውልድ ድምፅ በመሆን ስኬታማ ስራ እየሰራ መሆኑን የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሰለሞን ዲባባ በወቅቱ ገልፀዋል።

የከተማዋ ዋና የመረጃ ምንጭ የሆነው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የተቋሙን አሰራር፣ የይዘት ጥራት እና የቴክኖሎጂ አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር እና የከተማዋን እንቅስቃሴ በጥራት ለማድረስ ቴክኖሎጂዎችን ማሟላት ላይ በትኩረት እየሰራ ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

እንደ ዋርካና አገልጋዩ ያሉትን ፕሮግራሞች በመደገፍ ሀገራዊ መግባባትን የመገንባት ኃላፊነትን የሚወጡ ጥልቅና ተፅዕኖ ፈጣሪ የምርመራ ዘገባዎች ላይ ትኩረት እንደሚደረግ የገለጹት ዋና ስራ አስፈጻሚው፣ ተቋሙ በ2018 አፈፃፀሙ የይዘት ተደራሽነትን እና ጥራትን በማሳደግ ረገድ በበጀት ዓመቱ እንደ ከተማ የተሻለ አፈፃፀም ማስመዝገብ መቻሉን ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከአዲስ አበባ የለውጥና የዕድገት ጉዞ ጋር አብሮ የሚራመድ እና የወደፊት ርዕይን የሚያበስር ትልቅ የሚዲያ ተቋም ነው። ህብረተሰቡን እያዝናና የማስተማር፣ ታማኝ መረጃ ምንጭ የመሆንና የከተማዋን መልካም ገፅታ የመገንባት ጥረቱ ተጠናክሮ በመቀጠሉ፣ በመዲናዋ ሁለንተናዊ እድገት ላይ የሚያስመዘግበው አዎንታዊ አሻራ ወደፊትም ጎልቶ የሚታይ ይሆናል።

> **ሚዲያው በየጊዜው በይዘት፣ በፈጠራና በመረጃ ተደራሽነት እያሳየ ያለው ለውጥ የህዝቡን የለውጥና የመልማት ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ነው**

# የአዲስ ... ከገጽ 1 የዞረ

እንዳስቻላቸው አቶ ተማም ይናገራሉ፡፡

አቶ ሙስጠፋ አህመድ በአዲስ አበባ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ከአስር ዓመት በላይ በአሽከርካሪነት አገልግለዋል፡፡ ከፒያሳ እስከ ቦሌ አራብሳ ባለው መስመር የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ከጥቂት ዓመት በፊት በነበረው ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ መንገድ ላይ ቀላል የማይባል ሰዓት ያባክኑ እንደነበር በምሳሌ ያነሳሉ፡፡ “ለምሳሌ ከቦሌ አራብሳ መገናኛ ለመድረስ 72 ደቂቃ ይወስድብኝ ነበር፡፡ በኮሪደር ልማቱ መንገዱ እንዲሰፋ ተደርጎ ከተሰራ በኋላ ግን በ40 ደቂቃ መድረስ ችያለሁ። በኮሪደር ልማቱና በተለያዩ አካባቢዎች እየተገነቡ ያሉ ማስተንፈሻዎች የጉዞ ሰዓትን በማሳጠርና ምልልሱ ከፍ እንዲል በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና አላቸው” ብለዋል፡፡

በጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩት አቶ በኃይሉ በቀለ፤ ከመኖሪያ አካባቢያቸው ጃንሜዳ ተነስተው የሥራ ቦታቸው ወደሚገኝበት ዮሐንስ አካባቢ ሲመላለሱ በዋናነት ሳይክል እንደሚጠቀሙ ይናገራሉ። ቀደም ሲል በአካባቢው የነበረው መንገድ ለሳይክል ተጠቃሚዎች፣ ለአሽከርካሪዎችም ሆነ ለእግረኞች እንቅስቃሴ ምቹ አልነበረም። በተለይም የሳይክል መሄጃ መንገድ ባለመኖሩ ምክንያት፣ ጠባብ የነበረውን የተሽከርካሪ መንገድ አብሮ ለመጋራት ይገደዱ እንደነበር ይገልጻሉ።

በተጨማሪም መንገዶቹ ጥራት የሌላቸው፣ በተለይ በክረምት ወቅት ውሃ ያቁሩ ስለነበር እግረኞች ውሃ በተሽከርካሪ እንዳይረጩ ለማምለጥ በሚያደርጉት ጥረት ለተለያዩ አደጋዎች የሚጋለጡበት ሁኔታ እንደነበር ያነሳሉ። በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት የተሽከርካሪ፣ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች ተለይተው፣ ደረጃቸውን ጠብቀውና እጅግ ምቹ ሆነው በመሠራታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል።

ነሀሴ 12 ቀን 2018 ዓ.ም “ግሎባል ስታትስቲክስ ዋየር” የተሰኘ በኤክስ (ትዊተር) አህጉራዊና አለምአቀፋዊ መረጃዎችን፣ ደረጃዎችን እና ስታቲስቲክስን በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚያጋራ፣ ከ180 ሺህ በላይ ተከታዮች ያሉት የመረጃ ምንጭ ይፋ ባደረገው መረጃ፣ አዲስ አበባ ከአፍሪካ ከተሞች ምርጥ የመንገድ መሰረተ-ልማት ባለቤት ከሆኑ ቀዳሚ ከተሞች አንዷ ናት፡፡ በአፍሪካ የተሻለ እና ጥራት ያለው የከተማ መንገድ መሠረተ ልማት ካላቸው ከተሞች ከደቡብ አፍሪካዋ ኬፐታውን በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል፡፡

የዓለም ባንክ በገፀ ድሩ ያወጣው መረጃ እንደሚያሳየው፣ መንገድ ከቦታ ቦታ መሸጋገሪያ መረብ ብቻ ሳይሆን፣ የንግድ ፍሰትን በማቀላጠፍና ምርታማነትን ለማሳደግ ካለው ድርሻ አንፃር እንደ "ደም ዝውውር ስርአት" ተደርጎ የሚታይ መሠረተ-ልማት ነው። የአንድ ከተማ ስልጣኔና ዘመናዊነት ከሚለካባቸው መመዘኛዎች መካከል መንገድ ዋነኛው ነው።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በኮሪደር ልማቱ ዘመናዊነትን ከተላበሱ የከተማዋ መንገዶች በከፊል

የኢትዮጵያውያን መዲና፣ የአፍሪካ የፖለቲካና ዲፕሎማሲ ማዕከል፣ በዓለም ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችው አዲስ አበባ፤ ከዓመታት በፊት የነበራት መንገድ ካላት ድርብርብ ሚናና ኃላፊነት አኳያ የሚመጥናት አልነበረም፡፡ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ኢያሱ ሰለሞን ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፣ ቀደም ባሉት ዓመታት የነበራት የመንገድ ሽፋን በቂ ካለመሆኑ ባሻገር አንዱ መስመር ለረጅም ጊዜ ተሽከርካሪዎች የሚቆሙበት (ፓርክ የሚደረጉበት) ሆኖ ያገለግል ነበር። በተጨማሪም የእግረኛ መንገድ ሽፋኑ እጅግ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ፣ የነበሩት ጥቂት መንገዶችም በሕገ-ወጥ የጎዳና ላይ ንግድና በተለያዩ ያልተገቡ እንቅስቃሴዎች የተያዙ በመሆናቸው ለሕዝብ እንቅስቃሴ አመቺ አልነበሩም፡፡ በዚህም ምክንያት በከተማዋ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ይስተዋል ነበር፡፡

ባለፉት ዓመታት የከተማዋን የመንገድ ሽፋንና ጥራት ለማሳደግ ሰፋፊ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በኮሪደር ልማት የተካሄደውን ሳያካትት በመደበኛው የመንገድ ግንባታ ዕቅድ በ2014 ዓ.ም 205 ነጥብ 7፣ በ2015 ዓ.ም 190 ነጥብ 5፣ በ2016 ዓ.ም 336 ነጥብ 3፣ በ2017 ዓ.ም 370 ነጥብ 5 እና 2018 ዓ.ም 258 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር በድምሩ ከ1 ሺ 361 ኪሎ ሜትር በላይ በተለያየ ደረጃ የሚገኝ (የአስፋልት፣ የኮብል፣ የጠጠርና የእግረኛ መንገድን ጨምሮ) የመንገድ መሰረተ ልማት መገንባቱን አቶ ኢያሱ ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ከተገነቡ አዳዲስና ነባር የመንገድ መሠረተ-ልማቶች መካከል፡ - የቃሊቲ ቱሉ- ዲምቱ፣ ቃሊቲ-ቂሊንጦ፣ ቦሌ ኤርፖርት- ጎሮ፣ አሌክሳንደር ፑሽኪን - ቄራ - ጎተራ መንገድ፣ ሠላም ጎዳና፣ ሽሮሜዳ - ቁስቋም - እንጦጦ፣ ሽሮሜዳ - ኪዳነምህረት፣ሃጫሉ ጎዳና ተጠቃሾች ናቸው። ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት ባላቸው የከተማዋ ዋና ዋና የመንገድ መጋጠሚያ ሥፍራዎች ላይ በቁጥር 7 ግዙፍ የትራፊክ ማሳለጫ ተሸጋጋሪ ድልድዮች ተገንብተው ለአገልግሎት በቅተዋል።

አዲስ አበባ ዘመናዊና ምቹ መንገድ እንዲኖራት፣ የመንገድ ሽፋኑን በማሳደግ ረገድ የኮሪደር ልማቱ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ ኢያሱ እንደገለፁት፣ በሁለት ምዕራፍ ተከፍሎ የተከናወነው የኮሪደር ልማት፤ የከተማዋን ታዋቂ እና ነባር አካባቢዎችን የሸፈነ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ አምስት፤ በሁለተኛ ምዕራፍ ዘጠኝ በድምሩ 14 የመንገድ ኮሪደሮች ለምተዋል። በአጠቃላይ ከተማዋ አሁን ያላት የመንገድ መሰረተ ልማት ከ8 ሺህ 227 ኪሎ ሜትር በላይ ደርሷል።

የመንገድ ግንባታው የከተማ አስተዳደሩ አስፈፃሚ እና የመሠረተ-ልማት አቅራቢ ተቋማት (የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን፣ የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፣ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ኢትዮቴሌኮምና መሰል ተቋማት) ቅንጅታዊ አሰራር ጎልቶ የታየበት ነው፡፡ የኮሪደር ልማቱ ከአረንጓዴ ሥፍራና የህዝብ መዝናኛ የተለያዩ ይዘቶች ጋር ተሳስሮ እንዲፈፀም መደረጉ፣ ከተማዋ አዲስና ውብ ገጽታ እንድትላበስ ማስቻሉን አቶ ኢያሱ ያስረዳሉ፡፡

አዲስ አበባ በአሁኑ ወቅት የከተማዋን ገጽታ የቀየሩ፣ የተሳለጠ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር ያስቻሉ ዘመናዊና ደረጃቸውን የጠበቁ ሰፋፊ የመንገድ መሠረተ ልማቶች ባለቤት ሆናለች። የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከአስር ወር በፊት ከሳር ቤት፣ ጀርመን አደባባይ፣ ጋርመንት እስከ ፉሪ አደባባይ የተከናወነው የኮሪደር ልማት መጠናቀቅን አስመልክቶ ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ በኮሪደር ልማቱ የተሽከርካሪ መንገዶች ሰፍተው መገንባታቸውን ገልጸዋል። ለምሳሌ፣ ከኃይሌ ጋርመንት እስከ ጀርመን አደባባይ ባሉት ሁለቱም አቅጣጫዎች መንገዱ እንዲሰፋ ተደርጓል። በግንባታው ደረጃቸውን የጠበቁ እና የተለያዩ አገልግሎቶችን አካትተው የተሰሩ ሰፊ የእግረኛ መንገዶች ተገንብተዋል። ከመንገዱ ጋር ተያይዞ መሸጫ ሱቆች፣ ዘመናዊ መጸዳጃ ቤቶች፣ የህፃናት መጫወቻ ስፍራዎች እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች ተሟልተዋል፡፡ ከተማን ከተማ የሚያሰኙ እንደ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች እና የመብራት ገመዶች ያሉ መሠረተ ልማቶች ከመሬት በታች እንዲቀመጡና ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ ተደርጓል።

### የመንገድ መስፋፋትና ፋይዳው

በከተማዋ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ምቹና ዘመናዊ መንገዶች መገንባታቸው ፋይዳው ዘርፈ ብዙ እንደሆነ አቶ ኢያሱ ያስረዳሉ። አንደኛ የትራንስፖርት እንቅስቃሴው የተሳለጠ እንዲሆን እያደረገ ነው፡፡ ቀደም ሲል የመንገድ መሰረተ-ልማት ባልተካሄደባቸው አካባቢዎች ጭምር አዳዲስ መንገዶች ተከፍተዋል። ነባር መንገዶችም ደረጃቸው ተሻሽሎና የጎን ስፋታቸው እንዲጨምር ተደርጎ የተገነቡ ከመሆኑም ባሻገር በቂ የህዝብ ማመላለሻ ተርሚናሎች፣ የታክሲ ማውረጃና መጫኛ ቦታዎች እንዲሁም የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በመገንባታቸው የተቀላጠፈ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ለአብነት የቃሊቲ-ቱሉ ዲምቱ መንገድ ነባር ከሚባሉ መንገዶች አንዱ ሲሆን ጠባብና ነባራዊ የትራፊክ እንቅስቃሴ መሸከም የሚችል አልነበረም፡፡ መንገዱ 50 ሜትር የጎን ስፋት፣ የመንገድ አካፋይ፣ የእግረኛና ብስክሌት መንገድ አካትቶ በዘመናዊ መልኩ እንዲገነባ ተደርጓል፡፡

የቃሊቲ-ቂሊንጦ መንገድንም ከዚህ ቀደም ያልነበረ ባለፉት አምስት ዓመታት ከተሰሩ ጉልህ ፋይዳ ያላቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ይህ መንገድ ከመሰራቱ በፊት የኮዬ ፈጬ ነዋሪዎች ወደ መሀል ከተማ ለመምጣት በጎሮ አሊያም በጋርመንት መዞር ይጠበቅባቸው ነበር። መንገዱ ቀድሞ የተጀመረ ቢሆንም ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ 10 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ርዝመትና እስከ 60 ሜትር የጎን ስፋት ያለው መሆኑን አቶ ኢያሱ ገልጸዋል፡፡

ሌላው ፋይዳው የከተማዋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲነቃቃ ማድረጉ ነው። መንገዶች ሲሻሻሉ የንግድ እና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ይጨምራሉ። ሸቀጦች እና አገልግሎቶች በፍጥነት ወደ ገበያ ስለሚደርሱ የከተማዋ ኢኮኖሚ እንዲነቃቃ እያደረገ ነው። ከዚህ በተጨማሪ መንገዶቹ ለከተማ ውበት እና ዘመናዊነት ማደግ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ኢያሱ እንደሚያስረዱት፣ ዘመናዊ የተሽከርካሪና የእግረኛ መንገዶች፣ የመንገድ መብራት ስርዓቶች እና አረንጓዴ ልማቶች የከተማዋን ገጽታ አሻሽለውታል፤ ከተማዋንም ለነዋሪዎችና ለጎብኚዎች ይበልጥ ማራኪ አድርገዋታል፡፡

በኮሪደር እሳቤ እየተከናወነ የሚገኘው የመንገድ ግንባታ፤ ከተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ባሻገር የሞተር አልባ ትራንስፖርት መስመሮችን አካትቶ እየተገነባ ያለና ዘመናዊ የትራፊክ ምልክቶችን ያካተተ በመሆኑ የትራፊክ አደጋ እንዲቀንስ እያገዙ መሆኑን አቶ ኢያሱ ይገልጻሉ፡፡ ቀደም ሲል ዳር የነበሩ አካባቢዎች ከዋና የከተማ ማዕከላት ጋር በቀላሉ ተገናኝተዋል፤ ይህም ለነዋሪዎች የአገልግሎት ተደራሽነትን አሳድጓል። አዲስ አበባ በመሠረተ ልማት በአፍሪካ እና በዓለም ተወዳዳሪ እንድትሆን እያደረገ ነው፡፡ ቱሪዝም፣ ኢንቨስትመንት እና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች እንዲጨምር አድርጓል፡፡

የኮሪደር ልማቱ የመንገድ መሰረተ ልማትን ወደተሻለ ደረጃ ከፍ ማድረጉን ያብራሩት አቶ ኢያሱ፣ ከዚህም በላይ አዲስ አበባ አዲስ ገፅታ እንድትላበስ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተመራጭ ከተማ እንድትሆን የመንገድ ዘርፉ ጉልህ ሚና እያበረከተ ይገኛል። በዚህም ከተማዋ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ አካታች የመንገድ መሠረተ-ልማት ባለቤት እንድትሆን ታቅዶ እየተሰራ ነው። በቀጣይም በኮሪደር ልማት ሂደት የተገኙ ጠቃሚ ልምድና የቅንጅታዊ አሠራር ተሞክሮዎችን በማስፋፋት የተሻለ የመንገድ መሠረተ-ልማት በሁሉም የከተማዋ ክፍሎች ለማዳረስ እንደሚሰራ አብራርተዋል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም

# የቀዳማይ ልጅነት ልማት ለሀገራዊ እድሳት

## ክፍል ሁለት



**በአሌክስ ብርሀኑ (የሰላምና ደህንነት መምህር እና ተመራማሪ)**

ኢሜል፡- alexbirhanu81@gmail .com

ውድ አንባቢዎቻችን፤ ባለፈው የክፍል አንድ እትማችን በዋናው ርዕስ ስር በሰው ልማት ላይ የተመሰረተ አዲስ የሀገር ግንባታ አቅጣጫ እና የቀዳማይ ልጅነት ኢንቨስትመንት ሳይንታዊ መሰረት፡- የሰው አቅምን ከመጀመሪያው ጀምሮ መገንባት በሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የጻሃፊውን ሰፊ ትንታኔ አስነብበናችኋል። የጽሁፉን ቀጣይ ክፍል እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፤ መልካም ንባብ!

### የአዲስ አበባ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ተነሳሽነት

የአዲስ አበባ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ተነሳሽነት ያለው ዋና ጠቀሜታ መንግሥታት የልማት ችግሮችን የሚያዩበትንና የሚፈቱበትን መንገድ ለመለወጥ በመሞከሩ ላይ ይመሠረታል። በተለምዶ ብዙ የመንግሥት አሠራሮች ችግሮች ከተፈጠሩ በኋላ ምላሽ በመስጠት ላይ ያተኩራሉ። ለምሳሌ፡- ወጣቶች በቂ ክህሎት ሳይኖራቸው ከትምህርት ሲወጡ የሥራ አጥነትን ለመፍታት መሞከር፣ ሕፃናት በትምህርታቸው ደከም ካሉ በኋላ የትምህርት እኩልነት ችግርን ለመቀነስ መሞከር፣ ወይም ማህበራዊ ችግሮች ከተጠናከሩ በኋላ ለመቆጣጠር መጣር ብዙ ጊዜ የሚታዩ አቀራረቦች ናቸው።

ነገር ግን የአዲስ አበባ አቀራረብ ከዚህ የተለየ የልማት ፍልስፍና ያሳያል። ይህም ችግሮች ከመከሰታቸውና ከመባባሳቸው በፊት መነሻ ምክንያቶቻቸውን በመለየት ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል የቅድመ ጣልቃ ገብነት (preventive approach) ሞዴል ነው። ይህ አስተሳሰብ ብዙ የማህበረሰብ ችግሮች በመጀመሪያ ደረጃቸው ላይ ተገቢ ድጋፍ ቢያገኙ እና መሠረታቸው ላይ ቢሠራ መፍትሔ ማምጣት እንደሚቻል ይገነዘባል።

የቀዳማይ ልጅነት ልማት በዚህ አውድ አንዱ የተለያዩ ዘርፎችን የሚያገናኝ የተቀናጀ የልማት ስርዓት ለመፍጠር ያለመ ነው። ይህም የሕፃናት ጤና፣ አመጋገብ፣ ቅድመ ትምህርት፣ የወላጅ ድጋፍ፣ የሕፃናት ጥበቃ እና ለእነሱ ተስማሚ የሆነ የከተማ ልማትን በአንድ ላይ የሚያስተሳስር አቀራረብ ነው። ይህ አቀራረብ በዓለም አቀፍ የሕፃናት ልማት ጥናቶች የተደገፈ መሠረታዊ ግንዛቤን ያንፀባርቃል፤ ይኸውም አንድ ሕፃን የሚያድገው በአንድ ዘርፍ ብቻ አይደለም።

የአንድ ሕፃን የወደፊት ሕይወት በብዙ ተያያዥ ሁኔታዎች ይቀረፃል። እነዚህም የቤተሰብ ሁኔታ፣ የሚኖርበት ማህበረሰብ አካባቢ፣ የጤና ሁኔታ፣ የመማር ዕድል፣ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት እና የሚያገኘውን የስሜታዊና ማህበራዊ ድጋፍ ያካትታል። ስለዚህ የቀዳማይ ልጅነት ልማት የትምህርት ዘርፍ ብቻ ኃላፊነት ሳይሆን፣ የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት፣ ቤተሰቦች፣ ማህበረሰቦች እና መላው ህብረተሰብ በጋራ የሚሸከሙት ሀገራዊ ኃላፊነት መሆኑን ያሳያል።

ይህ የተቀናጀ አቀራረብ ቅድመ ትምህርትን እንደ የትምህርት ዘርፍ ብቻ የማየት የተለመደ አስተሳሰብን የሚለውጥ ነው። ይልቁንም ሕፃናትን መገንባት ማለት የወደፊት ሀገርን መገንባት መሆኑን ያስቀምጣል። በዚህ መልኩ የአዲስ አበባ የቀዳማይ ልጅነት ተነሳሽነት ከአጭር ጊዜ የችግር ምላሽ ወደ ረጅም ጊዜ የሰው አቅም ግንባታና ሀገራዊ ልማት እይታ የተሸጋገረ የስትራቴጂያዊ አመራር ምሳሌ ሆኖ ይታያል። በአጠቃላይ፣ ሕፃናትን ቀድሞ መደገፍ የዛሬ ችግሮችን ለመቆጣጠር ብቻ ሳይሆን፣ የነገ ችግሮችን ለመከላከልና የተሻለ ሀገር ለመገንባት የሚደረግ ስትራቴጂያዊ የሰው ኃይል ኢንቨስትመንት ነው።

### የቀዳማይ ልጅነት ልማትና የኢትዮጵያ የአዎንታዊ ሰላም ፍለጋ

በአዲስ አበባ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ተነሳሽነት ውስጥ ካሉት እጅግ ጠቃሚ ገጽታዎች አንዱ ከ"አዎንታዊ ሰላም" (Positive Peace) ጽንሰ ሀሳብ ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ብዙ ጊዜ ሰላም የሚታየው ጦርነት ወይም የትጥቅ ግጭት ካለመኖሩ ጋር ብቻ ነው። ነገር ግን የሰላም ጥናት ምሁራን በተለይም የኖርዌይ ምሁር ዮሃን ጋልቱንግ (Johan Galtung) እንደሚያስረዱት፣ እውነተኛና ዘላቂ ሰላም የሚገኘው ግጭት በመጥፋቱ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች በክብር፣ በደህንነት፣ በእኩል ዕድል እና በመከባበር እንዲኖሩ የሚያስችሉ ማህበራዊ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ነው።

ከዚህ አንፃር በቀዳማይ ልጅነት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት የአዎንታዊ ሰላም መሠረተ ልማት አካል ሆኖ ሊታይ ይችላል። ምክንያቱም አንድ ማህበረሰብ የበለጠ ሰላማዊ የሚሆነው የማግለል ሁኔታዎች ሲቀንሱ፣ ዜጎችም ተፈጥሯዊ አቅማቸውን ለማዳበር በቂ ዕድል ሲያገኙ ነው። ድህነት፣ የማህበራዊ እኩልነት እጦት፣ የትምህርት እድል ውስንነት፣ የጤና ችግሮች እና ማህበራዊ መገለል ለረጅም ጊዜ የማህበረሰብ ደካማነትን ሊፈጥሩ የሚችሉ መዋቅራዊ ምክንያቶች ናቸው።

የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራሞች በእነዚህ መሠረታዊ ችግሮች ላይ በመሥራት ለማህበረሰብ መረጋጋት ስጋት የሆኑ ችግሮች ለመቀነስ ያግዛል። ይህ ማለት ግን የቀዳማይ ልጅነት ልማት ብቻውን የፖለቲካ ግጭቶችን ሊፈታ ወይም አስፈላጊ የመንግሥት ማሻሻያዎችን ሊተካ ይችላል ማለት አይደለም። ይልቁንም ዘላቂ ሰላም የሚገነባው የዛሬ ግጭቶችን በአግባቡ በመቆጣጠር እና ሰላማዊ ማህበረሰብ እንዲፈጠር የሚያስችል የሰው ልማት መሠረቶችን በረጅም ጊዜ በመገንባት ነው።

### ሕፃናት የሀገራዊ ጽናት መሠረት

በዓለም ዙሪያ በርካታ ጥናቶች የሕፃናት እድገትና የሀገራዊ ጽናት (National Resilience) በጥልቅ እንደሚገናኙ ያሳያሉ። ጽኑ ማህበረሰብ የሚገነባው በጠንካራ ተቋማት ብቻ አይደለም፤ አቅም ያላቸው፣ በኃላፊነት የሚሳተፉ እና ማህበራዊ እሴቶችን የሚያከብሩ ዜጎች ግንባታም ያስፈልጋል።

በቂ ድጋፍ አግኝተው የሚያድጉ ሕፃናት በተለምዶ፡- በራስ መተማመንና የስሜት መረጋጋት፣ የመግባባትና የመተባበር ችሎታ፣ ችግር የመፍታት አቅም፣ ትላልቅ ሰዎች ክብርና መቻቻል፣ በማህበረሰብ ውስጥ ገንቢ ተሳትፎ የማድረግ ችሎታ የመሳሰሉ ባህሪያትን ያዳብራሉ።

እነዚህ ባህሪያት ለግለሰብ ስኬት ብቻ ሳይሆን፣ ለዲሞክራሲያዊ ዜግነት፣ ለማህበራዊ አንድነት፣ እና ለሰላማዊ አብሮነት መሠረታዊ ናቸው። በዚህ መልኩ በቀዳማይ ልጅነት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ የወደፊት ማህበራዊ ስሪት (social fabric) ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ነው። ጤናማ፣ የተማረ እና ከማህበረሰቡ ጋር የተሳሰረ ትውልድ የሀገር ክፍፍሎችን ለመቀነስ፣ በኢኮኖሚ ለመሳተፍ እና ለሀገራዊ ልማት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ለማበርከት የተሻለ አቅም ይኖረዋል።

### የረጅም ጊዜ የልማት ትውስታ

የከንቲባ አዳነች አቤቤ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ተነሳሽነት መገምገም ያለበት በአሁኑ ጊዜ በሚታዩ ውጤቶች ብቻ ሳይሆን፣ በያዘው ሰፊ የልማት ርዕይ ነው። ይህ ተነሳሽነት አንድ መሪ ኃላፊነት የሚወስደው የዛሬን ችግር ለመፍታት ብቻ ሳይሆን፣ ማህበረሰብን ለነገ ፈተናዎች ለማዘጋጀት መሆኑን ያሳያል። ብዙ የመንግሥት ፕሮግራሞች የሚመዘኑት በአጭር ጊዜ ውጤት ምክንያት ነው። ነገር ግን የቀዳማይ ልጅነት ልማት የተለየ አስተሳሰብ ይፈልጋል፤ ምክንያቱም ትልቁ ጥቅም የሚታየው ከዓመታት እና ከአሥርት ዓመታት በኋላ ነው።

የዚህ ተነሳሽነት እውነተኛ ውጤት በሚመጡት ዘመናት የሚለካው፡- ለትምህርት በተሻለ ዝግጅት የሚገቡ ሕፃናት፣ በሚመዘገበው ውጤት፣ ጤናማና ብቃት ያላቸው የወደፊት ሠራተኞች፣ ጠንካራ ቤተሰቦች፣ የእኩልነት እጦትን በመቀነስ፣ በጠነከረ ማህበራዊ አንድነት ነው። በቀጣይነት ከተደገፈና በጥራት ከተተገበረ፣ የአዲስ አበባ የቀዳማይ ልጅነት ኢንቨስትመንት ለኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የሰው ልማት ታላቅ አስተዋፅኦ ከሚያበረክቱ ተግባራት አንዱ ሊሆን ይችላል።

### ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ትልቁ ተግዳሮት የዛሬን ቀውስ መቆጣጠር ብቻ አይደለም፤ የነገን ቀውስ ከመነሻው መከላከል ጭምር እንጂ። ይህም ከወቅታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጫናዎች በላይ የሆነ የሀገራዊ ልማት ርዕይ ይፈልጋል። የአዲስ አበባ የቀዳማይ ልጅነት ተነሳሽነት ይህንን ርዕይ ያንፀባርቃል። ሀገር ግንባታ ዜጎች ወደ ፖለቲካ ሕይወት ከገቡ በኋላ ብቻ እንደማይጀምር ያሳያል። የሚጀምረው ከጤናማ እርግዝና፣ ከተጠበቀ ቤተሰብ፣ ከተደጋጋፊ ማህበረሰብ፣ ጥራት ካለው የመማሪያ አካባቢ እና ሕፃናት ሙሉ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ከሚሰጣቸው ዕድል ነው።

ድልድይ ሁለት ቦታዎችን ያገናኛል፤ መንገድ ገበያዎችን ያገናኛል፤ ነገር ግን ብቃት ያለው፣ በራሱ የሚተማመን እና ማህበራዊ ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ የአንድ ሀገርን ያለፈ ታሪክ ከወደፊቱ ያገናኛል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፈንታ በሚረከበው ትውልድ ላይ የሚመሠረት ከሆነ፣ በሕፃናት ላይ መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ ሁለተኛ ደረጃ ጉዳይ አይሆንም። አንድ ሀገር ልትሠራው ከምትችላቸው በጣም ስትራቴጂያዊ ኢንቨስትመንቶች አንዱ ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያ የወደፊት መሠረት ዛሬ እየተገነባ ነው፤ ከቀዳማይ ልጅነት ጀምሮ።




ፎቶ- ከፋይል
ህፃናት ላይ መስራት ለሀገር ግንባታው አይተኬ ሚና ይጫወታል

ኢኮኖሚ

# መዳረሻዎችን የማስተዋወቁ ስራ ምን ውጤት እያመጣ ነው?



ፎቶ ከገፀ ድር
ከአዲስ አበባ የቱሪስት መዳረሻዎች በከፊል

በለይላ መሐመድ

አዲስ አበባ በተፈጥሮ፣ በታሪክ እና በባህል ሀብቶች የታደለች ከተማ ናት። ኢትዮጵያን የሰው ዘር መገኛ ካሰኘችው ድንቅነሽ ወይም ሉሲ ከሚገኝበት ብሔራዊ ሙዚየም አንስቶ እስከ እንጦጦ፣ አንድነት እና አራዳ ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ እና የሳይንስ ሙዚየምን አካትቶ በመዲናዋ የሚገኙ አዳዲስ እና ነባር መስህቦች ከተማዋን በጎብኚዎች ተመራጭ እያደረጓት ይገኛሉ። በቅርብ ዓመታት በኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት የተከናወኑ ስራዎች ከቱሪስት መሸጋገሪያነት ወደ መዳረሻነት በማሸጋገር ረገድ አይተኬ ሚና አላቸው፡፡

እነዚህን የከተማዋን የቱሪዝም መስህቦች በአግባቡ እና በዘመናዊ መልኩ ማስተዋወቅ ለከተማዋ መልካም ገጽታ ግንባታ፣ ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በኢትዮጵያ የወራት አቆጣጠር ከመስከረም አዲስ ዓመት ጀምሮ፣ እንደ መስቀል እና ኢሬቻ ያሉ የአደባባይ በዓላት በድምቀት የሚከበሩ በመሆኑ በርካታ ቱሪስቶች ወደ ሀገር ቤት ይመጣሉ፡፡

ከሳምንታት በኋላ የሚከበሩትን እነዚህን በዓላት አስመልክቶ ጎብኚዎች ወደ ከተማዋ በስፋት እንዲመጡና መስህቦቹ በአግባቡ እንዲተዋወቁ በማድረግ ረገድ እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቱሪዝም ኮሚሽን የቱሪዝም ዲጂታል ግብይትና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍረሂወት ገብረ መድህንን አነጋግረናቸዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ ኮሚሽኑ የተቋቋመበት አንደኛው ዓላማ ከተማዋ ካለችበት ፈጣን ዕድገት አንጻር በውስጧ የሚገኙ የቱሪዝም መስህቦችን እና መዳረሻዎችን ለቱሪስቶች ማስተዋወቅ ነው። በተጨማሪም በከተማዋ የሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶችን የመሸጥ ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡ በዚህ መነሻነት ባሳለፍነው በጀት ዓመት ከተማዋ ምን ምን ሀብቶች እንዳሏት ትኩረት ተደርጎ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከኢንቨስትመንት፣ ከቱሪዝም መዳረሻዎች፣ ከኮንፈረንስ ቱሪዝም (ማይስ ቱሪዝም)፣ አገልግሎቶች... አንጻር ምን አቅም እንዳላት መረጃ በስፋት ተደራሽ ተደርጓል፡፡ ባለፉት ጊዜያት አዲስ አበባ ያላትን የቱሪስት መስህቦች ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ሀገር ቱሪስቶች በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዘ የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ለዚህም "Visit Addis Ababa" የተሰኙ ይፋዊ የከተማ ማስተዋወቂያ እና መተግበሪያ ገጸ ድሮች ተዘጋጅተዋል።

የሀገር ውስጡንና ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡን ተደራሽ የሚያደርጉ እንደ ፌስቡክ፣ ቲክቶክ፣ ኢንስታግራም፣ ሊንክደን፣ ዩቱዩብ ያሉ ገጾችን በመክፈት በየመዳረሻዎቹ በመሄድ በየጊዜው የሚከናወኑ ተግባራትን ለበርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች የማስተዋወቅ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በሚዲያዎችም መስህቦቹን የሚያስተዋውቁ አጫጭር ማስታወቂያዎች፣ ዘጋቢ ፊልሞች እና ዶክመንተሪዎች ተሰርተው እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለትምህርት፣ ለኮንፈረንስ፣ ለቢዝነስ እና ለጉብኝት የሚመጡ እንግዶችን ከመጡበት ዓላማ ጎን ለጎን ከተማዋን የማስጎብኘትና የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ ነው፤ ይህም ወደፊት ቤተሰቦቻቸውን ይዘው እንዲመለሱና ለሌሎች አምባሳደር ሆነው እንዲያስተዋውቁ ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ወይዘሮ ፍረሂወት ይናገራሉ፡፡

እንደ አይሾው ስፒድ እና ዲላንፔጅ ያሉትን ጨምሮ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን በመጋበዝ በዲጂታል ሚዲያ አማካኝነት ሰፊ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ በእነዚህ እንግዶች አማካኝነት የከተማዋን ውበት፣ ደህንነት፣ እንግዳ ተቀባይነት እና እያንዳንዱን የቱሪዝም ሀብት በቀጥታ ስርጭት ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲተዋወቅ ተደርጓል። በዚህም የማህበራዊ ሚዲያ ተከታዮቻቸውን ጨምሮ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የከተማዋን የቱሪዝም ሀብቶች ብቻ ሳይሆን፣ ባህላዊ እሴቶቹንም ጭምር እንዲያውቃቸው ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማነቃቃት ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስትና የግል ተቋማት ሰራተኞች እንዲሁም በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ዜጎች አዳዲሶቹን ፓርኮች በልዩ ቅናሽ እንዲጎበኙ በማድረግ ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ ተሠርቷል።

## ምን ውጤት እየተገኘ ነው?

ወይዘሮ ፍረሂወት እንደሚገልፁት፣ የቱሪዝም መስህብና መዳረሻዎችን የማስተዋወቅ ስራው ላይ ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ ተጨባጭ ለውጦች መጥተዋል፡፡ የጎብኚዎች የቆይታ ጊዜ እንዲጨምር አድርጓል፡፡ ከዚህ ቀደም የውጭ ሀገር ቱሪስቶች አዲስ አበባን የሚጠቀሙት ለመሸጋገሪያነት ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ያሉትን በርካታ ፓርኮች እና ታሪካዊ ቦታዎች ለመጎብኘት ሲሉ ብቻ ቆይታቸውን የሚያራዝሙባቸው አጋጣሚዎች ተፈጥረዋል።

ከዚህ በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ባህል እያደገ መጥቷል፡፡ ቀደም ሲል 'ቱሪዝም ለውጭ ሀገር ዜጎች ብቻ ነው' የሚለው አስተሳሰብ አሁን ላይ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። በየቀኑ ማታ ማታ በተለይ ደግሞ ቅዳሜና እሁድ በርካታ ቤተሰቦች በዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ በአንድነትና እንጦጦ ፓርኮች፣ በወዳጅነት አደባበይ... በመገኘት የመዝናናት ባህላቸውን አሳድገዋል። ይህ ለከተማዋ አዲስ ማህበራዊ ድባብ ፈጥሯል። የቱሪስቶች ቆይታ በመጨመሩ ምክንያት ሆቴሎች፣ ባህላዊ ምግብ ቤቶች፣ አስጎብኚዎች እና የከተማ ታክሲዎች ገቢያቸው እያደገ መጥቷል።

ሌላው ከተማዋ ለማይስ ወይም ለስብሰባ ቱሪዝም ተመራጭ ማዕከል እየሆነች እንድትመጣ አድርጓታል፡፡ አዲስ አበባ እንደስሟ አዲስ እና ውብ እንዲሁም ምቹ እየሆነች በመምጣቷ በርካታ ሀገር፣ አህጉር እና ዓለም አቀፍ ትላልቅ ስብሰባዎች እንድታካሂድ ዕድል ፈጥሯል። ከጥቂት ዓመታት በፊት በከተማዋ ይካሄዱ የነበሩ ኹነቶች ውስን ነበሩ፤ በየዓመቱ የሚካሄደው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤን ነበር የምታስተናግደው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶ ከተሰራ ወዲህ ግን የሚካሄዱ ስብሰባዎች ቁጥር እያደገ መጥቷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት አዲስ አበባ 150 አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን አስተናግዳለች፡፡ ባሳለፍነው በጀት ዓመት ደግሞ ከ221 በላይ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን ማስተናገድ ችላለች፡፡

ለስብሰባ የሚመጡ እንግዶች የከተማዋን መስህቦች በመጎብኘታቸው ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት እድል ፈጥሯል። ከዚህ አንጻር በ2018 በጀት ዓመት የቱሪስት ቁጥር ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ብልጫ አለው፡፡ ለምሳሌ በ2017 በጀት ዓመት አንድ ሚሊየን የውጭ ሀገር ቱሪስት ከተማዋን ጎብኟታል፡፡ በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ 1 ነጥብ 3 ሚሊየን ቱሪስቶች ጎብኝተዋል፡፡ በቱሪዝም ዘርፉ የታየው ለውጥ በቱሪስት ፍሰቱ ብቻም ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ ለውጥም አምጥቷል፡፡ በዚህም 2017 በጀት ዓመት 143 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር ገቢ የተገኘ ሲሆን 2018 ላይ ደግሞ 242 ነጥብ 6 ቢሊየን ብር ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ መሆኑን ወ/ሮ ፍረሂወት ያነሳሉ፡፡

ዳይሬክተሯ እንደሚገልፁት፤ መጭው ጊዜ በተለይም መስከረም እና ጥቅምት ለኢትዮጵያ ቱሪዝሙ ዘርፍ ልዩ ትርጉም አላቸው። ክረምቱ አልፎ መሬቷ በአረንጓዴና በአደይ አበባ በምትሸለምበት በዚህ ወቅት ተከታታይ እንደ አዲስ ዓመት፣ መስቀል፣ ኢሬቻ ያሉ ትላልቅ ሀይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት ይከበራሉ። በዚህም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንም ቤተሰቦቻቸውንና ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ሀገር ቤት ይመጣሉ፡፡ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች የሚኖሩበት ሀገር አየር ሙቀታማ ከመሆን ጋር ተያይዞ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡበት ወቅትም ነው፡፡

ከዚህ ቀደም ቱሪስቶች ከአዲስ ዓመት ጀምሮ የሚከበሩ በዓላትን ለመታደም ሲመጡ አዲስ አበባ የምታገለግለው እንደ መሸጋገሪያ ብቻ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ከተማዋ የራሷን የጎብኚ ድርሻ እንድታገኝ እና የቱሪስቶችን ቆይታ ለማራዘም በርካታ አዳዲስና ስትራቴጂካዊ የማስተዋወቅ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ ዳይሬክተሯ ያነሳሉ።

በዓላት እሴቶቻቸውን ጠብቀው እንዲተዋወቁ ከባህልና ከሞራላዊ እሴት ባለፈ እንደ አንድ የቱሪዝም ምርት ተቀርጸው እንዲቀርቡ እየተሰራ ይገኛል። ለዚህም በዓላትን በቱሪዝም ፓኬጆች ውስጥ በማካተት "በዚህ ቀን እንዲህ ዓይነት በዓል አለ" በሚል አቀራረብ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ የማስተዋወቅ ሥራ ይከናወናል። በተለይም ዓለም አቀፍ ተቋማትን በመለየት የሀገራችንን ባህል ትክክለኛ ገጽታ የሚያሳዩ መልዕክቶችን፣ "እንኳን አደረሳችሁ" የሚሉ የበዓል ካርዶችን እና የተለያዩ ባህላዊ ስጦታዎችን በማዘጋጀት ተደራሽ የማድረግ ስራ በልዩ ትኩረት እየተሰራበት ይገኛል።

ጊዜውን የሚመጥን የማስታወቂያ ስራዎች መስራት ስለሚገባ ጎብኚዎች በከተማዋ ስላሉ የቱሪስት መስህቦችና መዳረሻዎች፣ ሆቴሎች፣ የባህል ስፍራዎችና የበዓላት ሁነቶች ሙሉ መረጃ የመፍጠር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ የጉብኝት ሰዓቶችን እንዲሁም ወደ ሀገር ቤት መምጣት ለማይችሉ ወይም አስቀድመው እቅድ ለሚያወጡ የውጭ ጎብኚዎች፣ ዲያስፖራዎች... እንደ አንድነት ፓርክ፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያና ብሔራዊ ሙዚየም ያሉ ቦታዎችን በዲጂታል አማራጭ በበይነ-መረብ ቀድመው እንዲጎበኙ የሚያስችሉ የሞባይል፣ የ3D እና የቨርቹዋል (ጎብኚዎች ከተቀመጡበት ቦታ ሳይነሱ በከተማዋ የሚገኙ ሙዚየሞችን፣ ታሪካዊ ቦታዎችን ወይም የቱሪስት መስህቦችን እንዲጎበኙ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የኪነ ጥበብ ድግሶች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የእውቅና መርሃ ግብር፣ የንባብ አውደ ርእይ፣ የኪነ ጥበብ ሙያዊ ውይይት እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል።



ፎቶ- ከገፀ ድር
ከመዲናዋ የጥበብ መሰናዶዎች በከፊል

## የንባብ አውደ ርእይ

14ኛው ከተማ አቀፍ የንባብ ፌስቲቫል ሳምንት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ "ከስክሪን ቀንሰን መጽሐፍትን እንግለጥ" በሚል መሪ ሀሳብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ ያዘጋጀው ይህ መርሃ ግብር የከተማዋን የንባብ ባህል ለማጎልበት እና የዲጂታል ቴክኖሎጂ ጫናን በመቀነስ የህብረተሰቡን ትኩረት ወደ መጽሐፍት ለማዞር ያለመ ነው፡፡

በአውደ ርእይው ላይ ማህበራዊ ሚዲያ እና የንባብ ባህል፣ ለምን እንጽፋለን? (ከታወቁ ደራሲያንና ጸሐፊዎች ጋር ውይይት)፣ መጽሐፍ እንዴት አስተሳሰባችንን ይቀይራል?፣ የንባብ ባህልን ከፌስቲቫሉ በኋላ እንዴት እናስቀጥል? የሚሉና ሌሎችም ጉዳዮች ውይይት እየተደረገባቸው ይገኛል። መርሃ ግብሩ ነሐሴ 21 ቀን 2018 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን እስከ ነሃሴ 25 ቀን 2018 ዓ.ም በአስሩ አንዱም ክፍለ ከተሞች ይከናወናል፡፡

## መጽሐፍት

በጋዜጠኛ ደረጀ ትዕዛዙ የተፃፈው እና በተባባሪ ፕሮፌሰር ተስፋዬ ገሠሠ ህይወት ላይ ትኩረቱን ያደረገ መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል፡፡ "ተስፋዬ ገሠሠ፡ ጉምቱ የጥበብ ባለሟል" በሚል ርእስ የቀረበው ይህ የህይወት ታሪክ መጽሐፍ በ452 ገጽ የተቀነበበ ነው፡፡ አንጋፋው የጥበብ ሰው ተባባሪ ፕሮፌሰር ተስፋዬ በአገራችን የቴአትር እና የኪነ ጥበብ ታሪክ ላይ የራሳቸውን አሻራ ትተው ያለፉ ባለውለታ እንደሆኑ አይዘነጋም። እኚህ አንጋፋ የጥበብ ሰው በታህሳስ 2013 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸው ይታወቃል። ደራሲው ከዚህ ቀደም የጋዜጠኛ፣ የደራሲና የታሪክ ተመራማሪው ጳውሎስ ኞኞን የሕይወት ታሪክ አዘጋጅቶ ለአንባቢያን አድርሷል።

## ሙያዊ ውይይት

በዛሬው እለት በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ውይይት ይደረጋል፡፡ የውይይቱ ርእሰ ጉዳይ "ኤክስፕሬሲቭ አርትስ ቴራፒ (በኪነ-ጥበብ የሚደረግ ሕክምና)፡ ከተግባር ወደ ማስረጃ፣ ከማስረጃ ወደ ሙያዊ እድገት" የሚል ነው። ተመራማሪዎች፣ ተማሪዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ የሳይንሱ ማህበረሰብ አባላት እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው በሙሉ በሚካሄደው መርሃ-ግብር ላይ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል፡፡ ውይይቱ 8፡00 ሰዓት ላይ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል እና ጉለሌ ወረዳ 8 ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ በሚገኘው በአካዳሚው ዋና መስሪያ ቤት ይደረጋል፡፡

## ሙዚቃ

ድምጻዊት ተዓምር ግዛው የመጀመሪያዋ የሆነ እና 16 ዜማዎችን ያካተተ "በፍቅር" የተሰኘ አልበም በዛሬው እለት ይለቀቃል። አልበሙ በድምጻዊቷ ይፋዊ የዩትዩብ (YouTube) ቻናል እና በተለያዩ ዲጂታል የሙዚቃ ማደመጫ መተግበሪያዎች (Music Streaming Platforms) ላይ እንደሚለቀቅ ተገልጿል። በአልበሙ ዝግጅት ላይ በርካታ አንጋፋ እና ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች ተሳፈውበታል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ በብሄራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7፡30 ሰዓት "12ቱ እንግዶች" እንዲሁም በ11:30 "በር የሌለው ቤት" ይታያሉ፡፡ እሁድ በ7፡30 ሰዓት "ንጉስ አርማሕ" እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት ደግሞ "እምዩ ብረቷ" ለእይታ ይቀርባሉ፡፡ ተመልካቾች ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ"ሁሉ በጄ" መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ "እሳት ወይ አበባ" ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 ሰዓት እንዲሁም "ባልቻ አባነፍሶ" ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጐ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት "አዮ ቦራ" የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት "የንባብ ከተማ" የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ በ8፡00 ሰዓት በቅርቡ ወደ መድረክ የመጣው "ወሀኒ አምባ" እንዲሁም 11፡30 ሰዓት "አትጥሪኝ" የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ።

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረቡእ በ11፡00 ሰዓት "አሉ"፣ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት "ነገሩ አይቆምም"፣ እሑድ በ8፡00 ሰዓት "ሰዴታ" (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት "የመጨረሻው ፍርድ" ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

የባለፈው ጥያቄ መልስ ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው 2 × 5 - 2 = 8 ይሆናል፡፡ ሁለተኛው 7 × 2 – 5 = 9 ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የመጨረሻው 3 × 4 – 7 = 5 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ቁጥር **5** ነው፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

የዛሬው የቁጥር ጨዋታ ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን።



# የመዝናኛ ስፍራዎችን በአዲስ እይታ

**በጊዜው አማረ**

መዝናኛ የሰው ልጅ የህይወት የኑሮ ዘይቤ አካል ነው፡፡ ሰው ከዕለት ተዕለት ውጥረትና ስራ ጫና ነፃ ወጥቶ አእምሮውን ማደስ ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ በርካታ የተዝናኖት አማራጮች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በዚህም ዛሬ ላይ መዝናኛ ከቀድሞው ተለምዷዊ አሰራር ወጥቶ፤ ባህልን፣ ተፈጥሮን እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ያቀፈ ዘርፍ ሆኗል። ለለውጡ መሰረት የሆኑት የተለያዩ የመዝናኛ አማራጮች ህብረተሰቡ ጊዜውን በአግባቡ እንዲጠቀም እና እና ተዝናኖትን የእለት ተእለት የህይወት ልምዱ እንዲያደርገው አስችለዋል፡፡

በዚህ ሰፊ የመዝናኛ ዓለም ውስጥ ባህል እና ቅርሶች ይጎበኛሉ። ሰዎች አይረሴ ፎቶዎችን ይነሳሉ። ነዋሪዎችም የየሀገራቸውን ታሪክ፣ የጥበብ ስራዎች እና የዕለት ተዕለት አኗኗር የሚያንጸባርቁ ሙዚየሞችን፣ ቅርሶችን እና በዓላትን ይታደማሉ፡፡ ከመዝናናት ባሻገር ማህበራዊ ትስስርን ይፈጥራሉ። ለትውስታ የሚበቃ ጊዜ ያሳልፋሉ። ከዚህ በተጨማሪ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ አረንጓዴ ቦታዎች እና ፓርኮች ዜጎች ከጫጫታ ርቀው ንጹህ አየር የሚተነፍሱባቸው፣ አእምሯቸውን የሚያሳርፉባቸው እና ከቤተሰብ ጋር የማይረሳ ሰዓት የሚያሳልፉባቸው ተመራጭ መዳረሻዎች ሆነዋል።

ከእነዚህ የመዝናኛ አማራጮች ውስጥ ውሃ አንዱ ነው፡፡ ውሃ ለሰው ልጅ አካላዊ እና አእምሯዊ ጤንነት ካሉት መሰረታዊ ጥቅሞች ባሻገር፣ ለመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጠው ፋይዳ እጅግ የጎላ ነው። የባህር ዳርቻዎች፣ ሐይቆች፣ ፏፏቴዎች፣ ወንዞች እና ሰው ሰራሽ የመዋኛ ገንዳዎች ሰዎች ከዕለት ተዕለት ውጥረትና የስራ ጫና ተላቅቀው እረፍት የሚያደርጉባቸው መዳረሻዎች ናቸው።

ከአእምሮ ዕረፍት ባለፈ፣ ውሃ ተዝናኖትን የሚፈጥሩ የተለያዩ አሳታፊ ተግባራትን ለማከናወን ያስችላል። እንደ መዋኘት፣ አሳ ማጥመድ እና በጀልባ መንሸራሸር ያሉት መዝናኛዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ከደስታ ጋር የሚያጣምሩ ናቸው።

በዚህ ዘመን የቱሪዝም እና መዝናኛ ኢንዱስትሪዎች የውሃ አካላትን መሰረት ያድረጉት በዚህ መነሻነት ነው። በውሃ ዳርቻዎች የሚገነቡ ሪዞርቶች፣ ዘመናዊ መዋኛ ፓርኮች እና የውሃ ፏፏቴዎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ከማሳደግም በላይ፣ የሰዎችን የኑሮ ደረጃ እና የተዝናኖት ፍላጎት ከፍ ያደርጋሉ።

ይሁንና ኢትዮጵያ በበርካታ ወንዞች፣ ሐይቆች እና ውብ የተፈጥሮ ጸጋዎች የታደለች ሀገር ብትሆንም ለውሃ መዝናኛ ልማት ብዙም ትኩረት ሳትሰጥ ቆይታለች። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ሀገሪቱ እነዚህን የተፈጥሮ ስጦታዎች በአግባቡ በመጠቀም የቱሪዝም እና



ፎቶ፡- ኤ አይ ቻት ጂፒቲ

ፎቶ- ከገፀ ድር

ውሃ ተጨማሪ ውበት ከፈጠረላቸው የአዲስ አበባ የመዝናኛ አካባቢዎች በከፊል

የመዝናኛ ዘርፉን ለማሳደግ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ነው። በተለይም የውሃ አካላትን መሰረት ያደረጉ ዘመናዊ መሰረተ ልማቶችን በመስራቷ ዘርፉ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቱሪስቶችን በመሳብ ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው።

በአዲስ አበባ፣ በክልል ከተሞችና በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማት እና የውሃ ፓርኮች ግንባታዎች ተጠቃሽ ናቸው። በአዲስ አበባ ቀበናን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የተከናወኑ ፕሮጀክቶች የውሃ መዝናኛዎችን ያካተቱና የነዋሪዎች የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ አዲስ መልክ እንዲይዝ አድርገዋል።

ከመዲናዋ ውጭ የሚገኙት እንደ ጣና፣ ሎጊያ፣ አርባ ምንጭ፣ ወንጪ፣ አባያ፣ ሐዋሳ ያሉ ትላልቅ ሐይቆች የቱሪዝም መዳረሻዎች በመሆን እያገለገሉ ናቸው። በእነዚህ የሐይቅ ዳርቻዎች የተገነቡ ሪዞርቶች፣ የጀልባ ማቆሚያዎች እና የመዋኛ ስፍራዎች ጎብኚዎችን በመሳብ ለጉዞ እና ለእረፍት ተመራጭ ስፍራዎች ሆነዋል።

እነዚህ የውሃ መዝናኛ አማራጮች መስፋፋታቸው ለአእምሮ መታደስ እና ለእረፍት ከመጥቀሙም በላይ፣ ህብረተሰቡ እርስ በእርስ የሚገናኝባቸው እና ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክርባቸው ማዕከላት ናቸው። ቤተሰቦች ወደ ውሃ ዳርቻዎች እና ፓርኮች በመሄድ አብረው ጊዜ ያሳልፋሉ፤ ወጣቶችም በተለያዩ የውሃ አካባቢዎች በሚደረጉ አዳዲስ መዝናኛዎች ይሳተፋሉ። ይህ ማህበራዊ መስተጋብር የህብረተሰባችንን የጋራ ትስስር እያጠናከረው መሆኑን በቀበና ወንዝ ያለው ሁኔታ አንዱ ማረጋገጫ ነው። በቀበና ህጻናት የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡ የማህበራዊ ሚዲያ ይዘት ፈጣሪዎች የመዝናኛ ቪዮዎችን ይቀርጻሉ። በትንንሽ ጀልባዎች ደግሞ ቤተሰቦችና ጓደኛሞች ይንሸራሸራሉ፡፡

ኢትዮጵያ በውሃ መዝናኛ ልማት ላይ እያከናወነችው ያለው ስራ እነዚህን የውሃ ሀብቶች ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና ከኢኮ-ቱሪዝም መርሆዎች ጋር በማጣጣም ይበልጥ ተደራሽ እና አዋጭ ለማድረግ ትልቅ ተስፋ ሰጪ መሰረት ጥሏል።

በተለይ የአዲስ አበባ ወንዞች እና ፏፏቴዎች ውበትን ከንጽህና ጋር በማቀናጀት ከተማዋን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመዲናዋ እየተከናወኑ ያሉ የወንዞች ልማት ፕሮጀክቶች እና ውብ ፏፏቴዎች የከተማዋን የቱሪስት መዳረሻነት እያሳደጉት ይገኛሉ። እነዚህ የውሃ አካላት የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ ለነዋሪዎች እና ለጎብኚዎች ልዩ የእረፍት ስፍራዎችን በመፍጠር ላይ ናቸው።

የአዲስ አበባ የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን በቅርቡ ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንደተናገሩት፣ በከተማዋ ውሃማ አካላትን ያካተቱ የህዝብ መዝናኛዎች በስፋት እየተገነቡ ነው፡፡ አንድ ፓርክ ፓርክ ነው የሚባለው ከ80 በመቶ በላይ በአረንጓዴ ሲሸፈን ነው። የውሃና ሌሎችም አካላት ሽፋን ከ20 እስከ 30 በመቶ መሆን አለበት፡፡ በአዲስ አበባ በኮሪደር ልማት የተሰሩ ፓርኮች እነዚህን ዓለም አቀፍ መመዘኛዎች የሚያሟሉ ናቸው፡፡ ለአብነት፡- በእንጦጦ ፓርክ ያለው ውሃ፣ አረንጓዴ ሽፋንና ግንባታው ዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲያሟላ አስችሎታል፡፡

በሌሎች የመዲናዋ አካባቢዎች በተሰሩ የወንዝ ፕሮጀክቶች ዙሪያ የተዘረጉ የእግር መንገዶች፣ የአረንጓዴ ልማት ፓርኮች እና የመዝናኛ ስፍራዎች ሰዎች ከከተማው ጫጫታ ርቀው ተፈጥሮን እንዲያጣጥሙ እድል ሰጥተዋል፡፡ ለእንግዶች ምቹና ንጹህ መዳረሻ ሆነዋል፡፡ ይህም የአዲስ አበባን የኮንፈረንስ ቱሪዝም ተወዳዳሪነት በከፍተኛ ደረጃ ያሳድገዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር) ቦሌ አትላስን እንዲሁም የቅርብ ጊዜ የቀበና ወንዝ ፕሮጀክትን ጨምሮ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ የእንጦጦ እና አራዳ ፓርኮች፣ ወዳጅነት አደባባይ አራዳ ፓርክ እና ሌሎችም የኮሪደር ልማት ስራዎች የአዲስ አበባን የከተማ ደረጃና ጽዳት ታሪክ በአዲስ ምዕራፍ የጻፈ ስኬት ነው። ቀደም ሲል ባዶና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች አጋላጭ የነበሩ ወንዞችና ቦታዎች፣ ዛሬ በፅዳታቸውና በአረንጓዴነታቸው ወደሚደነቁ ዘመናዊ መዝናኛዎች ተለውጠዋል። እነዚህ በርካታ ነዋሪዎችና ጎብኝዎች በየቀኑ የሚዝናኑባቸው የውበት ማዕከላት መሆን ችለዋል ሲሉ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም በዋና ዋና አደባባዮች እና የህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች የተገነቡና የሚገነቡ ውብ ፏፏቴዎች ከተገጠመላቸው ብርሃናማ ቀለማት ጋር ሲዋሃዱ የከተማዋ ውበት ማሳያ ድንቅ ጥበቦች ሆነዋል። በምሽት ጊዜ በተለያየ ቀለም መብራቶች የሚዋቡት እነዚህ ፏፏቴዎች ለመዲናዋ ልዩ ድምቀት በመስጠት ከቀን በተጨማሪ የምሽት ህይወትን ይበልጥ ማራኪ አድርገውታል፡፡ የውሃ ውበት ከዘመናዊ መብራቶች እና አርክቴክቸር ጋር ሲዋሃድ የከተማዋን ዘመናዊነት እና ስልጡን ገጽታ ለዓለም ይመሰክራል፡፡ አዲስ አበባም በዚህ መንገድ ላይ ትገኛለች፡፡

እነዚህን የመዲናዋ የወንዞች እና የፏፏቴን መዝናኛ ስፍራዎችን ማልማትና መጠበቅ የከተማዋን ኢኮኖሚ ከማሳደጉም በተጨማሪ ለነዋሪዎች ምቹ የተዝናኖት መዳረሻዎች እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ ቱሪስቶች ከተማዋን ሲጎበኙ የሚፈጥሩት የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እድል ለሆቴሎች፣ ለአስጎብኚዎች እና ለአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ትልቅ እድል ይፈጥራል። በአጠቃላይ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የተሰሩ ኢኮ ሪዞርቶች፣ የአዲስ አበባ ወንዞችና ፏፏቴዎች መዲናችንን ብሎም ሀገራችንን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ እና የቱሪዝም ማዕከልነትን ለማረጋገጥ የማዕዘን ድንጋይ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# በዘንድሮው መሐር ከከተማ ግብርና ምን ይጠበቃል?

- በአዲስ አበባ ከተማ በመኸር እርሻ 7 ሺህ 165 ሄክታር መሬት በተለያዩ ሰብሎች መሸፈናቸው ተመላክቷል


ፎቶ፡- ከገጸ ድር
በመኸር እርሻ ከተከናወኑ የከተማ ግብርና ስራዎች መካከል አንዱ



በይግለጡ ጓዴ

የመኸር እርሻ ወቅት በኢትዮጵያ ግብርና ውስጥ ከፍተኛውን የምርት ድርሻ የሚይዝ እና የሀገሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ዋና የምርት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት በገጠር የአገሪቱ ክፍሎች የሚካሄደው የግብርና እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚካሄደው የከተማ ግብርናም ከፍተኛ ምርት የሚያስገኝበትና ለከተማዋ የምግብ አቅርቦት ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክትበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በዘንድሮው የመኸር ወቅትም በከተማዋ አመርቂ የምርት ውጤት ማግኘት የሚያስችል ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ትግበራ ተገብቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ለአካባቢው አርሶ አደሮች አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብዓቶችን ማለትም እንደ ዳፕ እና ዩሪያ ያሉ የአፈር ማዳበሪያዎችን፣ የተሻሻሉ ምርጥ ዘሮችን፣ የውሃ ፓምፖችን እና ሌሎች ግብዓቶችን በበቂ ደረጃ ማሰራጨቱን አስታውቋል። ይህ የግብዓት አቅርቦትና ሙያዊ ድጋፍ ለአርሶ አደሮች በወቅቱ በመድረሱ የእርሻ ስራው በጥሩ ሁኔታ እንዲቀላጠፍ አስችሏል።

ለአብነት ያህል በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር ታቦር ከበበ፣ መሬታቸውን በደንብ በማረስና በማለስለስ 10 ሄክታር መሬት በተለያዩ የዘር አይነቶች መሸፈናቸውን ገልጸዋል። ከአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ኮሚሽን ባለሙያዎች በቂ የግብዓትና ሙያዊ ድጋፍ ማግኘታቸውን የጠቆሙት አርሶ አደር ታቦር፤ በዘንድሮው ወቅት 2 ሄክታር ስንዴ፣ 7 ሄክታር ጤፍ እንዲሁም 1 ሄክታር ጓያና ሽምብራ ዘርተዋል። ለዚህም 25 ኩንታል ዳፕ እና 100 ኪሎ ግራም የጤፍ ዘር ጥቅም ላይ ማዋላቸውን ጠቅሰው፣ የአረም እና ኩትኳቶ ስራዎችን በወቅቱ በማካሄድ ከ150 ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት አቅደው እየሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በየክፍለ ከተማው ያለው ዝግጅትና የልማት እንቅስቃሴ ሲታኝም ከፍተኛ ውጤት እንደሚመዘገብ ያመላክታል። በቦሌ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የእፅዋት ልማት ቡድን መሪ ወይዘሮ ህይወት በለጠ እንደገለጹት፣ በክፍለ ከተማው በመኸር የሰብል እርሻ አመርቂ ውጤት ማስገኘት የሚያስችል ዝግጅት ተደርጓል። ለዚሁ ስራ 1 ሺህ 210 ኩንታል ዩሪያ እና 1 ሺህ 210 ኩንታል ዳፕ ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል። በክፍለ ከተማው 891 ነጥብ 9 ሄክታር ጤፍ እና 220 ሄክታር ስንዴ በድምሩ ከ1 ሺህ 111 ሄክታር በላይ መሬት በዘር የተሸፈነ ሲሆን፣ ከዚህም 3 ሺህ 108 ቶን የምርት መጠን ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ 1 ሺህ 90 ሄክታር መሬት ለሰብል ልማት መዘጋጀቱን የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ አህመድ ኡርጎ አስታውቀዋል። በክፍለ ከተማው 2 ሺህ 180 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እና 226 ኩንታል የተሻሻለ ምርጥ ዘር ጥቅም ላይ በማዋል፣ ከ39 ሺህ 240 ኩንታል በላይ የስንዴ እና የጤፍ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል።

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በበኩሉ 365 ሄክታር መሬት በጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ እና ሌሎች ሰብሎች መሸፈኑን የእጽዋት ዘርፍ ቡድን መሪ ወይዘሮ ታየች አለማር ገልጸው፣ ለዚህም 820 ኩንታል ዳፕ እና ዩሪያ ማዳበሪያ እንዲሁም የተለያዩ ምርጥ ዘሮች ጥቅም ላይ ውለዋል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ከፍተኛ አግሮኖሚስት አቶ ተስፋዬ ኪዳነማርያም እንደተናገሩት፣ በሁሉም ማስፋፊያ ክፍለ ከተሞች 7 ሺህ 165 ሄክታር መሬት በመኸር ሰብል ለምቷል። የመኸር ምርቱን በሚፈለገው መጠንና ጥራት ለማግኘት አስፈላጊው የሙያና የግብዓት ድጋፍ ወቅቱን ጠብቆ ለሁሉም ክፍለ ከተሞች መደረጉን ገልጸዋል።

አርሶ አደሮች የእርሻ ማሳ ዝግጅታቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲያከናውኑ በተሰጠው ግንዛቤ መሠረት በቦሌ፣ ለሚ ኩራ፣ አቃቂ ቃሊቲ እና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ 413 ሞዴል አርሶ አደሮች መሬታቸውን በትራክተር አርሰው መዝራታቸው በመስክ ምልከታ ተረጋግጧል። በጠቅላላው 4 ሺህ 982 ነዋሪዎች በመኸር እርሻው ተሳታፊ ሲሆኑ፣ ለ764 ሞዴል አርሶ አደሮች ደግሞ ልዩ ግንዛቤ መፈጠሩ ተገልጻል።

ኮሚሽኑ ህብረተሰቡን በከተማ ግብርና በስፋት በማሳተፍ፣ ለከተማ የሚስማማ የኤክስቴንሽን ስርዓት ሥራ ላይ በማዋል እና ጤናማ የግብርና ምርት አቅርቦትን በማሳደግ ረገድ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። አርሶ አደሩ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ማሽኖችን በመጠቀም ሰብሉን በመስመር እንዲዘራ ተደርጓል። በተጨማሪም የኑሮ ውድነቱን ለማቃለልና ከተማዋን ከተረጂነት ወደ አምራችነት ለማሸጋገር ሲባል፣ ክፍት መሬቶችና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ግቢ ውስጥ ያሉ ክፍት ቦታዎች እንዲታረሱ ተደርጓል።

በምርት ዘመኑ እስከ አሁን ድረስ ከጠቅላላው 14 ሺህ 384 ነጥብ 5 ኩንታል ዳፕ እና ዩሪያ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል። በምርጥ ዘር በኩል ከተያዘው 1 ሺህ 075 ኩንታል እቅድ ውስጥ 341 ነጥብ 1 ኩንታል ሲ-1 እና 5 ሺህ 961 ነጥብ 2 ኩንታል ሲ-2 በድምሩ 6 ሺህ 302 ነጥብ 3 ኩንታል ምርጥ ዘር ማከፋፈል ተችሏል።

የመኸር እርሻ ስራው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ቢሆንም፣ የተቀመጡ የቴሌግራም ሪፖርት ማድረጊያ ቻናሎችን ተጠቅሞ ወቅታዊ መረጃዎችን ሙሉ በሙሉ አለመላክ፣ የሚታረስ መሬት መረጃ ተለዋዋጭ መሆን፣ አርሶ አደሩ የሲ-1 ምርጥ ዘርን በስፋት አምጥቶ አለመጠቀም እና በዘር ወቅት የዝናብ ዘግይቶ መጀመር እንደ ችግር ተጠቅሰዋል።

እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ኮሚሽኑ የትራንስፖርት ድጋፍ በማድረግ፣ በየደረጃው ከሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ስራ እያካሄደ ይገኛል።

በቀጣይም ያልተጠናቀቁ እንደ ሽምብራና ጓያ ያሉ የጥራጥሬ ሰብሎች የዘር ስራ እንዲጠናቀቅ፣ የተዘሩ ሰብሎችን የአረም፣ የበሽታና የተባይ መከላከል ስራዎች በትኩረት እንደሚሰሩ ተገልጿል። በዚህ የእርሻ እንቅስቃሴ የሴቶችና የወጣቶች ተሳትፎ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፣ በ2018/19 የምርት ዘመን በከተማዋ በለማው 7 ሺህ 165 ሄክታር መሬት በአጠቃላይ 20 ሺህ 704 ነጥብ 78 ቶን የምርት መጠን ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አደረጃጀት በመኸር ወቅት የከተማዋን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የኑሮ ውድነትን ለማቃለል እየተከናወነ ያለው ሰፊ የግብርና ስራ እንቅስቃሴ አበረታች ነው። በክፍለ ከተሞች በለማው 7 ሺህ 165 ሄክታር መሬት ላይ ከ20 ሺህ 704 ቶን በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዶ የአፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ የቴክኖሎጂና የሙያ ድጋፍ ለአርሶ አደሮች ተሰራጭቷል። ምንም እንኳን የዝናብ ዘግይቶ መጀመርና የመረጃ ልውውጥ ክፍተቶች ያሉ ቢሆንም፣ የክትትል ስራዎችን በመጠናከር፣ ያልታረሱ መሬቶችን በመጠቀም እና የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ በማሳደግ ከተማዋን ከተረጂነት ወደ አምራችነት የማሸጋገር ስራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ ይገኛል።

# ለአዲሱ የትምህርት ዘመን የልጆች ዝግጅት

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? ክረምቱን እንዴት እያሳለፋችሁ ነው? ጥሩ ነው እንደምትሉ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን መጪው ጊዜ አዲስ የትምህርት ዓመት የሚጀመርበት እንደመሆኑ መጠን የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻል ዘንድ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ እናንተ በምን ልክ ተዘጋጅታችኋል? ሀሳብ ተለዋወጡ፤ እኛ ደግሞ ያነጋገርናቸውን ልጆች አስተያየት በሚከተለው መልኩ አቅርበንላችኋል፡፡


ፎቶ፡- ኤ አይ ቻት ጂፒቲ
አስቀድሞ የሚደረግ ዝግጅት ለተማሪዎች የዕውቀት መጎልበት ትልቅ ፋይዳ አለው

ዮሐንስ አለምእሸት እባላለሁ፡፡ 10 ዓመቴ ነው፡፡ የ3ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ በክረምት ወቅት እረፍት አድርጌያለሁ። ጠዋት 1፡00 ሰዓት ነበር ከእንቅልፌ የምነሳው፡፡ አሁን ላይ 12፡30 ሰዓት በመነሳት ልምምድ እያደረግሁ ነው። ለዚህ እንዲያግዘኝ ማታ እስከ 2፡00 ሰዓት ባለው እተኛለሁ፡፡ በዕረፍት ጊዜዬ የተለወጠውን የመኝታና የጨዋታ ፕሮግራም ቀስ በቀስ ወደ መደበኛው እየመለስኩ ነው፡፡

ሌላኛው ዝግጅት እያደረግሁ ያለሁት የማንበብ ልምምድ ነው፡፡ ሳላነብ ብቆይ ወደ ትምህርቱ ስገባ ሊያስቸግረኝ ስለሚችል ትንሽ ትንሽ እያነበብኩ ነው።

እየሩሳሌም ከተማ እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ሲሆን የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። ለ2019 የትምህርት ዘመን በተለያዩ ነገሮች ቅድመ ዝግጅት እያደረግኩ ነው፡፡ በመደበኛው ትምህርት ወቅት ለእንቅልፍ፣ ለጥናት፣ ለጨዋታ እና ቤተሰቦቼን ለማገዝ ብዬ ከዚህ በፊት የማወጣውን የጊዜ ሰሌዳ ቀድሜ አውጥቻለሁ፡፡ ይህንን የማደርገው እንደ አዲስ ስጀምረው በትምህርቴ ላይ ጫና እንዳይፈጥርብኝ ነው፡፡ የ6ኛ ክፍል መጻሕፍትንም እያነበብኩ ነው፡፡

ያነጋገርናቸው ልጆች ሃሳባቸውን በዚህ ልክ አጋርተዋል፡፡ ይህን የልጆች ሀሳብ ባለሙያዎች ይስማሙበታል፡፡

ወይዘሪት ህይወት አየለ እባላለሁ። ሁለንተናዊ የልጆች እድገት ባለሙያ ነኝ፡፡ ልጆች፤ ዛሬ የምነግራችሁ ለ2019 የትምህርት ዘመን ምን ምን ዝግጅቶችን ማድረግ እንዳለባችሁ ነው። የመጀመሪያው መዘጋጀት ያለባችሁ የጊዜ አጠቃቀማችሁ ላይ ነው፡፡ ይህም ስትማሩ ንቁና የማያረፍድ ልጅ ለመሆን የእንቅልፍ ሰዓታችሁን ማስተካከል፣ ከዚህ በፊት የምታደርጉትን የቀን ውሏችሁን ከመዝናናትና ከመጫወት ይልቅ ማንበብ፣ ረጅም ሰዓት ስልክና ቴሌቪዥን ላይ የምታሳልፉ ከሆነ መቀነስ አለባችሁ፡፡

ሁለተኛው መዘጋጀት ያለባችሁ በሥነ ልቦና ነው፡፡ ይህም ሲባል አዳዲስ ጓደኞች፣ መምህራን ልታገኙ እንዲሁም የምትማሩት የትምህርት አይነት ቁጥሩ ሊጨምር እንደሚችል ታሳቢ ማድረግ አለባችሁ፡፡ ጥሩ ውጤት ለማምጣትም ግብ ማስቀመጥ ይጠበቅባችኋል። እነዚህንና መሰል ዝግጅቶችን አስቀድማችሁ ካደረጋችሁ የተሻለ የትምህርት ዓመት ይሆንላችኋል፡፡

## ስለ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ በጥቂቱ




ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ማለት በነዳጅ ምትክ በኤሌክትሪክ ሃይል የሚንቀሳቀስ መኪና፣ አውቶቡስ ወይም ሌላ ተሽከርካሪ ነው። ኃይሉን በባትሪ ውስጥ ይይዛል፤ ባትሪውም በቻርጅ መሙያ ይሞላል። እንደ ነዳጅ የሚቃጠል ነገር ስለማይጠቀም የአየር ብክለትንና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ ይረዳል። በተጨማሪም የነዳጅ ወጪን ይቀንሳል። ስለዚህ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ንጹህ አየር እና ጤናማ ከተማ ለመፍጠር ከሚረዱ መንገዶች አንዱ ነው።

አዲስ አበባም ይህን ዘመናዊ የመጓጓዣ መንገድ እየተጠቀመች ነው። በከተማዋ ኤሌክትሪክ አውቶቡሶች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ በከተማዋ የኤሌክትሪክ መኪናዎች ባትሪ የሚሞሉባቸው ፈጣን የቻርጅ ጣቢያዎች እየተስፋፉ ነው፡፡ አንዳንድ የኮሪደር ልማቶችም የቻርጅ ጣቢያዎችን አካትተዋል። ይህም አዲስ አበባ ወደ ንጹህ፣ አረንጓዴና ዘመናዊ የመጓጓዣ ሥርዓት እየተሸጋገረች መሆኗን ያሳያል።

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ቆርቋፊት ምላጭትን ወለደች፤ምላጭትን ቆርቋፊትን ወለደች?**

**መልስ፡-** ለ. ዶሮ እና እንቁላል

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ግንዱ ወደ ላይ ጫፉ ወደ ታች?**

ሀ. ካሮት
ለ. ቅርንጫፍ
ሐ. የከብት ጅራት

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# “ባለፉት ዓመታት በዲጂታላይዜሽን ዘርፉ ታሪካዊና ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች ተወስደዋል”

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አዋሌ መሐመድ**

**በደረጀ ታደሰ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የተቋቋመበት ዋና ተልዕኮ የመዲናዋን አጠቃላይ የመንግስትና የህዝብ አገልግሎቶች በዘመናዊ የዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዙ፣ የተቀላጠፉ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ማድረግ ነው። በተጨማሪም ቢሮው የከተማዋን የስማርት ሲቲ ርዕይ ዕውን ለማድረግ የሚያስችሉ የመሰረተ-ልማት፣ የሶፍትዌር፣ የደህንነት እና የሰው ኃይል አቅም ማሳደጊያ ስልቶችን በመቀየስ መሪ ሚና ይጫወታል።

ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እጅግ ወሳኝ በሆነበት በዚህ ዘመን፣ እንዲህ ያለ ርዕይ እና ተልዕኮ ያላቸው ተቋማት አስፈላጊነታቸው አያጠያይቅም፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን ቁልፍ ጉዳይ ለማሳካት የተቋቋመው ቢሮው፤ ባለፉት ዓመታት ያከናወናቸው ተግባራት፣ ያሳካቸው ውጤቶች እና በቀጣይ ትኩረት የሚያደርግባቸው ተግባራት ላይ ሰፊ ማብራሪያ ይዘናል፡፡

አቶ አዋሌ መሐመድ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ ናቸው፡፡ እሳቸው የሚመሩት ተቋም የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት፣ ተቋማዊ ርዕዩንና ተልዕኮውን ለማሳካት በትኩረት እየሠራ መሆኑን በመጠቆም፤ “አዲስ አበባን በምስራቅ አፍሪካ ቀዳሚ ዲጂታላይዝድ እና ብልህ (Smart) ከተማ ማድረግ፣ የመንግስት አገልግሎቶችን ሙሉ ለሙሉ በዲጂታል አማራጮች ማቅረብ፣ የህዝቡን የዲጂታል ክህሎት ማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራና ስታርት-አፖችን መደገፍ እንዲሁም አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ መሰረተ-ልማት መገንባት” የሚሉት ከተቋሙ ቁልፍ ተግባራት መካከል የሚጠቀሱ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

ቢሮው፣ የተሠጠውን ኃላፊነት በውጤታማነት ከመወጣት አንጻር፣ ያለፉት ሦስት እና አራት ዓመታት በስኬታማነት የሚጠቀሱ ስለመሆናቸው ያነሱት አቶ አዋሌ፤ ለዚህ ደግሞ የከተማ አስተዳደሩ ለዘርፉ የሰጠው ከፍተኛ ትኩረት፣ ያልተቋረጠ መመሪያና ድጋፍ ቁልፍ ሚና መጫወቱን አስረድተዋል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በመዲናዋ በዲጂታላይዜሽን ዘርፍ በርካታ ታሪካዊና ስትራቴጂካዊ እርምጃዎች መወሰዳቸውንም ገልጸዋል፡፡

የቢሮ ኃላፊው አቶ አዋሌ እንዳብራሩት፤ ባለፉት ዓመታት በተሠራው ሥራ የመንግስት አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከልና በዲጂታል ፕላትፎርም አቀናጅቶ ማቅረብ ተችሏል፡፡ የከተማዋን ፈጣን ዕድገትና ለውጥ ታሳቢ ያደረገ የኢንፎርሜሽን



ፎቶ- ከፋይል
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አዋሌ መሐመድ

> ባለፉት ዓመታት በተሠራው ሥራ የመንግስት አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከልና በዲጂታል ፕላትፎርም አቀናጅቶ ማቅረብ ተችሏል። የከተማዋን ፈጣን ዕድገትና ለውጥ ታሳቢ ያደረገ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታም ተከናውኗል

ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ተከናውኗል፡፡ ለአብነት ያክል፡- በከተማዋ በተካሄዱት የኮሪደር ልማት ስራዎች በመቶ ኪሎ ሜትሮች የሚለኩ የመሬት ውስጥ የፋይበር ኦፕቲክስ ቧንቧና የመረጃ መስመር ዝርጋታ መከናወኑ፣ የዳታ ሴንተር መገንባትና ማዘመን መቻሉ፣ ደረጃውን የጠበቀና አስተማማኝ Tier-III የዳታ ሴንተር በማልማት የሁሉም ተቋማት መረጃ በአንድ ቋት እንዲደራጅ መደረጉ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እንደከተማ አስተዳደር የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞው በርካታ ስኬቶች ያሉት ቢሆንም፣ በሂደቱ ውስጥ ችግሮች እንደሚያጋጥሙ አቶ አዋሌ አልሸሸጉም፡፡ በዘርፉ ከሚታዩ ችግሮች መካከል፡- የኢንተርኔት አገልግሎት እና የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት መቆራረጥ፣ በዚህ ምክንያት በዲጂታል አገልግሎት ላይ መጓተት መፈጠር አንዱ መሆኑን አንስተዋል፡፡ የለውጥ መቋቋም (Resistance to Change) ሌላኛው የዘርፉ ችግር ሲሆን፤ ይህም በአንዳንድ ተቋማት ዘንድ ባህላዊውን አሰራር የመልቀቅ ፍላጎት ማነስና ለዲጂታል አሰራር ጥርጣሬ ማደር እንደሚስተዋል ኃላፊው አብራርተዋል፡፡

መዲናዋ በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞዋ ልትደርስበት ካለመቻው ግብ እንዳትገታ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት ስልታዊ የመፍትሔ እርምጃዎችን መውሰዱን ኃላፊው አስረድተዋል፡፡ እንደሳቸው ገለጻ፤ የኢንተርኔትና የኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥን ለመፍታት የተለያዩ አማራጮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተቋማት በቅርቡ ለአገልግሎት የበቃውን አዲሱን የፋይበር ኦፕቲክስ ኮሪደር መስመር እንዲጠቀሙ መደረጉ፣ ከጸሐይ (ሶላር) የኃይል አማራጭን በመጠቀም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል በድንገት በሚቋረጥበት ወቅት ኮምፒዩተሮች እና የዲጂታል አገልግሎት መስጫ ማሽኖች ሥራቸውን እንዳያቋርጡ ኃይል ቆጥበው የሚያቀርቡ (Backup UPS) ሲስተሞችን በዳታ ሴንተሮች በመትከል ለአገልግሎት የበቁበት ውጤታማ የመፍትሄ እርምጃዎች ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፤ የአመራር ቁርጠኝነትን በማሳደግ፣ ሰፊ የአመለካከት ማነጻጸሪያና የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደ-ጥናቶችን (Workshops) በማዘጋጀት እና ተያያዥ ተግባራትን በመፈጸም በየተቋማቱ ባለው የሠው ኃይል ላይ የሚታየውን የአስተሳሰብ ተግዳሮት ማሻሻል ተችሏል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ስኬታማ ተግባራት በውጤታማነታቸው ለማስቀጠል፣ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ ቀሪ ተግባራትን ለማከናወን የያዝነው አዲሱ (የ2019) በጀት ዓመት ወሳኝ ስለመሆኑ፣ እንደቢሮ የተቀመጡ የዓመታዊ ዕቅዱ ዋና ዋና የትኩረት መስኮች ያሳያሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የከተማዋን ዲጂታል ሽግግር ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ካስቀመጣቸው ቁልፍ ተግባራት አንዱ፣ የመዲናዋን የዲጂታል አገልግሎት ስምሪት (Full End-to-End Digitalization) 100 ፐርሰንት ማድረስ ነው፡፡ በከተማ ደረጃ የሚሰጡ ሁሉንም የህዝብ አገልግሎቶች የወረቀት ንክኪ የሌላቸው ማድረግና ተገልጋዮች በአካል ሳይገኙ በሞባይልና በዌብሳይት አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ በተሟላ አግባብ ዕውን ማድረግ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥና አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (AI & Data Analytics Integration) አቅምን ማሳደግ፣ ለትራፊክ አስተዳደርና ለከተማ ፕላን አገልግሎት የሚውሉ የAI ቴክኖሎጂዎችን መተግበር፣ የሳይበር ደህንነት ማዕከልን ማጠናከር በበጀት ዓመቱ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፤ በቀጣይ ዓመታት አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ በስማርት ቴክኖሎጂ የተገናኘች (Smart Connected City) ማድረግ፣ የቴክኖሎጂ ፓርኮችን ማጠናከር፣ እና ወጣቶች በዲጂታል ስራዎች (Digital Freelancing) የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙበትን ዕድል ማስፋፋት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የትኩረት መስኮች ስለመሆናቸው የቢሮው ኃላፊ አቶ አዋሌ መሐመድ ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተሠራው ሥራ አዲስ አበባ ዘመናዊነትን ያማከለ ዕድገት አስመዝግባለች፤ የስማርት ሲቲ ርዕይዋን ለማሳካትም እስካሁን የመጣችበትን ጉዞ አጠናክራ ማስቀጠል ይገባታል። ለዚህ ደግሞ የሚመለከታቸው ተቋማት፣ አመራሮች፣ ሙያተኞች እና መላው ሕብረተሰብ በባለቤትነት ስሜት ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ ኃላፊው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

**ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ**

# ፅንሰ ሀሳበ በተግባር የሚጎለብትባቸው ማዕከላት

- **የኮሌጁ የሰርቶ ማሳያ ማዕከላት ተማሪዎች በንድፈ-ሀሳብ የቀሰሙትን እውቀት በሰው ሰራሽ ሞዴሎች ላይ በተግባር እንዲለማመዱ በማድረግ ብቁ የጤና ባለሙያዎችን ለማፍራት ማስቻላቸው ተገልጿል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**



ፎቶ፡- ከገፀ ድር
የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች በኮሌጁ የሰርቶ ማሳያ ማዕከል ተግባራዊ ልምምድ ሲያደርጉ

የዘመናዊ የህክምና ትምህርት ጥራት የሚለካው ከተማሪዎች የንድፈ-ሀሳብ እውቀት ባሻገር በተግባር በተሞከረ እውቀት በመደገፉ ነው። ለዚህ ዘርፍ አይነተኛ ድርሻ ያላቸው የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች ለሀገር ጤና አገልግሎት ጥራት መረጋገጥ መሠረት የሚሆኑ ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያደርጉት ጥረት ከክፍል ውስጥ የፅንሰ ሀሳብ ትምህርቶች አልፎ ዘመናዊ ማዕከላትን በመገንባት ላይ ያተኮረ ነው። ከእነዚህም መካከል የሰርቶ ማሳያ እና ክህሎት ማዕከላት (Skill Lab and Demonstration Centers) ዋንኞቹ ሲሆኑ፣ የህክምና ተማሪዎች ከእውነተኛ ህሙማን ጋር ከመገናኘታቸው በፊት መሰረታዊ እና ውስብስብ የህክምና ክህሎቶችን ያለስጋት እንዲለማመዱ የሚያስችሉ ወሳኝ ግብዓቶች ናቸው።

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት እነዚህ ማዕከላት ታካሚን የማዕከላዊነት መርህ በጠበቀ መልኩ፣ በዘመናዊ ሰው ሰራሽ አካላት (Simulators)፣ በህክምና ቁሳቁሶች እና በቴክኖሎጂ የተሟሉ በመሆናቸው ተማሪዎች በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ የቀሰሙትን እውቀት ወደ ተግባራዊ ስራ ለመለወጥ እንደ ዋና ድልድይ ያገለግላሉ። በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች ግቢ ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም የሰርቶ ማሳያ ስልጠና የተማሪዎችን በራስ መተማመን ከማሳደጉም በላይ፣ በህክምና ስራ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ስህተቶችን በመቀነስ የህብረተሰቡን ደህንነት የሚያረጋግጥ ነው። በመሆኑም የኮሌጆቹ የሰርቶ ማሳያ ማዕከላት የነገውን የጤና ዘርፍ እጣ ፈንታ በመቅረጽ ረገድ ተተኪ የማይገኝላቸው የተግባር ማማዎች መሆናቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ የህክምና ታሪክ ውስጥ በተለይም የጤና ባለሙያዎችን በብቃትና በብዛት አሰልጥኖ ለዘርፉ ከሚያበረክቱ ተቋማት መካከል ትልቅ ስም ያለው ነው፡፡ ይህ አንጋፋ ተቋም የማስተማርና የስልጠና ስራውን ለረጅም ዓመታት በብቃት እንዲያስቀጥል ካስቻሉት አንዱ ደግሞ በኮሌጁ የተደራጀና የተሟላ የሰርቶ ማሳያ (Skill Lab and Demonstration) ማዕከል መኖሩ እንደሆነ የኮሌጁ የስራ ኃላፊዎች ይናገራሉ፡፡

በኮሌጁ የሰርቶ ማሳያና ግብዓቶች ዳይሬክተር የሆኑት የወርቅውሃ ጌታቸው የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች የሰርቶ ማሳያ ማዕከላት እንዲኖራቸው መደረጉ ብቁና ተወዳዳሪ ባለሙያዎችን ለማፍራት እጅግ ከፍተኛ ጥቅም አለው ይላሉ። ዳይሬክተሯ አክለውም፣ የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብቁና ተወዳዳሪ ተማሪዎችን የሚያፈራበት፣ በሀገሪቱ አሉ በሚባሉ ተመሳሳይ ተቋማት የሚገኙ አምስት የሰርቶ ማሳያ ማዕከላት መኖራቸው ብቁ ባለሙያዎችን በማፍራት ረገድ ቀደምት ስሙን ጠብቆ እንዲጓዝ ማስቻሉን ገልጸዋል።

በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጁ በቅድመ-ምረቃና በድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር ከሃያ በሚበልጡ የትምህርት ዘርፎች የማስተማር አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልጸው፣ ከእነዚህም መካከል በአስራ ሦስቱ የቅድመ-ምረቃ ትምህርት ዘርፎች የሚማሩ ተማሪዎች በንድፈ-ሀሳብ የተማሩትን ትምህርት በሰርቶ ማሳያና ስኪል ላብ ክፍል በተግባር ሰው በሚመስሉ የተለያዩ አሻንጉሊቶችና ሞዴሎች ላይ እንደሚለማመዱ ተናግረዋል፡፡

የሰርቶ ማሳያ ማዕከሉ ዋና ተግባር የንድፈ-ሀሳብ እውቀትን ከተግባራዊ ክሊኒካዊ ክህሎት ጋር ማገናኘት ነው የሚሉት ዳይሬክተሯ፣ በማዕከሉ ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ታካሚዎች ከመሄዳቸው በፊት ደህንነቱ በተጠበቀና ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ በተለያዩ የማስተማሪያና አስመሳይ መሣሪያዎች ላይ እንዲለማመዱ እንደሚደረግ ያብራራሉ።

እንደ ዳይሬክተሯ ማብራሪያ፣ የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በኮሌጁ ግቢ ውስጥ የሚገኘው ትልቁ ሰርቶ ማሳያ ወይም ማዕከላዊ ሰርቶ ማሳያን ጨምሮ በፒያሳ በሚገኘው ዋናው ካምፓስ 5 ልዩ ልዩ የሰርቶ ማሳያ ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ በእነዚህም ፋርማሲ፣ ላብራቶሪ፣ ሚድዋይፈሪ (ማዋለድ) እና ጤና ኢንፎርማቲክስ የሚማሩ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ያደርጋሉ፡፡

ሰርቶ ማሳያዎቹ ከጤና ባለሙያዎች በተለይም ከሙያ ብቃት ማነስ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ከማቃለል አኳያ ምን ድርሻ ይኖራቸዋል? ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ፣ በኮሌጁ ከሚሰጡ ትምህርቶች ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነው በሰርቶ ማሳያ (Skill Lab) ላይ እንደሚሰራ አውስተው፣ ይህም በዘርፉ ብቁ፣ ተወዳዳሪና የተሻለ ባለሙያ በመፍጠር ረገድ ጉልህ ድርሻ እንዳለው አረጋግጠዋል፡፡

> **“የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሰርቶ ማሳያ ማዕከላት ተግባራዊ ልምምድም የተካኑ፣ በራስ የሚተማመኑ እና ለታካሚዎች ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጡ ባለሙያዎችን ለሀገር ለማበርከት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ አርአያነት ያለው በጎ ጅምር ነው”**

ማዕከሉ ዘመኑን በዋጁ የተሻሉ የህክምና መሳሪያዎችና የመማሪያ ግብዓቶች የተደራጀ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች ምንም አይነት የግብዓት እጥረት ሳያጋጥማቸው ማወቅ ያለባቸውን በተደጋጋሚና በአግባቡ ተምረው የሚወጡበት ተቋም ነው፡፡ በማዕከላቱ የሚደረጉ የተግባር ልምምዶች በርካታ ጥቅሞች አስገኝተዋል፡፡

ተማሪዎች በሕይወት ባሉ ህመምተኞች ላይ ከመለማመዳቸው በፊት በሰው ሰራሽ ሞዴሎች ላይ እንዲለማመዱ መደረጉ ሳይፈሩ እንዲሳሳቱና ከስህተታቸው እንዲማሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ይህም ተደጋጋሚ ልምምድ በማድረግ ወደ እውነተኛ ህሙማን ከመሄዳቸው በፊት ሙሉ እምነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ተማሪዎች ገና በቂ እውቀትና ክህሎት ሳይኖራቸው በታካሚዎች ላይ በመለማመድ ሊያደርሱ የሚችሉትን የህክምና ስህተት ያስቀራል። በተጨማሪም የታካሚዎችን መብትና ክብር ሳይነካ የህክምና ጥበባትን በነጻነት ለመማር ይረዳል።

እንደ ደም መውሰድ፣ መርፌ መውጋት እና የተወሳሰቡ የቀዶ ጥገና ተግባራትን በተደጋጋሚ በመስራት ክህሎትን ለማዳበር ያስችላል። መምህራንም የተማሪዎችን አሰራር በቅርብ ርቀት ሆነው ደረጃ በደረጃ ለመገምገም እና በማስተካከል ረገድ የማዕከላቱ እገዛ ቀላል አይደለም፡፡

በእውነተኛ ህይወት የማይገኙ አጋጣሚዎችን መፍጠር ሌላኛው ማዕከላቱ የሚያስገኙት ጥቅም መሆኑን ዳይሬክተሯ ገልፀዋል፡፡ ነጥቡን ሲያብራሩም፣ በብዛት በሆስፒታል የማይከሰቱ ነገር ግን ወሳኝ የሆኑ ድንገተኛ የጤና እክሎችን በሲሙሌሽን (Simulation) በመፍጠር ተማሪዎች ለድንገተኛ አደጋዎች ያላቸውን ዝግጁነት ያጠናክራሉ ብለዋል፡፡

የቡድን ስራ ባህልን ማዳበርም ከማዕከላቱ የሚገኝ ተጨማሪ ጥቅም ነው፡፡ ምክንያቱም የተለያየ የጤና ዘርፍ ተማሪዎች (ዶክተሮች፣ ነርሶች እና ሚድዋይፎች) በጋራ በመሆን የድንገተኛ ጊዜ ህክምናን በቡድን እንዴት መስጠት እንዳለባቸው እንዲለማመዱ ያደርጋሉና።

በተማሪዎች መካከል ፍትሃዊ ፈተና ለማካሄድ በተለይም ተማሪዎችን በተግባር ለመመዘን የሚረዳውን የOSCE (Objective Structured Clinical Examination) ፈተና በዚሁ ማዕከል ውስጥ በተደራጀ መልኩ ለመስጠት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

የሰርቶ ማሳያና ግብዓቶች ዳይሬክተሯ የወርቅውሃ ጌታቸው አክለው እንደገለጹት፤ ተግባራዊ ስልጠናዎችን ማስተናገድ እና ማስተካከል፣ ተግባራዊ ክሊኒካዊ ልምምዶችን ማዘጋጀት፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ጥራትና ክምችትን መቆጣጠር፣ እንዲሁም የደህንነትና የኢንፌክሽን መከላከያ ደንቦችን መተግበር ዋና ዋና ተግባራት ናቸው። ከዚህ ባለፈም ለፈተናዎችና ለአዳዲስ ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የዕለት ተዕለት ስራቸው አካል ነው።

በእያንዳንዱ ሴሚስተር መጀመሪያ ላይ ለክፍሉ አዲስ ለሆኑ ተማሪዎች ስለ መሣሪያዎቹና ስለ ማዕከሉ ሕግና ሥርዓት በቂ ገለጻ ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪም ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ተግባራዊ የችሎታ መመዘኛ ፈተናዎች በሚሰጡበት ወቅት ለመምህራንና ለፈታኞች አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ እንደሚደረግ ዳይሬክተሯ ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች የሰርቶ ማሳያ ማዕከላትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂና ግብዓቶች አሟልተው መስራታቸው፣ በፅንሰ-ሀሳብና በተግባር መካከል ያለውን ክፍተት በማጥበብ ረገድ የሚተካው የለውም። የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እያካሄደ ያለው ይህ ተግባራዊ ልምምድም የተካኑ፣ በራስ የሚተማመኑ እና የታካሚዎችን ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጡ ባለሙያዎችን ለሀገር ለማበርከት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ አርአያነት ያለው በጎ ጅምር ነው።

# የወላጆችን ጫና ያቃለለው ማዕድ


ፎቶ ከገፀ ድር
ለወላጆች እፎይታ የሰጠው የተማሪዎች ምገባ

> የተማሪዎች ምገባ ከመጀመሩ በፊት ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ወላጆች ልጆቻቸውን በቂ የሆነ ቁርስ ለመመገብና ምሳ አስረው ለመላክ ይቸገሩ ነበር። ምገባው ይህን ጭንቀት አስወግዶል። ወላጆች በየዕለቱ ለምግብ የሚያወጡትን ወጪ እንዲቀንሱ አድርጓል

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ወርሃ መስከረም የአዲስ ዓመት መባቻ ብቻ አይደለም፤ የተለያዩ በዓላት የሚከበሩበት ጭምር እንጂ፡፡ ይህ ደግሞ ወላጆችን ለተለያዩ ወጪዎች እንደሚዳርግ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ላይ ትምህርት የሚጀመርበት ወር እንደመሆኑ መጠን ለዚህ የሚሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት የወላጆች ሌላኛው ፈተና ሆኖ ቆይቷል፡፡ ልጅን ቁርስ አብልቶ እና ምሳ ቆጥሮ ወደ ትምህርት ቤት መላክ በዚህ ረገድ የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ምክንያት የትምህርት ቤት መከፈት ለብዙ ቤተሰቦች የጭንቀት ምንጭ ሆኖ ቆይቷል። አንዳንድ የተማሪ ወላጆች ቁራሽ ዳቦ፣ አለፍ ሲልም "ምሳ ይዟል" እንዲባል ብቻ ባዶ ምሳ እቃ አስይዘው የሚልኩባቸው ጊዜያት እንደነበሩ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ይህ ሲሆን ተማሪዎች ከትምህርት የማቋረጥ፣ ክፍል ውስጥ በአግባቡ ያለመከታተልና ውጤታማ ያለመሆንም ችግሮች ያስከትል እንደነበር ይታወሳል፡፡

ይህንኑ መራር እውነታ ወይዘሮ በቀለች አንበሴ ያረጋግጣሉ፡፡ ወይዘሮ በቀለች በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ነዋሪ ናቸው፡፡ በየሰፈሩ ልብስ አጥበው፣ ሰው ቤት ሰርተው ለልጆቻቸው ዳቦ ይዘው ይገባሉ፡፡ ባለቤታቸውም በተመሳሳይ እቃ በመሸከምና በመጫን ስራ ላይ ነው የተሰማሩት፡፡ ይህን ስራ በአግባቡ እንዳይሰሩ የሚያደርግ የኩላሊት ግፊት እንዳለባቸው በሀኪም ተነግሯቸዋል፡፡

የተማሪዎች የምገባ መርሃ ግብር ከመጀመሩ በፊት ያለውን ጭንቀት ወይዘሮ በቀለች ሲገልፁ፤ "ቤት ያፈራውን ወይም የተገኘውን ቂጣም ሆነ ሌላ ነገር ለልጄ በምሳ እቃ አድርጌ እልከው ነበር። እሱም ጓደኞቹን በመፍራት ከእነሱ ርቆ ብቻውን እንደሚበላ ይነግረኛል። ለልጆቼ የማስርላቸው ሳይኖረኝ ሲቀር እንደ እናት ከባድ ሲቃይ ይሰማኝ ነበር" ሲሉ ያስታውሳሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚሰራቸው ሰው ተኮር ስራዎች አንዱ የሆነው የተማሪዎች የቁርስና ምሳ ምገባ መመቻቸቱ ልጆቻቸው ሳይርባቸው እንዲማሩ እንዳደረጋቸውና እሳቸውንም "ዛሬ ምን ቁርስ ልመግባቸው፣ ምሳስ ምን ልቋጥርላቸው" ከሚል ጭንቀት እንደገላገላቸው ይገልጻሉ፡፡

እየተማሩ ያሉ ሁለት ልጆች እንዳሏቸው የሚናገሩት ወይዘሮ በቀለች፣ በአሁኑ ወቅት ያለሀሳብ ልጆቻቸውን እያስተማሩ ነው፡፡ ድጋፉ ጫናቸውን በማቃለሉ በኑሯቸው ደስተኛ ናቸው። ልጆቻቸው ቁርስና ምሳ መመገብ ከሚችሉት ሌሎች ተማሪዎች እኩል ተመግበው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ በማየታቸው "ትልቅ የአዕምሮ ሰላም አግኝቻለሁ" ይላሉ፡፡ ይህን ሰው ተኮር ተግባር በመተግበር በዝቅተኛ ገቢ ለሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ ላደረገላቸው መንግስት ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ የአራዳ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ሰላም ደሳለኝ ናቸው፡፡ ብቻቸውን የሚያሳድጉት የ7ኛ ክፍል ተማሪ ልጅ እንዳላቸው የሚናገሩት ወይዘሮዋ፣ "ምገባው ከመጀመሩ በፊት ቤት ውስጥ የተገኘውን ሻይም ሆነ ዳቦ ሰጥቼ እልከዋለሁ፡፡ የሚያስጨንቀኝና ሰላሜን የሚነሳኝ ምሳ ምን ልቋጥርለት የሚለው ነበር፡፡ ምገባው ከዚህ ሁሉ ጭንቀት ገላግሎኛል" ሲሉ ልጃቸው የመርሃ ግብሩ ተጠቃሚ በመሆኑ ደስተኛ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ አሁን ላይ ከእሳቸው የሚጠበቀው የትምህርት ቤት ቁሳቁሱን ይዞ ሳይረፍድበት እንዲሄድ ማድረግ ብቻ እንደሆነ አክለዋል፡፡

"በየቀኑ የቁርስ እና የምሳ ወጭን አስቀርቶልኛል፡፡ በተለይ በርካታ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ይህንን ወጪ በየቀኑ መሸፈን ቀላል የማይባል በጀት የሚጠይቅ በመሆኑ ጫናው ከባድ ነው፡፡ መንግስት ልጄን እየመገበ ማስተማሩ ህይወቴን ያለጭንቀት እንድኖር አድርጎኛል" ሲሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፀዳለች ሚካኤል በበኩላቸው፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚሰራቸው ሰው ተኮር ስራዎች አንዱ የተማሪዎች ምገባ ነው፡፡ የምገባው ዓላማ ምግብ መስጠት ወይም መመገብ ብቻ ሳይሆን፣ ተማሪዎች በቂና የተመጣጠነ ምግብ አግኝተውና ጤናማ ሆነው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማስቻል ነው። ሳይራቡ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ለማድረግ፣ መጠነ መድገምንና ማቋረጥን ለማስቀረት፣ እውቀት ያለውና የተሻለ ትውልድ ለመገንባት ነው፡፡ ይህ መደረጉ በቤተሰብ ላይ የሚፈጠረውን የኢኮኖሚ ጫና በመቀነሱ ላቅ አይተኬ ሚና አለው" ብለዋል፡፡

የተማሪዎች ምገባ ከመጀመሩ በፊት ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ወላጆች ልጆቻቸውን በቂ የሆነ ቁርስ ለመመገብና ምሳ አስረው ለመላክ ይቸገሩ ነበር፡፡ ምገባው ይህን ጭንቀት አስወግዶል፡፡ ወላጆች በየዕለቱ ለምግብ የሚያወጡትን ወጪ እንዲቀንሱ እንዳደረጋቸው ተናግረዋል፡፡

ምገባ ኤጀንሲ በአዲሱ የትምህርት ዘመን ስለሚከናወነው የምገባ ስራ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የሚናገሩት ዋና ዳይሬክተሯ፣ ከ1 ሚሊዮን በላይ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንደሚመገቡ ገልፀዋል፡፡

የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን ከግብዓት ቀጥሎ ምገባው ወሳኝነት አለው ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፣ መጋቢ እናቶች በተሟላ አቅም ወደ ስራቸው እንዲገቡ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩ የመጋቢ እናቶችን የፍጆታ እቃ ክፍተቶችን ለይቶ የገበያ ትስስር በመፍጠር እንዲቀርብ ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ ገለጻ፣ ለተማሪዎች አካላዊ እና አዕምሯዊ ዕድገት ተስማሚ የሆነው፣ የተመጣጠነ የሳምንት የትምህርት ቤት የምግብ ዝርዝር ክለሳ ተደርጎበታል፡፡ በየዓመቱ በ6ኛ፣ 8ኛ እና 12ኛ ክፍል ፈተና እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻለ ውጤት በመመዝገብ ላይ ነው፡፡ ለዚህ ምገባው አይተኬ ሚና ተጫውቷል፡፡

ለአንድ ሀገር እድገት ቁልፍ ሚና ያለውን ብቃት ያለው የሰው ሀይል የማፍራት ስራ በሚሰራባቸው ትምህርት ቤቶች ላይ ምገባው ወሳኝነት እንዳለው የሚገልጹት ዋና ዳይሬክተሯ፤ በትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ ጤናማና በትምህርታቸው ውጤታማ ዜጎችን ለማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ወደፊትም ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ውጤታማ ማድረግ፣ የመጋቢ እናቶችን ማገዝ እና በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ እየመጣ ያለውን ለውጥ የበለጠ በማጠናከር ረገድ በየጊዜው ክትትል እና ማሻሻያ የማድረጉ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ምገባው ለተማሪዎች ከሚያስገኘው ጥቅም ባለፈ የወላጆችን የኢኮኖሚ ጫና በማቅለል ረገድ ቁልፍ ሚና እንዳለው ዋና ዳይሬክተሯ አብራርተዋል፡፡

## የአዲስ ... ከገጽ 7 የዞረ

### የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ምን ይላሉ?

ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) በተባበሩት መንግስታት በአስተዳደር፣ ድህነትና ዘላቂ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የፖለሲ አማካሪ፣ በአፍሪካ ሰብአዊ ኔትዎርክና የተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋማት ቦርድ ሰብሳቢና አባል በመሆን ሰርተዋል፡፡ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ እንደሚናገሩት፣ መንገድ ከከተማ ቁልፍና መሰረታዊ ከሚባሉ መሰረተ ልማቶች አንዱ ነው፡፡ በከተሞች የሰዎች፣ የምርትና አገልግሎት እንቅስቃሴ የተቀላጠፈ እንዲሆን እንዲሁም ኢንቨስትመንት እንዲያድግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። መንገድ ሲባል ከራሱ ባለፈ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን አቅፎ ይይዛል። የፍሳሽ መስመሮች፣ የኤሌክትሪክ፣ የስልክና ኢንተርኔት ኬብሎች፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ስርዓት ዝርጋታን ያካተተ ነው። እነዚህ ልማቶች የአንድ ከተማ ስራን ለማሳለጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በአዲስ አበባ የመንገድ መሰረተ ልማትን ተደራሽ ለማድረግ ሰፋፊ ስራዎች መሰራታቸውን ያነሱት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ፣ በተለይ በኮሪደር ልማቱ መንገዶች ምቹና ዘመናዊ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ከተሞች ጥሩ መንገድ ሲኖራቸው ጥሩ የፍሳሽ፣ ፅዳትና የተለያዩ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡

አዲስ አበባ የአፍሪካ የዲፕሎማሲና ፖለቲካ ዋና መዲና፣ በዓለም ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል እንደመሆኗ በምትሰጠው አገልግሎት፣ በፅዳትና በውበቷ ተምሳሌት መሆን ይጠበቅባታል። የመሰረተ ልማቶች መዘመን በከተማዋ መቀመጫቸውን ያደረጉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲበራከቱና ስራቸውን እንዲያቀላጥፉ ያደርጋቸዋል፡፡

ለምሳሌ፡- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኒውዮርክ ያለውን ቢሮ ወደ አፍሪካ የማዘዋወር እቅድ እንዳለው ያነሱት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ፣ አዲስ አበባ አዳዲስ ተቋማት ለመቀበል ከፈለገች ዓለም አቀፍ ሰራተኞች ሲመጡ የሚኖሩበት ቤት፣ ቢሮ፣ የሚንቀሳቀሱበት የተለያዩ ምቹ አገልግሎቶች ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የመሰረተ ልማት ተደራሽነትን ለማሳደግ የሚሰራው ስራ አዲስ አበባ ተወዳዳሪ እንድትሆንና የተለያዩ አዳዲስ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫነቷ ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ምሁሩ እንደገለፁት፣ በሰሜን እና ደቡባዊ አፍሪካ የሚገኙ በርካታ ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ መሰረተ ልማት ገንብተዋል፡፡ አዲስ አበባ ዓለም አቀፍ እውቅና ባለው ተቋም ከአፍሪካ ምርጥ የመንገድ መሰረተ ልማት ያላት ከተማ መሆኗ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ አንደኛ ለሀገር መልካም ስምና ገፅታ ይጠቅማል፡፡ አዲስ አበባ ዋና መዲና፣ የአፍሪካ ህብረት ጽህፈት ዋና መቀመጫ፣ በዓለም ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል እንደመሆኗ የከተማዋ መለወጥ የሀገር መልካም ስምና ገፅታ እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ ከተማዋ በርካታ እንግዶች የሚሳተፉበት የ"ኮፕ-32" የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ የምታስተናግድ እንደመሆኗ ዘመናዊና ጥራት ያለው መንገድ መኖሩ እንግዶች በተሽከርካሪ አሊያም በእግራቸው ከማረፊያ ቦታ ወደ ስብሰባ በቀላሉ እንዲንቀሳቀሱ፣ ከተማዋን እንዲጎበኙና እንዲዝናኑ ዕድል ይፈጥራል፡፡

በተለይ በኮሪደር ልማት የተሰሩ መንገዶች የእግረኛና ሳይክል መንገድ፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ፕላዛዎች፣ ሱቆች፣ የመኪና ማቆሚያዎችና የተለያዩ አገልግሎቶቹን ያሟሉ ዘመናዊ እንደሆኑ ያነሱት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ፣ በቀጣይ መንግስት ብቻ ሳይሆን የግል ዘርፉና ህብረተሰቡ እንዲሳተፍበት በማድረግ ማስፋት እንደሚገባ አብራርተዋል፡፡

የደቡብ ምስራቅ እስያ ሀገራት ከተሞች ያደጉት የግሉን ዘርፍ በመንገድ ግንባታው በማሳተፍና ለሚሰራው ስራ ከተጠቃሚው ገንዘብ በማሰባሰብ ነው፡፡ የከተማ አስተዳደር (Urban Governace) ህዝቡ ራሱ በመሳተፍ መሰረተ ልማት የሚያስፋፋበትን መንገድ የሚከፍት ነው፡፡ በርግጥ በኮሪደር ልማቱ የግሉ ዘርፍ በበጎ ፈቃደኝነት ተሳትፎ ማድረጉ የሚታወቅ ሲሆን ወደፊት የውዴታ ግዴታ አድርጎ ሰዎች ለሚጠቀሙበት መንገድ የሚከፍሉበት ሁኔታ በመፍጠር የመንገዶችን ተደራሽነትን ማሳደግ እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡

## መዳረሻዎችን ... ከገጽ 9 የዞረ

የሚያስችል) መተግበሪያዎች የማበልጸግ ስራ እየተሰራ ነው፡፡

በቲክቶክ፣ ኢንስታግራም፣ ኤክስ (ትዊተር) እና ፌስቡክ ላይ አዲስ አበባን የሚያስተዋውቁ ልዩ ልዩ የቪዲዮና የፎቶ ውድድሮች በማዘጋጀት የዲጂታል ንቅናቄ እየተደረገ ነው። ይህም ቱሪስቶች መጥተው እንዲጎበኙ ብቻም ሳይሆን ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ እድል የሚፈጥር እንደሆነ ወ/ሮ ፍረሂወት ይናገራሉ፡፡

ቱሪዝም በባህሪው በአንድ አካል ወይም በመንግስት ጥረት ብቻ ውጤታማ ስለማይሆን በዘርፉ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡ የአዲስ አበባ ቱሪዝም ኮሚሽንም ባለድርሻ አካላትን የመከታተል፣ የመደገፍና የማብቃት ስራዎችን ይሰራል፡፡ ለምሳሌ፡- የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሙያቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ ለቱሪዝም የሚመጥን አገልግሎት እንዲሰጡ የስራ ላይ የክህሎትና የአገልግሎት ጥራት ስልጠናዎች ይሰጣል፡፡ ለሆቴል ባለሙያዎች፣ ለቱሪስት አስጎብኚዎች እና ለታክሲ አሽከርካሪዎች የደንበኞች አያያዝ፣ የቋንቋ፣ የቱሪዝም ሥነ ምግባርና የደህንነት ጥንቃቄ ስልጠናዎች ይሰጣል።

አሁን ላይ በቱሪዝም ዘርፍ እየታየ ያለውን መነቃቃት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ህብረተሰቡ በተለይም ባህላዊና ሃይማኖታዊ በዓላትን 'የእኔ ባህል ነው' ብሎ ከማክበር ባለፈ የቱሪዝም ሀብት እና የኢኮኖሚ ምንጭ እንደሆኑ በመገንዘብ ሊጠብቋቸውና ሊንከባከባቸው ይገባል ሲሉም ዳይሬክተሯ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ እጅግ ግዙፍ እና ያልተነካ የቱሪዝም መስህብ እንዳላት የሚያነሱት የቱሪዝም መምህርና ተመራማሪው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) በበኩላቸው በተለይም መጪው የአዲስ ዓመት፣ የመስቀል እና የኢሬቻ ወቅት ከተማዋ ያላትን ጥንታዊ ባህል ከአዲሱ ዘመናዊ ውበቷ ጋር አቀናጅታ ለዓለም የምታሳይበት ወርቃማ ዕድል ነው ይላሉ።

እንደ አያሌው (ዶ/ር) ገለጻ፣ ትላልቅ የባህልና የሃይማኖት የአደባባይ በዓላት የሚከበሩበት ከመሆኑም በላይ የክረምቱ ዝናባማ ወቅት አብቅቶ አየሩ ለጉዞና ለመዝናናት እጅግ ተስማሚ የሚሆንበት መስከረም የሀገሪቱ ወርቃማ የቱሪዝም ዘመን ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ አሁኑኑ የተቀናጀ፣ ፈጣን እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የማስተዋወቅ ስራ ከተሰራ፣ አዲስ አበባ የቱሪስት ገቢዋን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም አቀፍ መድረክ "የአፍሪካ ቀዳሚ የባህል መዲና" የመሆን ታሪኳን በፅኑ መሰረት ላይ ታሳርፋለች።

የመጪውን የቱሪዝም ወቅት እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ፣ ምን መሰራት እንዳለበትና ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች እንዴት ወደ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መለወጥ እንደሚቻል የቱሪዝም ተመራማሪው ምክረ ሀሳቦችን ያስቀምጣሉ። በአሁኑ ዘመን የዓለም ቱሪስቶች የጉዞ ውሳኔ የሚያደርጉት በዲጂታል መረጃዎች ላይ ተመስርተው ነው። ስለሆነም እነዚህን ባህላዊና ሀይማኖታዊ በዓላት እንዲሁም የቱሪስት መስህቦች የሚገልጹ ጥራት ያላቸው የቪዲዮና የፎቶ እንዲሁም የታሪክ ይዘቶችን በማዘጋጀት በማህበራዊ የሚዲያ አማራጮች፣ በቱሪዝም ገጸ ድሮች እና በዓለም አቀፍ የጉዞ መድረኮች ላይ የማስተዋወቅ ስራ መስራት ይገባል።

ቱሪስቶቹ ከመጡ በኋላም አዲስ አበባ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ባከናወነቻቸው የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳርቻ ልማቶችን እንደ እንጦጦ ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ ያሉ የመስህብ ቦታዎችን እንዲጎበኙ የጉብኝት ፓኬጆችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የተቀናጀ የጉዞ መርሃ ግብር ዝግጅት ላይ ትኩረት በማድረግ መስራት ይገባል። የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝግጁነትና የእንግዳ ተቀባይነት ባህል ማጎልበትም ወሳኝነት አለው፡፡ ስለዚህ ሆቴሎችና አስተናጋጆች የአገልግሎት ጥራትን ማሻሻል፣ የባህል ምግቦችንና አልባሳትን ማስተዋወቅ፣ ፍትሃዊ የዋጋ ተመን መተግበር አለባቸው። ከትራንስፖርት አንጻርም ለቱሪስቶች የተዘጋጁ ደረጃቸውን የጠበቁ ተሽከርካሪዎች፣ ግልጽ የታሪፍ መረጃ እና የተቀናጀ የትራፊክ አስተዳደር ማዘጋጀት ይገባል። የጎብኚዎችን ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅ፣ በዓላቱ የሚከበሩባቸውንና የመስህብ ስፍራዎችን ጽዱ እና ከብክለት የጸዱ ማድረግም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን አያሌው (ዶ/ር) ምክረ ሀሳባቸውን

# ማስታወቂያ

በሲስተር አይናለም ኃይሉ ሰሙ ስም የተመዘገበ ይዞታ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090602055 ሴሪ ቁጥር L 026728 የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በ17/12/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 08 በካርታ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ሊ/ጨ/076/1 በሴሪ ቁጥር 010436 በአቶ ዘላለም ወልደአማኑኤል ዱባለ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳውቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር አዲስ የይዞታ ካርታ ቁጥር AA000020502084 የሆነው በአበበ ጌታቸው ጉደታ ስም የተመዘገበው የካዳስተር ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020502084 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 18/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር አዲስ የይዞታ ካርታ ቁጥር AA000020102357 የሆነው አምሳለ አካለወልድ ለማ ስም የተመዘገበው የካዳስተር ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020102357 ሴሪ ቁጥር R0212508 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 14/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ ሞገስ አለሙ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በሌ03/254/102-4662/00 ሴሪ ቁጥር 065916 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርትፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ማስታወቂያ

## የኦሜድላ መ/ደ/ት/ቤት
## ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የኦሜድላ መ/ደ/ት/ቤት ለ2019 ዓ/ም ለተለያዩ አገልግሎት የሚሆን ግብዓቶችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ከታች በተዘረዘሩት መሰረት ፡-

1. ሎት 1 የበጀት ኮድ 6211 የደንብ ልብስ ዕቃ-------------3500 ብር እንዲሁም ስፌቱን ብቻ ለሚወዳደሩ -----1500 ብር
2. ሎት 2 የበጀት ኮድ 6212 አላቂ የቢሮ ዕቃዎች--------------------- 4500 ብር
3. ሎት 3 የበጀት ኮድ 6213 የህትመት ስራዎች------------------------------ 1000 ብር
4. ሎት 4 የበጀት ኮድ 6214 የህክምና ዕቃ----------------------------- 1000 ብር
5. ሎት 5 የበጀት ኮድ 6215 የትምህርት ዕቃ----------------------------- 3000 ብር
6. ሎት 6 የበጀት ኮድ 6218 የፅዳት ዕቃ---------------------------------- 2000 ብር
7. ሎት 7 የበጀት ኮድ 6219 ልዩ ልዩ ዕቃዎች --------------------------- 1500 ብር
8. ሎት 8 የበጀት ኮድ 6313 የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ------------------------- 3000 ብር
9. ሎት 9 የበጀት ኮድ 6314 ቋሚ ዕቃ------------------------------------ 3500 ብር
10. ሎት 10 የበጀት ኮድ 6419 ልዩ ልዩ የመስተንግዶ ግብአቶች --------------- 1000 ብር

- በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ
- የግብር ከፋይነት ሰርተፊኬት/ቲን ያለው
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፈኬት /ቫት/ ተመዝጋቢ ሰርተፍኬት ያለው
- በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ
- ጥቃቅን እና አነስተኛ ተጫራቾች በሚያመርቱት እቃዎች የሀገር ውስጥ ምርት ብቻ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን በሌሎች በማያመርቱት ግብዓቶች ላይ አስፈላጊውን የጨረታ ማስከበሪያ በሎቱ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ መጠን የማስያዝ ግዴታ አለበት
- ጨረታው ለ10 የስራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን በ10ኛው ቀን 11፡30 ተዘግቶ በ11ኛው ቀን ጠዋት 3፡00 ሰዓት ታሽጎ ተጫራቶች እና ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 3፡30 ሰዓት ጨረታው የሚከፈት ሲሆን ነገር ግን የጨረታው መክፍቻ 11ኛው ቀን ቅዳሜ እና በዓል ቀን የሚውል ከሆነ የቀጣዩ የስራ ቀን ላይ የሚከፈት ይሆናል
- የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በኩል የተረጋገጠ ሲፒኦ ማቅረብ አለበት
- ተጫራቶች መ/ቤቱ ባቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ ዋጋ ሞልቶ ማቅረብ አለባቸው
- ተጫራቶች ለእያንዳንዱ እቃ የሚያቀርቡት ዋጋ ከነቫቱ መሆን አለበት
- ማንኛውም የጽሑፍም ሆነ የቁጥር ስርዝ ድልዝ ተቀባይነት የለውም
- በጨረታው ላይ በቀረቡት ከሎት 1 እስከ ሎት 7 እና ሎት 10 ያሉትን ዕቃዎች ተጫራቹ ( ናሙና) ወይም ሳምፕል ማቅረብ ያለበት ሲሆን የደንብ ልብስ ስፌትን በተመለከተ እሱም በሎቱ ላይ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ማስያዝ ያለበት ሲሆን የስፌት ሳምፕል ማቅረብ አለበት
- ከሎት 8 እስከ ሎት 9 ያሉትን በቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት ነገር ግን ተጫራቹ በከፊል ናሙናዎችን አቅርቦ ከሆነ ባቀረበው ናሙና ብቻ የሚወዳደር ይሆናል
- መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው
- የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ብቻ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ከግዥ ክፍል መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እና ነገር ግን ጥቃቅን እና አነስተኛ ራሳቸው በሚያመርቱት ዕቃ ብቻ ካደራጃቸው አካላት የድጋፍ ደብዳቤ ካቀረቡ መውሰድ የሚችሉ ይሆናል በሌሎች በማያመርቱት ዕቃዎች ላይ መወዳደር ከፈለጉ የጨረታ ሰነዱን የመግዛት ግዴታ አለባቸው
- አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች በሙሉ በየሎቱ የተገለፁትን አሸናፊ መሆናቸው ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ውል በተገባበት በ15 ቀናት ውስጥ ዕቃዎቹን አስገብተው ማጠናቀቅ አለባቸው

**አድራሻ ፡ - አብነት አለሙ ሜዳ 100 ሜትር ከፍ ብለው ያገኙናል**
**ስልክ ቁጥር 011-213-51-89**

**በልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ የኦሜድላ የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

ሰላሙ በለው አንዱአለም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 01 ውስጥ የሚገኝ ኮንደምንየም ቤት ካርታ ቁጥር AA0000801044761310110 ሴሪ ቁጥር 210690 በስማቸው የተመዘገበ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የ2019 በጀት ዓመት የኤሌክትሪክ መኪና ክራይ፣ የመኪና ቻርጀር ገመድ፣ የህትመት (ባነር፣ የስም ቲተር፣ መታወቂያ፣ የደረት ባጅ፣ የጠረጴዛ ባጅ፣ ሮል ሀፕ፣ ስቲከር፣ መጽሀፍ ዝግጅት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ የምስጋና የምስክር ወረቀት፣ የሽልማት ዋንጫ፣ በተለያየ) **የመኪና ክራይ፣ ዲኮርና ድንኳን፣ ዲጄ፣ ቋሚ ፈርኒቸር እቃ፣ የጽህፈት መሳሪያ፣ የጽዳት እቃ፣ የደንብ ልብስ፣ የመኪና ጌጣጌጥ፣ ቋሚ የኤሌክትሮኒክስ እቃ፣ የወጥ ቤት እቃዎች፣ የኤሌክትሮኒክስ ጥገና** በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| የሎት ቁጥር | የግዥ ዓይነት ዝርዝር /ሎት | የጨረታ ማስከበሪያ መያዣ /CPO |
|---|---|---|
| 1 | የመኪና ቻርጀር ገመድ | 50,000 /ሃምሳ ሺ ብር/ |
| 2 | ህትመት | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |
| 3 | የመኪና ክራይ | |
| 4 | ዲኮርና ድንኳን | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |
| 5 | ዲጄ | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |
| 6 | ቋሚ ፈርኒቸር እቃ | 50,000 /ሃምሳ ሺ ብር/ |
| 7 | የጽህፈት መሳሪያ | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |
| 8 | የጽዳት እቃ | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |
| 9 | የደንብ ልብስ | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |
| 10 | የመኪና ጌጣጌጥ | 50,000 /ሃምሳ ሺ ብር/ |
| 11 | ቋሚ የኤሌክትሮኒክስ እቃ | 50,000 /ሃምሳ ሺ ብር/ |
| 12 | የወጥ ቤት እቃዎች | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |
| 13 | የኤሌክትሮኒክስ ጥገና | 10,000 /አስር ሺ ብር/ |

**ማሳሰቢያ:-**

- ተጫራቾች በዘርፉ የተመዘገቡበትን የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት፣ የንግድ ስም
- ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።
- ከብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺ/ በላይ ለማቅረብ የሚወዳደሩ ተጫራቾች የቫት/VAT/ ተመዝጋቢ ሰርተፍኬት ማቅረብ አለባቸው።
- ተጫራቾች የሚያቀርቧዋቸው ሰነዶች ሁሉ ተነባቢ መሆን ይኖርባቸዋል።
- የጨረታ ማስከበሪያ በሲፒኦ /CPO/ ወይም የባንክ ጋራንቲ፣ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለበት ደረሰኝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ጥቃቅንና አነስተኛ በራሳቸሁ ምርት ብቻ ነው መወዳደር የምትችሉት።
- ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከሚዘጋበት ቀንና ሰዓት ድረስ የጨረታ ሰነድ መግዣ ለጠቅላላው ሎት የግዥ ዓይነት **የተቀመጠውን የማይመለስ 300.00 /ሦስት መቶ ብር ብቻ/ ለመስሪያ ቤታችን ለፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በመክፈል** ሰነዱን ከፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ሰባተኛ ፎቅ መውሰድ ይቻላል።
- **ፋይናንሻልና ቴክኒካል ሰነዶች ኦርጅናል እና ኮፒ በተለያየ ኤንቨሎፖች/ ፖስታዎች/በማሸግ ኦርጅናል እና ኮፒ የሚል ምልክት /ፅሁፍ/ በማድረግ በተለያየ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ማስገባት ይኖርባችኋል።**
- የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ የባንክ ጋራንቲ ወይም ጥሬ ገንዘብ የተከፈለበት ደረሰኝ ኮፒ፣ እንዲሁም ለጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት ካቋቋማቸው አካል የተሰጠ የዋስትና ደብዳቤ ኦርጅናል በታሸገ ፖስታ ውስጥ መካተት አለበት። በኦርጅናል እና በቅጅው መካከል ያለመጣጣም ቢከሰት ኦርጅናሉ፤ የበላይነት ይኖረዋል።
- በመጫረቻ ሰነዱ የቀረበው ዋጋ ጨረታው ከተከፈተበት ዕለት ጀምሮ ከ60 ቀናት በላይ የሚወስድ ከሆነ መስሪያ ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ግምገማው እስኪጠናቀቅ ድረስ ተጫራቾች ያቀረቡትን የመጫረቻ ዋጋ እንዲያራዝም የመጠየቅ መብት ያለው ሆኖ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ድርጅት ከጨረታው ይሰረዛል።
- ከተገለፀው ቀንና ሰዓት በኋላ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም።
- ጨረታው በተጠቀሰው የመክፍቻ ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልፅ የሚከፈት ይሆናል።
- ማንኛውም ተጫራች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ተመርኩዞ መጫረት አይችልም።
- ጨረታው በጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 /አስር የስራ ቀናት ክፍት ሆኖ ከቆየ በኋላ በ11ኛው ቀን ከጧቱ 4:30 ሰዓት ተዘግቶ ከጧቱ 5: 00 ስዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
- ጨረታው መዝጊያ እና መክፈቻው ቀን በበዓል ወይም ቅዳሜ እና እሁድ ላይ ከዋለ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ስዓት ይከፈታል።
- የተጫራቾች ተሟልቶ አለመገኘት የጨረታውን አከፋፈት ስነ ስርዓት አያስተጓጉለውም።
- ተጫራቾች የሚሰጡት ዋጋ ላይ ቫትን ያላካተተ ተጫራች የሰጠው ዋጋ ቫትን እንዳካተቱ ተቆጥሮ ይወሰዳል።
- መስሪያ ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት አለው። ተጫራቾች የጨረታ ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ7 የቅሬታ መስሚያ ቀናት ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። እንዲሁም ከ7 የቅሬታው መስሚያ ቀናት በኋላ ባለው 5 የስራ ቀናት ውል መውሰድ ይችላሉ።
- **ተጫራቹ ሰነድ ለመግዛት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ቁጥር 1000288861815 ላይ በማስገባት የባንክ ደረሰኝ ማምጣት አለባችው በጥሬ ገንዘብ መክፈል አይቻልም**

**ማስታወሻ፡-**

1. ይህ የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ሰነዱ አንድ አካል ተደርጎ ይቆጠራል።
2. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱ ላይ የሰፈሩትን ዝርዝር መረጃዎች በጨረታ መመሪያው ላይ ሰንጠረዥ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በትኩረት ማንበብ ይኖርባቸዋል።

አድራሻ፡-22 ለምሆቴል ዝቅ ብሎ ኤልሳ ቆሎ አጠገብ ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ 01118120087

በአዲስ አበባ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ቁ.2**

## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር /001/2019

በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 02 ፋይናንስ ጽ/ቤት በ2019 በጀት ዓመት የአንደኛ ዙር ግዥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| የሎት ቁጥር | የአገልግሎት ዓይነት | የጨረታ ማስከበሪያ (ሲፒኦ) |
|---|---|---|
| ሎት 1 | የጽህፈት መሳሪያ | 5000 |
| ሎት 2 | የደንብ ልብስ | 5,000 |
| ሎት 3 | የጽዳት እቃ | 5000 |
| ሎት 4 | የትራንስፖርት ኪራይ | 200 |
| ሎት 5 | ህትመት ስራ | 1,000 |
| ሎት 6 | የደንብ ልብስ ስፌት | 500 |
| ሎት 7 | የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች | 500 |
| ሎት 8 | የመኪና ጎማና ቸርኬ | 2000 |
| ሎት 9 | መስተንግዶ | 1000 |

ስለሆነም፡- ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርት የምታሟሉ ተጫራቾች ጨረታው ላይ መወዳደር ትችላላችሁ፡፡

1. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች አግባብነት ያለው በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ማቅረብ የሚችል፡፡
2. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች አግባብነት ያለው ንግድ ምዝገባ ማቅረብ የሚችል፡፡
3. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን፡፡
4. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች የግብር ከፋይነት መለያ ቲን ናበር ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የሀገር ውስጥ ተጫራቾች የቫት ተመዝጋቢዎች የሆኑ፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስረከቢያ ለእያንዳንዱ ሎቶች በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ/CPO/ ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገበ መሆን አለበት፡፡
8. ተጫራቾች በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን በ11ኛ ቀኑ ጠዋት 4 ሰዓት ታሽጎ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል።
9. ለእያንዳንዱ ሎት የማይመለስ የኢትዮጵያ ብር 100/አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ፋይናንስ የሥራ ክፍሎች ቦሌ ወረዳ 02 ህንጻ 4ኛ ፎቅ መውሰድ ይቻላል፡፡ ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ ሲያቀርቡ ቫት ያጠቃለለና ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች አሟልተው በታሸገ ፖስታ አንድ ኦርጅናልና አንድ ኮፒ ፋይናንስ የሥራ ክፍሎች ቦሌ ወረዳ 02 ግዥ ቡድን ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እስከ አስራ አንደኛው (11) የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ብቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያ የስራ ቀን የሚገባ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
10. ተጫራቾች በተወዳደሩበት እቃ አይነት ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ባሉት ሁለት ቀናት ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡ ከሰነዱ ጋር የተያያዘውን ስፔስፊኬሽን ማህተም በማድረግ መመለስ አለባቸው።
11. ጨረታው በዚያው ቀን ከ ጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ፋይናንስ የሥራ ክፍሎች ቦሌ ወረዳ 02 ህንጻ 4ኛ ፎቅ ይከፈታል፡፡
12. ተጫራቾች የጨረታ አሸናፊ ሆነው የተገኙባቸውን ዕቃዎችን ከአጠቃላይ ዋጋ 10% የውል ማስረከቢያ በማስያዝና ከቡድኑ ጋር የግዥ ውል ስምምነት መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡
13. ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርት ሳያሟሉ በጨረታ ላይ ለመሳተፍ መሞከር ከጨረታው ያሰርዛል፡፡
14. መ/ቤቱ ጠቅላላ ለጨረታው ከቀረበው ብዛት 20% ከፍና ዝቅ ብሎ የግዥ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
15. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
16. ከዚህ በፊት በማንኛውም ተቋም በዕቃ አቅርቦትም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ምንም አይነት ጉለት ያልታየበት፡፡

- ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የፋይናንስ የስራ ክፍሎች ግዥ ቡድን 4ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 4.1 ያናግሩን፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ ቢሮ መጥተው መጠየቅ ይችላሉ።**

**የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ፋይናንስ የስራ ክፍሎች**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ የወረዳ 02 አስተዳደርና ፋይናንስ የስራ ክፍሎች ፅ/ቤት**

አመልካች ፋይዛ አሊ በቀን 05/12/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የካርታ ቁጥር የካ/221233/11/ ሴሪ 1477457 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ10/139/4/1/253778/00 ሴሪ ቁጥር 1561740 በወ/ሮ አማረች ተፈራ ወ/ሃና ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያው መሰረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 201 AA000091305842 ሴሪ ቁጥር R 0201945 የተሰጠበት ቀን 04/10/2018 የሆነው በአቶ አደም አቡበከር መሀመድ ስም የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 14/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር --- የይዞታ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/14/13008/00 የሆነው አቶ ደሳለኝ ገልባ ዳማ ስም የተመዘገበው ካርታ እንደጠፋባቸው በቀን 20/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 774 የይዞታ ካርታ ቁጥር AA000020701123 የሆነው መሀመድ ጀማል መሀመድ ስም የተመዘገበው የካዳስተር ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020701123 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 18/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ይዞታ መለያ ቁጥር ቦሌ01/399/1199/00 ሴሪ ቁጥር R 128261 ይዞታነቱ የአቶ ግርማ ተክሌ ኪዳኔ የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የመሬት ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ አለልኝ ተረፈ ፈለቀ ስም የተመዘገበ ሊዝ ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090502839 ሴሪ ቁጥር L 0161868 የጠፋባቸው መሆኑን በ12/12/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በብ/ጄ አርአያ ዘርአይ ጊልያ ስም በቀድሞ ክፍለ ከተማ ደቡብ አዲስ አበባ፣ ከፍተኛ 23፣ ቀበሌ 13 በአዲሱ ክ/ማ በልደታ ክ/ማ ወረዳ 08፣ በካርታ ቁጥር 29222 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 13/12/2018 ዓ/ም በማመልከቻ ጠይቀውናል፣ ስለዚህ የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የቀጠለው የድል ቅብብሎሽ

**በሳህሉ ብርሃኑ**




ግራፊክስ- በእዮብ ተፈራ
በአትሌቲክስ ስፖርት ውጤታማ በመሆን የኢትዮጵያ መልካም ገፅታ ከገነቡ አትሌቶች ጥቂቶቹ

ኢትዮጵያ የጥንታዊ ታሪክ ባለቤትነቷ፣ የሉዓላዊነቷን ክብር በጽናት አስጠብቃ ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ፋና ወጊ መሆኗ፣ የራሷ የሆነ የዘመን አቆጣጠርና ፊደል ባለቤት መሆኗ፣ በዓለም ልዩ ስፍራ እንዲሰጣት ያደርጋታል። በስፖርቱ መስክም እንደዚሁ የኢትዮጵያ ስም በዓለም መድረክ ላይ ደምቆ እንዲታይ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል የድል አድራጊ አትሌቶች ብቃት አንደኛው ነው።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዓለም አቀፍ የሩጫ ውድድሮች በተለይም በማራቶን እና በረጅም ርቀት የሚያስመዘግቡት ድል ሀገሪቱን የዓለም የረጅም ርቀት ስፖርት መዲና አድርጓታል፡፡ በትውልድ ቅብብሎሽ የላቀ ወጤት እያመጣ የቆየው አትሌቲክሱ የኢትዮጵያን ስም ከፍ አድርጎት ቆይቷል። ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ስፖርት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ስም፣ ዝና እና ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ታሪክ በርካታ የወርቅ፣ የብር እና የነሐስ ሜዳሊያዎችን ሰብስባለች፡፡

የአትሌቲክሱ ስኬት የኢትዮጵያውያን አንድነትና ተስፋ መገለጫም ጭምር ነው። የአትሌቶች ድል ሲከበር፣ የሀገሪቱ ባንዲራ ከፍ ብሎ ሲውለበለብ፣ መላው ሕዝብ እንደ አንድ ቤተሰብ በአንድነት ይቆማል። በተለይም የረጅም ርቀት ሩጫ ማለት ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ማለት ደግሞ የረጅም ርቀት ሩጫ ነው እስከማለት ተደርሷል። ይህ ግንኙነት የተፈጠረው ደግሞ እንዲሁ በአጋጣሚ አይደለም። በርካታ አትሌቶች በጽናትና በትጋት ሰርተው ባገኙት ድል እንጂ።

በሮም አደባባይ (እ.ኤ.አ. 1960) ያውም በባዶ እግሩ ታላቁን ማራቶን ድል በማድረግ በአበበ ቢቂላ አንድ ብሎ የጀመረው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስኬት፣ በቶኪዮ ጎዳናዎችም በዚሁ ጀግና ታሪክ ከፍ ብሎ ታይቷል፡፡ ማሞ ወልዴን በማስከተል በሜክሲኮም ነግሷል፡፡ በትውልድ ቅብብሎሽ ማርሽ ቀያሪው ምሩፅ ይፍጠር በአንድ ኦሎምፒክ አምስትና አስር ሺህ ሜትር ድርብ ድል ባለቤት፣ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ መሠረት ደፋር፣ ሚሊዮን ወልዴና የመሳሰሉት ጀግኖች የወርቅ፣ እንዲሁም የብርና የነሐስ ሜዳሊያውን በማጥለቅ ዓለምን ሲያስደምሙ ኖረዋል፡፡

በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያና ሜዳሊያ የተገናኙት ገና ከጅምሩ ፊንላንድ ሄልሲንኪ በተደረገው የመጀመሪያው ውድድር ነበር። በዚህ የመጀመሪያው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለኢትዮጵያ እንዲሁም ለአፍሪካ የመጀመሪያውን ሜዳሊያ ያስገኘው አትሌት ከበደ ባልቻ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር እስካሁን ባከማቸቻቸው ሜዳሊያዎች ከዓለም ሰባተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። የኢትዮጵያ አጠቃላይ የሜዳሊያ ሰንጠረዥ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ታሪክ (እስከ 2025 ቶኪዮ ዓለም ቻምፒዮና ድረስ 35 ወርቅ፣ 40 ብር ፣ 33 የነሐስና በአጠቃላይ 108 ሜዳሊያዎችን ወስዳለች።

የኢትዮጵያ ተሳትፎ በኦሎምፒክ ጨዋታዎች ታሪክ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል በመካከለኛና ረጅም ርቀት አትሌቲክስ ሩጫዎች ላይ የተመሰረተ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ስም ያስጠራ ነው። ኢትዮጵያ በኦሎምፒክ ታሪኳ ያገኘቻቸው አጠቃላይ ሜዳሊያዎች ብዛት 62 ደርሷል፡፡ የመጀመሪያውን የኦሎምፒክ ወርቅ ሜዳሊያ ለኢትዮጵያ ያስመዘገበው አትሌት አበበ ቢቂላ በ1960ው የሮም ኦሎምፒክ በባዶ እግሩ ሮጦ ማራቶኑን አሸንፎ ነበር። በመቀጠልም በ1964ቱ የቶኪዮ ኦሎምፒክ ደግሞ በማሸነፍ ታሪክ ሰርቷል።

በምዕራቡ ዓለም የሰውነት አቋም ስሌቶች፣ በላቦራቶሪ ምርምሮች እና በዘመናዊ ስፖርታዊ ቴክኖሎጂዎች ብቻ የሚለካው የአትሌቲክስ ስኬት፣ የኢትዮጵያ ሰማይ ስር ሲታይ ፍጹም የተለየ ገጽታ አለው ይላል ብሪታንያዊ አንትሮፖሎጂስት እና ሯጭ ማይክል ክራውሊ፡፡ የምስራቅ አፍሪካ የረጅም ርቀት ሯጮች በዓለም አቀፍ ደረጃ አቻ የሌላቸውን የበላይነት እንዴት ሊጎናጸፉ ቻሉ? የሚለውን ምስጢር ለመረዳት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ 15 ወራትን ከታላላቅ አትሌቶች ጋር አሳልፏል።

ማይክል ክራውሊ የኢትዮጵያ ቆይታውን መነሻ አድርጎ በጻፈው "Out of Thin Air: Running Wisdom and Magic from Above the Clouds in Ethiopia" በተሰኘው ጽሑፍ ላይ እንዳሰፈረው በኢትዮጵያ ሩጫ የግል ጉዳይ ብቻ አይደለም። በማለዳው ጨለማ አዲስ አበባ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣት አትሌቶች በአንድነት ተሰልፈው አውራ ጎዳናዎችንና የእንጦጦ ተራሮችን ሲያቋርጡ፣ ልክ እንደ አንድ ወፍ መንጋ ሆነው እርስ በርስ የሚደጋገፉበት የቡድን መንፈስ ይታያል ይላል ፀሐፊው።

የኢትዮጵያ ሯጮች ስኬት ከዘመናዊ የላቦራቶሪ ቀመሮች ይልቅ፣ ከቀላል አኗኗር፣ ከከፍተኛ ተፈጥሯዊ ጽናት እና ከውስጣዊ የስነ-ልቦና ጽናት ጋር የተሳሰረ ነው። ብርታት በአንድ ግለሰብ አካል ውስጥ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፣ አትሌቶች በአንድነት ሲሮጡ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ ኃይል መሆኑንና በጋራ መሮጥ ትልቅ ጉልበት ሲሰጥ ተመለከቻለሁ ይላል ማይክል ክራውሊ።

በስልጠናም ወቅት ተራ በተራ መሪ ሆኖ ሌሎችን ማስኬድ የሌላውን ሸክም እንደ መጋራት እንደሚቆጠርና የመሪውን እግር ተከትሎ መሮጥ ደግሞ ከእሱ የሚወጣውን አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ኃይል በመመጋገብ የሚከናወን መሆኑንም ያስረዳል፡፡

በጥቅሉ ማይክል ክራውሊ የ15 ወራት የኢትዮጵያ ቆታውን "በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውስጥ ስኬት የግለሰብ ብቻ ሳይሆን የጋራ ትንፋሽ፣ የትከሻ መደጋገፍ እና ከሰውነት ያለፈ የማይታይ የኃይል ስርጭት ውጤት ነው" ሲል ይገልፀዋል።

አትሌቶች ከግል ክብራቸው ይልቅ ሀገርን በማስቀደም በቡድን ስራ የሚያስመዘግቡት ድል "አረንጓዴው ጎርፍ" የሚል ታዋቂ ስያሜ አሰጥቷቸዋል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሲዘከር አይረሴው የአረንጓዴው ጎርፍ ታሪክ ተጠቃሽ ነው፡፡ የአረንጓዴውን ጎርፍ ዝና ያናኙ፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ በዓለም አደባባይ ያውለበለቡ በርካታ ባለውለታዎች ድንቅ ችሎታና ገድል ለኢትዮጵያ መድመቂያዋ ሆኖ ለዓመታት የሚዘከር ነው፡፡

በሌላ በኩል ሶሺዮሎጂስት እና አንትሮፖሎጂስት የሆኑት ፈረንሳዊው ቤንዋ ጎዲን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ታሪካዊ አካሄድን፣ ተቋማዊ አወቃቀሮችን እንዲሁም ስፖርቱ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ፋይዳ በጥልቀት በመመርመር ይታወቃሉ። በምርምር ስራቸው የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ስኬት ከግለሰብ ድል ባለፈ ከህብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ እና ከባህላዊ እሴቶች ጋር አያይዘው ያቀርቡታል።

አትሌቲክሱ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ቦታ እና ስፖርቱ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መስተጋብር የሚጫወተውን ሚና በሶሺዮሎጂ አቀራረብ ይተነትናሉ። በዚህ ዙሪያ ባደረጓቸው ጥናቶች መሠረት፣ አትሌቲክስ ከቀላል የስፖርት ውድድር ባለፈ የሀገሪቱን ታሪካዊ ገጽታ የሚገነባ፣ ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክር እና ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር የሚያስተሳስር ወሳኝ የዲፕሎማሲ መሳሪያ ጭምር ነው።

ከአበበ ቢቂላ ባዶ እግር ታሪካዊው ስኬት እስከ ዛሬው የትውልድ ቅብብሎሽ ድረስ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ከስፖርት ማዕቀፍ በላይ የብሔራዊ አንድነት፣ የጽናትና የኩራት መገለጫ ሆኖ ዘልቋል። ማይክል ክራውሊ እንዳስተዋለው ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ድል በአንድ ግለሰብ ላቦራቶሪ ውስጥ የሚሰላ ሳይሆን፣ በማለዳው ጫካ ውስጥ አብሮ በመሮጥ፣ የሌላውን ሸክም በመጋራት እና የጠንካራ የቡድን ውጤት ነው። ዛሬም በዓለም አቀፍ አደባባዮች ሲውለበለብ የምናየው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ትውልድን አሻግሮ ለቀጣዮቹ ዘመናት የሚቀጥል የኢትዮጵያዊነት ሕያው የጽናት ዓርማ ነው።

> **ከአበበ ቢቂላ ባዶ እግር ታሪካዊው ስኬት እስከ ዛሬው የትውልድ ቅብብሎሽ ድረስ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ከስፖርት ማዕቀፍ በላይ የብሔራዊ አንድነት፣ የጽናትና የኩራት መገለጫ ሆኖ ዘልቋል**